አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
የቋንቋዎች ጥናት ተቋም
የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ-ጽሁፍ ክፍለ ትምህርት
የኮርሱ ስም ፡- የመመረቂያ ጥናት ትልም/ Master's Thesis

# ስነ-ፅሁፋዊና ኢ-ስነፅሁፋዊ ፅሁፎች የአማርኛ ቋንቋን የአንብቦ መረዳት ክሂልን በማሻሻል ረገድ ያላቸው ሚና በሻምቡ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት በ10ኛ ክፍል ተተኳሪነት

በ
ወንድሙ ዱባለ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
ሰኔ 2015 ዓ.ም

# ስነፅሁፋዊና ኢስነፅሁፋዊ ፅሁፎች የተማሪዎችን የአማርኛ ቋንቋ የአንብቦ መረዳት ክሂልን ከማሻሻል ረገድ ያለቸው ሚና (በሻምቡ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በአስረኛ ክፍልተተኳሪነት)


አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የቋንቋዎች ጥናት ተቋም

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ-ጽሁፍ ክፍለ ትምህርት


አማርኛን ለማስተማር ለ2ኛ ድግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት


አማካሪ፡- አቶ ደረጀ ገብሬ



ሰኔ 2015 ዓ.ም.

አዲስ አበባ

**ስነፅሁፋዊና ኢስነፅሁፋዊ ፅሁፎች የተማሪዎችን የአማርኛ ቋንቋ የአንብቦ መረዳት ክሂል ከማሻሻል ረገድ ያላቸው ሚና በሻምቡ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በሚል ርዕስ በወንድሙ ዱባለ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረበው ጥናት በውጭና በውስጥ ፈታኞች ተገምግሞ ተቀባይነት አግኝቷል፡፡**

## የፈታኞች ቦርድ አባላት

**የአማካሪ ስም ..................................ፊርማ.....................ቀን.........................**

**የውጭ ፈታኝ ስም ............................ፊርማ.......................ቀን......................**

**የውስጥ ፈታኝ ስም............................ፊርማ.......................ቀን........................**

# ማረጋገጫ

ስነ-ፅሁፋዊና ኢ-ስነ-ፅሁፋዊ ፅሁፎች የተማሪዎችን የአማርኛ ቋንቋ የአንብቦ መረዳት ክሂልን ከማሻሻል ረገድ ያላቸዉ ሚና (በሻምቡ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርትቤት በአስረኛ ክፍል ተተኳሪነት) በሚል ርዕስ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የቋንቋዎች ጥናት ተቋም የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሁፍ ክፍለ ትምህርት የአማርኛ ትምህርት ፕሮግራም ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ያቀረብኩት ይህ ጥናት ከዚህ በፊት በማነኛዉም ግለሰብ ያልተሰራ የኔ ወጥ ስራ መሆኑ፤እንዲሁም የተጠቀምኩባቸዉ ድርሳናትም በትክክል በዋቢነት የጠቀስኳቸዉ መሆኑና አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲም የጥናቱ ህጋዊ ባለቤትነት ያለዉ መሆኑን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

ስም…………………………………………

ፊርማ………………………………………..

ቀን…………………………………………

# ማስታወሻነቱ

ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ ማስታወሻነቱ ለዉዴ ባለቤቴ ለትንግርት ጌታቸው እና ከልብ ለምወዳትና ዘወትር ለምናፍቃት ልጄ ለየትምወርቅ ወንድሙ ይሁንልኝ፡፡

## ምስጋና

ከሁሉ አስቀድሜ ለሁሉም ዕዉቀትን ለሚያድለዉ ለልዑል እግዚአብሔር የከበረ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡በማስቀጠል ይህ ጥናት ከግብ እንዲደርስ አስፈላጊ የሆኑ ሙያዊ ምክሮችንና አስተያየቶችን በመለገስ በተጨማሪም ረቂቅ ጽሁፉን ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ ደጋግመዉ በማንበብና በማረም ከፍተኛ አስታዋጽኦ ላደረጉልኝ አማካሪዬ ለአቶ ደረጀ ገብሬ ከልብ የመነጨ ምስጋናየን አቀርባለሁ፡፡

ትምህርቱን ከጀመርኩበት ጊዜ አንስቶ የተለያዩ ነገሮች ማለትም ለትምህርት አስፈላጊ የሆኑ ቁሳቁሶችን በማቅረብ፣አማካሪ በመመደብና ለትናትና ምርምር የሚሆን ገንዘብ በማገዝ ድጋፍ ላደረገልኝ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ከፍ ያለ ምስጋና አቀርባለሁ፡፡

ሌላዉ በዚህ ጥናት ትግበራ ወቅት የሙከራ ትምህትርቱን በመስጠት መረጃ እንድሰበስብ ለተባበሩኝ ለሻምቡ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መምህራን፣ተማሪዎችና የአስተዳደር ሰራተኞች ምስጋናዬን ለመግለጽ እወዳለሁ፡፡

እንዲሁም ዘወትር ከጎኔ በመሆንና የቻሉትን ሁሉ በማድረግ ከዚህ ደረጃ እንድደርስ ለረዱኝ መ/ር ተመስገን ፍቅሩ ፤መ/ርት ዳኛነሽ አይሸሽም፣ መ/ር አለማየሁ በቀለ እና ቤተሰቦቼ ከፍ ያለ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

## ማውጫ

| ይዘት | ገፅ |
|---|---|


ማስታወሻነቱ.........................................................................................i
ምስጋና..............................................................................................ii
የይዘት ማውጫ.....................................................................................iii
የሠንጠረዥ ማውጫ..................................................................................v
አህፅሮተ ጥናት.......................................................................................vi
1 መግቢያ ........................................................................................ 1
1.1. የጥናቱ ዳራ ................................................................................ 1
1.2. የጥናቱ አነሳሽ ችግር ..................................................................... 4
1.3. የጥናቱ መሰረታዊ ጥያቄዎች............................................................. 7
1.4. የጥናቱ ዓላማ............................................................................... 6
1.5. የጥናቱ ጠቀሜታ........................................................................... 6
1.6. የጥናቱ ወሰን ............................................................................... 6
2. የተዛማጅ ድርሳናት ክለሳ.................................................................. 8
2.1. የአንብቦ መረዳት ምንነት................................................................ 8
2.2 የአንብቦ መረዳት ንድፈ ሀሳብ............................................................ 8
2.3. የአንብቦ መረዳት ሞዴሎች............................................................. 12
2.4. ስነፅሁፋዊ ስራዎችን ተጠቅሞ ቋንቋን ማስተማር..................................... 14
2.4.1. ቋንቋን መሰረት ያደረጉ ስነ ዘዴያዊ አቀራረቦች ............................... 17
2.4.2. ከአንድ አሀድ ውስጥ የሚዘጋጁ መልመጃዎች አይነትና ባህሪያት ................... 19
2.4.2.1. የመልመጃዎች ባህሪያት.............................................................. 20
2.4.2.2. የመልመጃዎች አይነት ............................................................... 20
2.4.2.2.1. የቋንቋ መልመጃዎች................................................................ 21
2.4.2.3. የስነ-ፅሁፍ መልመጃዎች ............................................................ 22
2.5. የግጥምና የአጭር ልቦለድ ባህርያት .................................................. 23
2.6. ኢስነፅሁፋዊ ፅሁፍ........................................................................ 24
2.7. የሀገር ውስጥ ጥናቶች ቅኝት............................................................ 25
3. የጥናቱ ዘዴ .................................................................................. 30
3.1. የጥናቱ ንድፍ............................................................................... 30
3.2. የናሙና አመራረጥ .......................................................................... 30
3.2.1. የትምርት ቤት አመራጥ ................................................................. 30
3.2.2. የተማሪዎች አመራረጥ .................................................................. 30
3.3. የማስተማሪያ ፅሁፍ ዝግጅት .............................................................. 31
3.4. የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ................................................................... 32
3.4.1 ፈተና ........................................................................................ 32
3.4.2 የፅሁፍ መጠይቅ............................................................................. 32
3.5. የመረጃ መተንተኛ ዘዴ ..................................................................... 33

4. የዉጤት ትንተና የውጤት ማብራሪያ.....................................................................34
4.1 የዉጤት ትንተና ........................................................................................ 34
4.2 የውጤት ማብራሪያ....................................................................................... 43
5.1ማጠቃለያ……………………………………………………………………………….46
5.2 መደምደሚያ ............................................................................................ 47
5.3 የመፍተሔ ሃሳብ…………………………………………………………………....47
ዋቢዎች………………………………………………………………………………... …..49
አባሪዎች……………………………………………………………………………………..53
አባሪ1. በስነፅሁፋዊና ኢ-ስነፅሁፋዊ ፅሁፍ የሚማሩ ተማሪዎች የቅድመትምህርት ፈተና ...........................................................................................................53
አባሪ 2. ስነ ጽሁፍ ቡድን የፈተና መረጃ……………..…………………………..……..…56
አባሪ 3. የኢስነ ጽሁፍ ቡድን የፈተና መረጃ...……………………………….……………..…..…56
አባሪ 4 በስነፅሁፍና በኢ-ስነፅሁፋዊ ፅሁፍ ለሚማሩ የቀረበ የድህረትምህርት ፈተና ምንባብ………………………………………………………………………………………57
አባሪ 5.የተማሪዎችን የማንበብ ተነሳሽነት ለመለካት የተዘጋጁ የፅሁፍ መጠይቆች...……..…..60
አባሪ 6 የቅድመና ድህረ መጠይቅ መረጃ…………………………………………………….61
አባሪ7. በስነፅሁፋዊና ኢ-ስነፅሁፋዊ ፅሁፎች ለሚማሩ ተማሪዎች ለማስተማሪያነት የተዘጋጀ ምንባብና መልመጃዎች……………………………………………………………………71

**የሠንጠረዥ ማውጫ**

ሠንጠረዥ4.1፡የስነ-ጽሁፋዊና ኢስነ-ጽሁፋዊ ቡድኖች የቅድመ ትምህርት የአንብቦ መረዳት ክሂል ፈተና ውጤት በነፃ ናሙና (independent sample t-test) ቲ-ቴስትትንተና........35

ሠንጠረዥ4.2 የስነ-ጽሁፋዊና ኢስነ-ጽሁፋዊ ቡድኖች የድህረ ትምህርት የአንብቦ መረዳት ክሂል ፈተና ውጤት በነፃ ናሙና (independent sample t-test) ቲ-ቴስት ትንተና........36

ሠንጠረዥ 4.3. የስነ ጽሁፍ ቡድን ቅድመና ድህረ ትምህርት የአንብቦ መረዳት ክሂል ፈተና ውጤት የነፃ ናሙና ቲ-ቴስት ትንተና........36

ሠንጠረዥ4.4. የኢስነ ጽሁፍ ቡድን ቅድመና ድህረ ትምህርት የአንብቦ መረዳት ክሂል ፈተና ውጤት የነፃ ናሙና ቲ-ቴስት ትንተና........37

ሠንጠረዥ4.5. የስነ ጽሁፍ ቡድን ቅድመና ድህረ ትምህርት የአንብቦ መረዳት ክሂል ፈተና ውጤት የዳግም ልኬት ቲ-ቴስት ትንተና........37

ሠንጠረዥ4.6. ኢስነ ጽሁፍ ቡድን ቅድመና ድህረ ትምህርት የአንብቦ መረዳት ክሂል ፈተና ውጤት የዳግም ልኬት ቲ-ቴስት ትንተና........38

ሠንጠረዥ4.7 ፡የፅሑፍ መጠይቅ የቅድመ የነፃ ናሙና ቲ-ቴስት ትንተና........40

ሠንጠረዥ4.8 ስነጽሁፍእና ኢስነጽሁፍ የፅሑፍ መጠይቅ የድህረ የነፃ ናሙና ቲ-ቴስት ትንተና........40

ሠንጠረዥ4.9 የሥነ ጽሁፍ  የነፃ ናሙና ቅድመና ድህረ መጠይቅ ትንተና........40

ሠንጠረዥ4.10 የኢሥነ ጽሁፍ ቅድመና ድህረ  የነፃ ናሙና ቅድመና ድህረ መጠይቅ ትንተና........41

ሠንጠረዥ4.11 የስነፅሑፍ የፅሑፍ መጠይቅ ቅድመና ድህረ የዳግም ልኬት ቲ-ቴስት ትንተና........41

ሠንጠረዥ4.12 የኢስነ ፅሁፍ የፅሑፍ መጠይቅ የዳግም ልኬት ቲ-ቴስት ትንተና........42

# አህፅሮተ ጥናት

የጥናቱ ዋና አላማ ስነፅሁፋዊና ኢስነስሁፋዊ ፅሁፎች የተማሪዎችን የአማርኛ ቋንቋ አንብቦ መረዳት ኪሂልን ከማሻሻል ረገድ ያላቸውን ሚና በንፅፅር መመርመር ነው፡፡ የጥናቱ ንድፍ ከፊል ሙከራዊ ነው፡፡ የጥናቱ ተሳታፊዎች በሆሮ ጉዱሩ ወለጋ ዞን ሻምቡ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ2015 ዓ.ም በ10ኛ የክፍል ትምህርታቸውን በመከታተል ላይ ከሚገኙት 915 ተማሪዎች መካከል በእድል ሰጪ ናሙና ዘዴ የተመረጡ 45 ወንድና 57 ሴት በድምሩ 102 ተማሪዎች ናቸው፡፡ ጥናቱም ሁለት ተጠኚ ቡድኖችን የያዘ የሁለት ቡድን ቅድመና ድህረ ልምምድ ፈተና ተግባራዊ ያደረገ ነዉ፡፡ ለተማሪዎች የቅድመ ትምህርት ፈተና ተሰጥቷል፡፡ ለስድስት ሳምንታት በአጥኚዉ ከተማሩ በኋላ የድህረ ትምህርት ፈተናዉ ከቅድመ ትምህርት ፈተናዉ በተመሳሳይ መለክ ተዘጋጅቶ እንዲፈተኑ ተደርጓል፡፡ ከዚያም ከተማሪዎች በቅድመ ትምህርትና ድህረ ትምህርት ፈተናዎችና በፅሁፍ መጠይቅ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡ መረጃዎችም መጠናዊ የምርምር ዘዴን በመጠቀም በነፃናሙናና ዳግም ልኬታ ቲ ቴስት ተተንትነዋል፡፡ በሁለቱም መረጃ መሰብሰቢያዎች አማካኝነት የተገኙ መረጃዎች በድህረ ትምህርት ፈተና አማካይ ውጤቶች የስነፅሁፍ 15.53 የኢስነፅሁፍ ቡድን 7.82 መካከል በነፃ ናሙና ቲ ቴስት ትንተናው መሰረት ጉልህ ልዩነት($p<0.05$) ታይቷል፡፡ ይህም በስነፅሁፋዊ ፅሁፍ የተማሩ ተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ክሂልን እንደሚያጎለብት አመላክቷል፡፡ በስነፅሁፊዊና ኢስነፅሁፋዊ ፅሁፍ የተማሩ ተማሪዎች የፅሁፍ መጠይቅ የድህረ ትምህርት አማካይ ውጤቶች መካከልም የስነጽሁፍ ቡድን ተማሪዎች 29.12 የኢስነፅሁፍ ተማሪዎች 23.29 መካከል በነፃናሙና ቲ ቴስት ትንተና ጉልህ የሆነ ልዩነት ($p<0.05$) የአሳየና የማንበብ ችሎታን የሚፈጥር ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በአንጻሩ ኢስነፅሁፋዊ ተማሪዎች የፅሁፍ መጠይቅ አማካይ ዉጤት እንዳመለከተዉ በተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ አንብቦ የመረዳት ክሂል ተነሳሽነት ላይ የተለየ ለውጥ የሚያመጣ አለመሆኑ በጥናቱ ተረጋግጧል፡፡ በአጠቃላይ በስነፅሁፋዊና ኢስነፅሁፋዊ ፅሁፎች የተማሩ ተማሪዎች የድህረትምህርት ፈተና በነፃናሙና ቲቴስት ስሌት መሰረት በስነፅሁፋዊ ፅሁፍ የተማሩት ተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ክሂል ችሎታ ጉልህ ልዮነት (p<s0.05) አሳይቷል፡፡ ምክንያት በተማሪዎች የማንበብ ችሎታ ላይ የታየው ለውጥ በስነ-ፅሁፋዊ ፅሁፍ የመጣ መሆኑን የጥናቱ ውጤት አመላክቷል፡፡

# ምዕራፍ አንድ
# 1. መግቢያ
## 1.1. የጥናቱ ዳራ

ቋንቋን ለማስተማር ስነጽሑፍን መሳሪያ ማድረግ የተጀመረው እ.ኤ.አ. በ1980ዎቹ ውስጥ ነበር፡፡ በሀገራችንም እነ ፍቅር እስከ መቃብር በ1960ዎቹ ብቅ ቢሉም ለማስተማሪያነት እንዲውሉ የተደረገው ግን ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ነበር፡፡ ይህ ደግሞ የቋንቋ ትምህርት ከተጀመረበት ጊዜ አንጻር ሲታይ እጅግ በጣም አጭር እድሜ ያለው መሆኑን ያረጋግጣል፡፡ ከተጠቀሰው ጊዜ ወዲህ ግን በባለሙያዎች በተደረገ ምሁራዊ ክርክር ምክንያት በተለይ እንግሊዝኛን በሁለተኛና በውጭ ቋንቋነት በማስተማር ተግባር ስነጽሑፍ ጉልህ አስተዋጽኦ እንዲኖረው ተደርጓል (Carter and Long, 1991)፡፡

ምንም እንኳን የመስኩ ባለሙያዎች ስነ-ጽሑፋዊ ስራዎችን ተጠቅሞ ቋንቋን ማስተማር አስፈላጊ መሆኑን ቢያትቱም በሌላ መልኩ ተቃውሞ የሚሰነዝሩም አልታጡም፡፡

Mckay (1986) በስነጽሑፍ አማካይነት ቋንቋን የማስተማር ሂደትን የሚቃወሙ ወገኖች የሚያቀርቧቸውን የመከራከሪያ ሀሳቦች በተመለከተ የሚከተለውን ብለዋል፡፡ ቋንቋን ስናስተምር ዋነኛ አላማችን ሰዋስዋዊ ህጎችን ማስተማር ነው፡፡ በአንጻሩ ስነ- ጽሑፋዊ ስራዎች ከዘወትራዊው የመግባቢያ ቋንቋ ያፈነገጠ አጠቃቀም ስለሚከተሉና ሰዋስዋዊ የመዋቅር ውስብስብነት ስለሚታይባቸው የሰዋስው ህጎችን ለማስተማር አያስችሉም፡፡ በተጨማሪም ስነጽሑፋዊ ጥናት ራሱን ችሎ ሊካሄድ የሚችል ተግባር በመሆኑ በቋንቋ ትምህርት ውስጥ የትምህርቱን አላማና ተግባር ለማሳካት ምንም አይነት አስተዋጽኦ አይኖረውም፡፡ እንዲሁም ስነጽሑፍ የማህበረሰቡ ባህላዊ ጉዳዮችን የሚያሳውቅ በመሆኑ ለተማሪዎች ከባድ ሊሆን ይችላል፡፡

ይሁን እንጂ ስነጽሑፍ ቋንቋን በማስተማር ሂደት ውስጥ ካለው ጉዳት ይልቅ ያለው ሚና ላቅ ያለ ነው፤ በማለት በርካታ የመስኩ ምሁራን ይከራከራሉ፡፡ ስነ ጽሑፍ ቋንቋን ለማስተማር ያለውን ፋይዳ በተመለከተም የተለያዩ ምሁራን የሰነዘሯቸውን የተለያዩ አስተያየቶች ከዚህ እንደሚከተለው እንመልከት፡፡

Hill (1986:7-9) በበኩላቸው ስነ ጽሑፍን በቋንቋ ትምህርት ውስጥ መጠቀም አስፈላጊ የሚሆንባቸውን ምክንያቶችን ሲገልፁ የቋንቋ ትምህርትን በእውነተኛ አውድ ለማስተማር ከተማሪዎች እለታዊ ህይወት ጋር አጣጥሞ በማቅረብ ተማሪዎች በፊት የሚያውቁትን እንዲያዳብሩና ቋንቋውንም የራሳቸው እንዲያደርጉት የበኩሉን ሚና ይጫወታል፡፡ ተማሪዎች በራሳቸው ጊዜ ቋንቋውን በአውድ በመገልገል ተግባቦት እንዲፈጥሩና ከክፍል ውጪም

እንዲጠቀሙበት በር ይከፍትላቸዋል። እንዲሁም የሚቀርቡ ልዩ ልዩ የስነጽሑፍ ስራዎች ተማሪዎችን ከተለያዩ ሰዎች ባህልና የህይወት ልምድ ጋር እንዲተዋወቁ ያደርጋቸዋል። ይህም ሂደት በተማሪዎች ላይ የመዝናናት ብሎም የማድነቅ ስሜትን ስለሚፈጥር ለትምህርቱ ያላቸው ጉጉት እንዲጨምር ያደርጋል።

እንደ ፈቃደ (1991፡12) አገላለጽ ለቋንቋ ትምህርት መዳበር ስነጽሑፍ ጉልህ ድርሻ አለው። በአንድ ስነጽሑፍ ውስጥ የሚገኙ ቃላት የተመረጡ ናቸው። በቃላቱ የተፈጠረው ሀሳብም በተለያዩ ዘይቤዎች፣ ፈሊጣዊና ምሳሌያዊ አነጋገሮች…ወዘተ የበለጸገ ሊሆን ይችላል። ሀሳቡ የተዋቀረባቸው ዐ.ነገሮች የተለያዩ አውዳዊ ፍቺዎችን የሚገልጹ ሆነው ሊመሰረቱ ይችላሉ። በመሆኑም የመልዕክቱ ፍቺ በቀላሉ አይገኝም፤ያመራምራል። የሀሳቡን ምንነት ለመረዳት ከብዙ አቅጣጫ እንዲመለከቱት ያስገድዳል። በዚህ ሂደት የሚደረገው ጥረትም በርካታ የቋንቋ መዋቅራዊ ህጎችንና ክሂሎችን ለመማር ይረዳል።

ከላይ ከተዘረዘሩት ጠቀሜታዎች በተጨማሪ በድሉ (1996፡ 8-9) ስነ ጽሑፋዊ ስራዎች የታላሚውን ቋንቋ ተናጋሪ ማህበረሰብ ባህል ለማወቅ አይነተኛ መሳሪያዎች በመሆናቸው በስርዓተ ትምህርት ውስጥ መካተት እንዳለባቸው በሚከለተው መልኩ ይገልፃሉ። ባህልን ከቤተሰብ መማር ይቻላል። ከቤተሰብ የማይገኙት ባህላዊ እሴቶች ደግሞ በማህበራዊ ተራክቦና በመደበኛ ትምህርት ይገኛሉ። ይሁን እንጂ አንዳንድ ጊዜ ከሶስቱ (ቤተሰብ፣ ህብረተሰብ፣ ትምህርት ቤት) በአንዱ ቦታ ክፍተት ይፈጠራል።… ስነ ጽሑፍ ይህንን ክፍተት ለመሙላት አይነተኛ መሳሪያ ነው። ተማሪዎች ከቤተሰብ ወይም ከህብረተሰብ የሚያጡትን ባህላዊ እሴት ከስነ ጽሑፍ ያገኙታል።

Nuttal (2000)፣ Grellt (1981)፣ Harmer (1991) ጨምረው እንዳብራሩት፣ ንባብ ፀሀፊው በፅሁፍ ውስጥ ያሰፈረውን ሀሳብ በተቻለ መጠን ለመረዳት፣ ለመለየት የሚደረግ ጥረት ነው። በመሆኑም አንባቢው በንባብ ሂደት የፅሁፉን መልዕክት ለመገንዘብና ከውስጡ አስፈላጊ መረጃዎችን ለይቶ ለማውጣት ጠቃሚ የንባብ ብልሃቶችን መጠቀም ያስፈልገዋል። ከሚነበበውም ቴክስት ፍሬ ሀሳብ ነቅሶ ማውጣት፣ የቴክስቱን ዝርዝር ሃሳብ መረዳት፣ የቴክስቱን መልዕክት መገንዘብ፣ የቴክስቱን አወቃቀርና አደረጃጀት መለየት ይጠበቅበታል።

Armbruister and Andorson (2002) እንዳመላከቱት፣ በመለስተኛና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚገኙ ተማሪዎች ማንበብን ለመማር አላማ እንዲጠቀሙ፣ አንብቦ የመረዳት ችሎታቸውን እንዲያሻሽሉ፣ አንብቦ መረዳት የሚያስችል ብልሃት መተግበር አለባቸው።

አብዛኛውን ጊዜ በንባብ ትምህርት የሚተገበሩት የአዳዲስ ቃላትን ትርጉም መለየትና የቴክስቱን ሀሳብ ወደ ተማሪዎች አፍ መፍቻ ቋንቋ መተርጎም ናቸው፡፡

Dole (1991) አገላለፅ በጥንታዊ አተያይ ጀማሪ አንባቢያን በቅደም ተከተል የተደራጁ የመረዳት ክሂሎችን ሊያዳብሩ ይገባል፡፡ እነዚህን ኪሂሎች ካዳበሩ ያነበቡትን ፅሁፍ ለመረዳት አይቸገሩም፡፡ በጥንታዊ የማንበብ ንድፈ ሃሰብ አንባቢዎች በምንባቡ ላይ የሰፈረውን መልዕክት ተቀባይ ብቻ ናቸው፡፡ የፅሁፍና የአናባቢ ግንኙነት ትርጉምን ያፈልቃል፡፡ Nunan(1991) በዚህ ጥንታዊ የማንበብ አተያይ ማንበብ ማለት በፅሁፍ የሰፈሩ ምልክቶችን በአዕምሮ ውስጥ ምስል እንዲፈጥሩ ማድረግና ወደ አቻ የንግግር ቋንቋ በመቀየር የፅሁፉን መልዕክት መረዳት ነው፡፡ ይህ ሂደትም ታች ላይ ሂደት እንደሚባል ይገልፃሉ፡፤ ይህ ማለት ትርጉም በተፃፈው ፅሁፍ ውስጥ የሚገኝ ሲሆን አንባቢው ፅሁፉን በማንበብ የሚያገኘው ነው፡፡ ከዚህ ላይ የማንበብ ሂደት ዋናው ጉዳይ የሚነበበው ነገር ሳይሆን አንባቢው ነው፡፡

Schema የማንበብ ንድፈ ሃሳብ ከአዕምሯዊ የማንበብ እይታ ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡ እንደ Rumelhart (1997) አገላለፅ Schema ማለት የመረዳት ዋናው መሰረት ሲሆን ይህም የስሜታዊ መረጃዎችን በመተንተን ሂደት አዕምሮ ውስጥ ካለ ነገር መረጃ በማግኘት ሂደት ዋና ዓላማንና ንዑስ ዓላማን በማደራጀት ሂደት ግብአትን በመመደብ ሂደት ላይ የሚያገለግል ነው፡፡ ስኬማችን የተሟላ ካልሆነና ከምናነበው ነገር ውስጥ ያገኘነውን መረጃ የማንረዳው ከሆነ ፅሁፉን በመተንተንና በመረዳት ላይ ችግር ያጋጥመናል፡፡ Guthrie et al (2008) የማንበብ ተነሳሽነት በማንበብ ሂደት ላይ ትልቅ ሚና የሚጫወት መሆኑን ይገልፃሉ፡፡ ተነሳሽነት ማለት በከፍተኛ ደረጃ አንድ ሰው የተወሰነ ተግባርን ለመተግበር የሚያነሳሳና ተፅእኖ የሚያደርግ ነው፡፡ ይኸውም ተማሪዎች ለማንበብ ከፍተኛ ተነሳሽነት ኑሯቸው በማንበብ ተግባር ላይ እንዲነሳሱ የሚያደርግ ነው፡፡ በሌላ በኩል ተማሪዎች ምንም ተነሳሽነት ከሌላቸው ሙሉ በሙሉ ማንበብ ይተዋሉ፡፡ Gamblrell and Marinalk (2005) የማንበብ ተነሳሽነት ግላዊ ምርጫን በመረዳት የንባብ ተግባራትን ልፈፅም ወይስ አልፈፅም ማለት ነው፡፡ ይህም ማለት የማንበብ ተነሳሽነትን ከፍ ለማድረግ አዕምሮን ዝግጁ ማድረግ፣ ፍቃደኝነትንና አመለካከትን (ግንዛቤን) በአንድ አካል በማንበብ ተግባር ለይ ተነሳሽነት መፍጠር ማለት ነው፡፡

እነዚህ ከላይ የቀረቡትን የምሁራን ሀሳቦች መነሻ በማድረግ የዚህ ጥናት ትኩረት ስነፅሁፋዊና ኢ-ስነፅሁፋዊ ፅሁፎች የአማርኛ ቋንቋ የአንብቦ መረዳት ክሂልን ከማሻሻል ረገድ ምን አይነት ሚና ሊኖራቸው እንደሚችሉ በሙከራ ማረጋገጥ ይሆናል፡፡

## 1.2 የጥናቱ አነሳሽ ችግር

Grham (1987)፣ Nilson (1984) እና Hiland (1990) ተማሪዎች በትምህርት አለም የተሻለ ውጤት አስመዝግበው ለመቀጠል ከሚያስችሏቸው ክሂሎች ውስጥ አንዱ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ስለሆነ፤ ክሂሉ ከሌሎቹ ችሎታዎች ቅድሚያ ይሰጠዋል፡፡ በእርግጥም በትምህርት አለም ያሉ ሰዎች በየእለቱ ከሚነበቡ በርካታ ነገሮች ጋር ይገናኛሉ፡፡ ቢሆንም የአንብቦ የመረዳት ችሎታቸው በአግባቡ ከጽሁፎች ተገቢውን እውቀት ለመቅሰም አያስችልም፡፡ ምክንያቱም በአንድ ጊዜ ንባብ ብቻ ተፈላጊውን መረጃ በመረዳት መያዝ ስለማያስችል ነዉ፡፡ በትምህርት ቤትም ይሁን ከትምህርት ቤት ውጪ ትምህርት ከሚገኝባቸው ምንጮች አንዱ ተማሪዎች ባላቸው የማንበብና አንብቦ የመረዳት ችሎታ መጠን ነው፡፡ እውቀታቸውም የሚጎለብተው በጽሁፍ በሚቀረበዉ ሃሳብ አማካኝነት ነው፡፡ የትምህርቱም ዋና ግብ ተማሪዎች ከንባብ በቂ የሆነ መረጃ እንዲያገኙ መርዳት ነው፡፡ ለትምህርት የሚዘጋጁ መጻሐፍትም አላማ በቂ እና ወቅታዊ እውቀትን ለተማሪዎች ማስገንዘብ ነው፡፡

ይሁንና Conely (1992)፣ Dymock (2007) እንደገለፁት፣ ዘወትር እንደሚታየው ተማሪዎች ከንባብ ጋር ሳይተዋወቁ ጥሩ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ሳይኖራቸው የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ያጠናቅቃሉ፡፡ በመሆኑም በርካታ ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታቸው ደካማ ነው፡፡ ለምሳሌ ተማሪዎች ከምንባብ የወጡ ጥያቄዎችን ማለትም ፍሬ ሀሳቦችን፣ ዝርዝር መረጃዎችንና ከምንባቡ የወጡ ቃላትን አገባባዊ ፍች፣ በምንባቡ መሰረት ትንበያ ማስቀመጥ የብዙ ተማሪዎች ድክመት ነው፡፡ ሌሎች ደግሞ የተሰጡትን ምንባባዊ ተግባራት አትኩሮት ሰጥተው ከመስራት ከመከታተል ይልቅ የመሰላቸት ስሜት ሲያሳዩ ይስተዋላል፡፡

በዚህ ርዕስ ጉዳይ ላይ ማለትም በስነፅሁፋዊና በኢ-ስነፅሁፋዊ ፅሁፎች የአማርኛ ቋንቋ የአንብቦ መረዳት ችሎታን ከማሻሻል አንጻር በተማሪዎች ላይ ያላቸውን ፋይዳ ለማየት የተሰራ የሀገር ውስጥ ጥናት ከተቃኙት መረጃዎች ባይገኝም ስነፅሁፋዊ ፅሁፍን በመጠቀም የማንበብ ክሂልን በማጐልበት ረገድ ያለውን ሚና በተመለከተ በተለያዩ የውጪ ሀገር ተመራማሪዎች ጥናቶች ተካሂደዋል፡፡ በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ላይ Reza Mokhtari በ30 ኢራናዊያን በኢስላሚክ አዛድ የኒቨርስቲ በወንዶችና በሴቶች ከ19 እስከ 30 ዓመት የሆኑ ተማሪዎች ላይ ባደረጉት ጥናት በአለው ነባራዊ ሁኔታ በስነፅሁፋዊና በኢ-ስነፅሁፋዊ ይዘት የሚማሩ ተማሪዎች የማንበብ ችሎታ ልዩነት እንዳላቸው ለማየት ተችሏል፡፡ ይሄውም በቋንቋ ብቃታቸው በኦክስፎርድ ፕሌስመንት ቴስት ፈተና ተመዝነዋል፡፡ ለዚህም ሁለት ዝግ ፈተናዎች አንደኛው በስነፅሁፍ

ሌላኛው በኢ-ስነፅሁፍ ፈተና በመፈተን የቲ-ቴስት ውጤቱም እንደሚያመለክተው በስነፅሁፍ የሚማሩት በማንበብ ክሂላቸው ላይ አወንታዊ አስተዋፅዖ እንዳለው አመልክተዋል፡፡

የ Reza Mokhtari ጥናት ከዚህ ጥናት ጋር የሚመሳሰለው ከስነፅሁፋዊ እና ከኢስነፅሁፋዊ ፅሁፎች የተማሪዎችን የማንበብ ክሂል ለማጎልት የተሻለዉ የትኛዉ እንደሆ በንጽጽር የሚመረምሩ መሆናቸዉና መጠናዊ የአጠናን ስልትን መጠቀማቸዉ ሲሆን የሚለያዩት ደግሞ Reza Mokhtari ከስነ-ፅሁፋዊ እና ከኢስነ-ፅሁፋዊ ፅሁፎች የተማሪዎችን የእንግሊዘኛ ቋንቋ ንባብን ለማስተማር የተሻለዉ የትኛዉ እንደሆነ መፈተሽ ዋነኛ ትኩረቱ ሲሆን ይህ ጥናት ደግሞ ከስነ-ፅሁፋዊ እና ከኢስነ-ፅሁፋዊ ፅሁፎች የተማሪዎችን የአማርኛ ቋንቋ የአንብቦ መረዳት ክሂል ለማሻሻል የተሻለው የቱ እንደሆነ መፈተሽ ዋነኛ ትኩረቱ ነው፡፡ በተጨማሪም ይህ ጥናት በ10ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ የሚሰራ ሲሆን የReza Mokhtari ጥናት ግን በዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ላይ የተሰራ ነው፡፡ ከዚህም በመነሳት በስነፅፋዊና ኢ-ስነፅሁፋዊ ፅሁፎች የአማርኛ ቋንቋ የአንብቦ መረዳት ክሂልን ማስተማር በተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ክሂል መዳበር ላይ ያላቸውን ሚና ለማነፃፀር በዚህ ጉዳይ ላይ አጥኝው ጥናት ለማድረግ ተነሳስቷል፡፡

ሁለተኛው ምክንያት በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በአማርኛ ቋንቋ መማር ማስተማር ሂደት ባለው ተሞክሮ አጥኚው በጥናቱ ለማየት የፈለገው በመማር ማስተማሩ ሂደት የአንብቦ መረዳት ክሂልን ለማዳበር ከተዘጋጁት አስር ምዕራፎች መካከል ስነፅሁፋዊ ዘርፍ ያላቸው ምንባቦች ሶስት ናቸው፡፡ ይህ ደግሞ የሚቀርቡ ምንባቦች በአብዛኛው ኢ-ስነፅሁፋዊ መሆናቸውን ያሳያል፡፡ ከዚህም በመነሳት አጥኚው ስነፅሁፋዊ ፅሁፎች በይበልጥ ቢቀርቡ በተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ክሂል ላይ ለውጥ ያመጣ ይሆን? የሚለውን ለመመርመር አጥኚው ወደዚህ ርዕስ ተስቧል፡፡

ለዚህ ጥናት እንደ ሶስተኛ አነሳሽ ምክንያት ሊጠቀስ የሚችለው አጥኚው ‹‹ሥነ-ፅሁፍ አማርኛ ቋንቋን በማስተማር ሂደት ውስጥ›› የሚለውን ኮርስ በሚማርበት ወቅት ስነ-ፅሁፋዊነት ያላቸው ምንባቦችን ተጠቅሞ ማስተማር በተማሪዎች የመማር ሂደት ላይ ለውጥ ሊያመጡ ይችላሉ የሚለውን ሃሳብ በጥናት ለማረጋገጥ መነሻ ሆኖታል፡፡ ይህም በመሆኑ አጥኚውን ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ የአንብቦ መረዳት ክሂል ክፍለ ጊዜ ከላይ የተዘረዘሩት የተማሪዎች ችግር ሊመጣ የቻለው በአብዛኛው ኢ-ስነፅሁፋዊ በሆነ ፅሁፍ የአማርኛ ቋንቋ የአንብቦ መረዳት ክሂል መማራቸው ሊሆን ይችላል የሚል መላምት አስቀምጧል፡፡ ስለሆነም በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ሙከራዊ ጥናት ለማካሄድ ተነሳስቷል፡፡

ስለዚህ በስነፅሁፋዊና በኢ-ስነፅሁፋዊ ፅሁፎች የአማርኛ ቋንቋን የአንብቦ መረዳት ክሂልን ከማሻሻል ረገድ ያላቸውን ሚና መፈተሽ የዚህ ጥናት አብይ ትኩረት ነው፡፡

## 1.3. የጥናቱ መሰረታዊ ጥያቄዎች

ይህ ጥናት ተከታዮቹን አንኳር ጥያቄዎች መልሷል፡፡

1. ከስነፅሁፋዊ እና ኢስነፅሁፋዊ ፅሁፎች በተማሪዎች አንብቦ መረዳት ችሎታ ላይ የበለጠ አስተዋፅኦ ያለው የትኛው ነው?
2. ከስነፅሁፋዊና ኢ-ስነፅሁፋዊ ፅሁፎች የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ክሂል ለማጎልበት እና ለማስተማር የበለጠ ልዩነት ያሳየው የትኛው ነው?

## 1.4. የጥናቱ ዓላማ

የዚህ ጥናት ዋነኛ አላማ ከስነ-ፅሁፋዊና ኢ-ስነፅሁፋዊ ፅሁፎች የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ክሂል ለማጎልበት የበለጠ ፋይዳ ያለው የቱ እንደሆነ መመርመር ነው፡፡ ለዚህ ተግባር ማስፈፀሚያ የሚያገለግሉ ዝርዝር አላማዎች ደግሞ ተከታዮቹ ናቸው፡፡

1. ከስነፅሁፋዊና ከኢስነፅሁፋዊ ፅሁፎች በተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታ ላይ የበለጠ ፋይዳ ያለውን መመርመር፡፡
2. ከስነፅሁፋዊና ኢ-ስነፅሁፋዊ ፅሁፎች የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ክሂል ለማጎልበት የበለጠ ልዩነት ያሳውን መለየት፡፡

## 1.5. የጥናቱ ጠቀሜታ

ከስነጽሑፋዊና ኢ-ስነፅሁፍ ፅሁፎች በአማርኛ ቋንቋ የአንብቦ መረዳት ክሂልን ከማጎልበት ረገድ ያላቸውን ሚና ማነፃፀር ስለሆነ ይህ ጥናት ተከታዮቹ ጠቀሜታዎች አሉት፡፡

- ለተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታቸውን ለማጎልበት ያግዛል፡፡
- ለመምህራን ከስነፅሁፋዊ ፅሁፎች እና ከኢስነፅሁፋዊ ፅሁፎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ክሂል ለማዳበር የትኛው የበለጠ አስተዋፅኦ እንዳለው በመገንዘብ የተሸለውን እንዲተገብሩ መረጃ ይሰጣል፡፡
- ለመምህራን ስነፅሁፋዊና ኢ-ስነፅሁፋዊ ፅሁፎች ከአንብቦ መረዳት ክሂል አንፃር ሚናቸውን ያሳያል፡፡
- ስነ-ጽሑፍ ኢ-ስነፅሁፋዊ ፅሁፎችን ተጠቅሞ በቋንቋ ትምህርት ዙሪያ ወደ ፊት ጥናት ማድረግ ለሚፈልጉ አጥኝዎች ለመነሻ የሚሆኑ ሀሳቦችን ያጋራል፡፡

## 1.6. የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት የሚካሄደው በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በሆሮ ጉዱሩ ወለጋ ዞን በሻንቡ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ2015 ዓ.ም በሚማሩ የአስረኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ ብቻ

ይሆናል፡፡ የጥናቱ ትኩረትም ከስነፅሁፋዊ ፅሁፎች አጭር ልቦለድና ግጥምን ከኢ-ስነፅሁፋዊ ፅሁፎች ጋዜጦች፣ መፅሄቶችና የህይወት ታሪኮች ላይ ብቻ የተመሰረተ ሲሆን ከክሂሎች ደግሞ አንብቦ መረዳትን ብቻ ይመለከታል፡፡ ሌሎችን ትምህርት ቤቶች ፤ የክፍል ደረጃዎች፤የስነ-ፅሁፍ ዘርፎችና ኢ-ስነፅሁፋዊ ስራዎችን አጥኚዉ ካለበት የጊዜ፤ የገንዘብና የጉልበት ዉስንነት አንፃር አይመለከትም፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

# 2. የተዛማጅ ድርሳናት ክለሳ

## 2.1. የአንብቦ መረዳት ምንነት

አንብቦ መረዳት ሲባል በጽሁፍ ዉስጥ ሊተላለፍ የተፈለገዉን መልእክት በተቻለ መጠን መገንዘብ ነው፡፡ በሌላ አባባል የሚፈለገዉን መረጃ ከአንድ ጽሁፍ ዉስጥ ፈልቅቆ ማዉጣትን የሚጠይቅ ነው፡፡ አንባቢውበተገቢው ፍጥነት የሚፈልገውን መረጃ የሚያወጣበት የማይፈለገውንም የሚለይበት ጥልቅ ግንዛቤ የሚመለከትበት ዘዴ ነው (Wiliams,1990)፡፡ እንደ Greenwood (1981) አንብቦ መረዳት በአንድ ጽሁፍ ዉስጥ ሊተላለፍ የፈለገዉን መልእክት መገንዘብ ነው፡፡ በእርግጥ አንብቦ የመረዳት ደረጃ ሊለያይ ይችላል፡፡ ይህም ከሚነበበዉ ነገር፣ ከሚነብብበት ዓላማ፣ ከአነባበብ ዘዴዉ መለያየት ሊከሰት ይችላል (Nuttal, 2000)፡፡ Simith(1985) እንደሚሉት ደግሞ አንብቦ መረዳት አንባቢዉ ይዞት ለሚነሳዉ ጥያቄ መልስ ማግኘት ማለት ነዉ፡፡ አንባቢ ለጠየቀዉ ጥያቄ መልስ አገኘ ማለት በአንባቢዉና በጸሀፊዉ መካከል በአንብቦ መረዳት ተግባቦት መኖሩን ያሳያል፡፡ በአጭሩ አንብቦ መረዳት ማለት ከአንድ ምንባብ ዉስጥ የሚፈለገዉን መረጃ ለይቶ ማዉጣት መቻል ነዉ፡፡

## 2.2 የአንብቦ መረዳት ንድፈ ሀሳብ

Gaffney & Anderson (2000፣21) ከ1965 እስከ 1998 ድረስ በማንበብ ዙሪያ ተሰርተው በአራት ጆርናሎች የታተሙ ምርምሮችን በመቃኘት ውጤታቸውንና የተከተሉትን ንድፈሀሳብ አሳይተዋል፡፡ እንደ Gaffney& Anderson (2000) ማብራሪያ የምርምሮቹ ንድፈ ሀሳባዊ መሰረት ከባህሪያውያን ወደ አዕምሯውያን ከአዕምሯውያን ወደ ማህበረ-ባህላዊያን ተለዋውጧል፡፡ በ1960ቹ አካባቢ የባህሪያውያን ንድፈሀሳብ መስፋፋቱ በማንበብ ዙሪያ በሚሰሩ ምርምሮች የታዋቂው BF Skinner ግኝት የሆኑት ማበረታታት ፣ ማስለመድና የባህርይ ትንተና የሚሉት ጽንሰሀሳቦች በሰፊው አገልግሎት እንዲሰጡ አድርጓል (Gaffney & Anderson, 2000፣12)::

እንደባህርያውያን ንድፈሀሳብ እይታ ማንበብ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ ወይም ከታች ወደ ላይ እያደገ የሚሄድ ክሂል ነው፡፡ መማርም አንድ ተማሪ ለቀረበለት ማነቃቂያ ምላሽ የሚሰጥበት ሂደት እንደሆነ በዚህ ንድፈሀሳብ ይታመንበታል፡፡ በአንብቦመረዳት ሂደት ውስጥ እንደማነቃቂያ የሚቆጠሩት የታተሙ ጽሁፎች ናቸው፡፡

እንደ ባህርያውያን (ቀዳማዊ የማንበብ ንድፈሀሳብ) እይታ የማንበብ ሂደት ከታች ወደ ላይ እየዳበረ የሚሄድ ነው፡፡ ማለትም ማንበብ የሚጀምረው ፊደላትን ከመለየት ሲሆን ወደ

አጠቃላዩ ትርጉም የማውጣት ሂደት እያደገ ይሄዳል። የዚህ ንድፈ ሀሳብ አቀንቃኝ የሆኑት ተመራማሪዎች እንደሚያስረዱት የማንበብ እድገት በሚከተለው ቅደም ተከተል መሰረት እየዳበረ የሚሄድ ነው።

የማስተማር መመሪያቸው ለስነድምጽ ቅድሚያ ይሰጣል። በመጀመሪያ ድምጹ ይለያል። በመቀጠል ያንን ድምጽ የሚወክለው ፊደል ከታወቀ በኂላ ራሳቸውን ችለው መጽሀፍ ማንበብ ይጀምራሉ ማለት ነው። በዚህ ንድፈ ሀሳብ ተማሪዎች ፍዝ እንዲሆኑ ይጠበቃል። በሌላ አባባል የተማሪዎች ተሳትፎ ዝቅተኛ ነው ። አብዛኛውን ሚና የሚጫዎተው አስተማሪው ነው። መረጃ አቀባዩ መምህሩ ነው። ተማሪዎች ደግሞ ተቀባዮች ናቸው። እንድሪስ (2009) የባህርያውያን ንድፈ ሀሳብን እንዲህ ይገልጹታል።

የባህርያዊያን የማስተማር ንድፍ በአወንታ ወይም በአሉታ መልሶም ገባ የሚጠናከር አነቃቂ ተግባርን በመፍጠር ላይ ያነጣጠረ ነው። ከፍተኛ እርከን ያላቸው የሀሳብ ተዛምዶዎች ወይም ቅበላዎች ጠቃሚ ተደርገውም አይታዩም። በአጭሩ የባህርያዊያን መማር ንድፈሃሳብ በአዕምሯዊ ክዋኔ ትስስሮች ጥናት ላይ የተመሰረተ፣መማር እንደባህርይ ለውጥ የሚበየንበት፣ማሰብ ከቅጽበታዊ የቀስቃሽ-ምላሽ ጥምረት የሚመነጭበት፣ማሰብን ለመማር ትኩረት የማይሰጥበት፣ የቀስቃሽ-ምላሽ መማር ሞዴልን የሚከተል ነው። የንድፈሃሳቡ አላባዎችም ሁኔታዎችን መልመድ፣ምላሽ መስጠት፣መግራት፣ ማጠናከርና ቀድሞ የታቀደ ጥብቅ አሰራርን መከተል ናቸው።

በሁለተኛ ደረጃ የሚጠቀሰው ንድፈ ሀሳብ በ1970ቹ የተስፋፋው የአዕምሯውያን ንድፈ ሀሳብ ነው። ይህ ንድፈ ሀሳብ ለተማሪው ስኬማ ሚናና ለታተመው ጽሁፍ ጠቀሜታ እኩል ትኩረት የሚሰጥ ንድፈ ሀሳብ ነው። የስኬማ ንድፈ ሀሳብ ተብሎም ይጠራል። ስኬማ ማለት አዕምሯዊ ግንባታ ማለት ሲሆን መረጃ በረጅም ጊዜ ትውስታ እንዲደራጅ የሚፈቅድ ነው (Huang, 2009) ፣ Pearson (2009)። የስኬማ ንድፈ ሀሳብን ሲያብራሩት በ1970ዎቹ ተቀባይነት ያገኘው ስኬማ በማንበብ ሂደት ቋንቋና መረጃን ከጽሑፍ ለይቶ ለማውጣት የሚያስችልና አንባቢን እንደ ትርጉም መስራች የሚያይ ንድፈ ሀሳብ ነው።

እንድሪስ (2009፣ 26) በስኬማ ንድፈሃሳብ መሰረት እውቀት በሚከማችበት መንገድ አምሳያ የማስተማር መማር ተግባራት አዲሱን ከነባሩ እውቀት ጋር ማስተሳሰር አለባቸው፤ትስስር መፍጠሩም አዲሱን መረጃ በቀላሉ ዳግም ማስታወስ እንደሚያስችል ይታሰባል። ይህ ተዛምዶም መረጃን በስኬማ ላይ በመጨመር፣ ዳግም በማዋቀር የሚፈጠር ነው። ተዛምዶዎቹ በትስስር

የሚፈጠሩ ሲሆኑ እነዚያ ትስስሮች መስመሮችን ሳይጠብቅ እንደተፈጠረ የማስታወሻ አሰፋፈር ተደርገው ይታሰባሉ፡፡ በስኬማ ንድፈሃሳብ አቀንቃኞች የሚታቀዱ ተግባራት የተማሪዎቹን ቀደምት እውቀት ማስታወስንና መረጃውን ከሚያውቁት ሀሳብ ጋር ማዛመድን የሚያካትቱ ናቸው፡፡

እንደስኬማ ንድፈሀሳብ ማንኛውም ጽሁፍ በራሱ ትርጉም የለውም፡፡ ጽሁፉ ትርጉም የሚኖረው አንባቢው የቀደመ እውቀቱን ተጠቅሞ የቀረበውን ጽሁፍ መረዳት ሲችል ነው (Huang,2009)፡፡ እንደHuang (2009) አገላለጽበ ስኬታማ ንባብ የሚባለው ከዚህ በፊት በአዕምሮ ውስጥ ተደራጅቶ የተቀመጠውና ከእይታ ውጭ የሆነው እውቀት በጽሁፍ ታትሞ ከሰፈረውና በአይን ከሚታየው መረጃ ጋር በትክክል መቀናጀት ሲችል ነው፡፡ Sheridan (1981) በተጨማሪ እንደሚያብራሩት ተማሪዎች በአካባቢያቸው ስለሚታየው እውነታና የህይወት ዑደት ያላቸውን ነባር ዕውቀት በላይታችና በታችላይ የንባብ ሂደት የመጠቀም ሁኔታ ስኬማ ይባላል፡፡ እንደስኬማ አገላለጽ ፅሁፉ ብቻውን በራሱ ትርጉም የለውም፡፡ ትርጉም የሚኖረው አንባቢው የራሱን ልምድ፣ ስሜትና የባህል እውቀት በመጠቀም መረዳት ሲችል ነው፡፡ በዚህ መልኩ ከተረዳ ደግሞ ስኬማ ይባላል፡፡ እንደስኬማ ንድፈሀሳብ ጽሁፍን የመረዳት ሂደት በጽሁፉና በአንባቢው ነባር እውቀት መካከል በሚደረግ ንቁ ተሳትፎ የሚፈጠር ነው፡፡

በማንበብ ሂደት በጥቅም ላይ የሚውሉ የስኬማ አይነቶች የይዘት ስኬማ፣ መደበኛ ስኬማና ስነልሳናዊ ስኬማ ናቸው (Khalaji & Vafaeeseresht, 2012)፡፡ የመጀመሪያው የይዘት የሚባለው ስኬማ የአንባቢው ዳራ ወይም ለአለም ያለው ነባር እውቀት ሲሆን አዲሱን እውቀት ለማነጻጸር እንደመሰረት የሚያገለግል ነው፡፡ በሌላ አገላለጽ አንባቢዎች በጽሁፉ ያለውን ክስተትና ድርጊት በህይወታቸው ካጋጠማቸው ተመሳሳይ ክስተትና ድርጊት ጋር እንዲሁም ከራሳቸው ባህል ጋር እያነጻጸሩ የሚገነዘቡበት ነው፡፡

መደበኛ የሚባለው ሁለተኛው የስኬማ አይነት በአብዛኛው ዘውግ-ተኮር ስኬማ እየተባለ ይጠራል፡፡ ይህ ስኬማ አንባቢዎች የተጻፉ ጽሁፎችን ቅርጽና መዋቅራዊ ባህርይ በማየት ምን ሊገጥማቸው እንደሚችል አስቀድመው የሚገምቱበት ስኬማ ነው፡፡ ለምሳሌ መጽሄት ከልቦለድ የተለየ ስለሆነ ልቦለድ ለማንበብ የተዘጋጀ ሰው ምን ሊገጥመው እንደሚችል የሚገምትበት ነው፡፡ በአጠቃላይ አንባቢዎች ቅርጽን በማየት በጽሁፉ ሊያጋጥማቸው ስለሚችለው መዋቅር፣ ቃላት፣ ሰዋሰውና የጽሁፉ የመደበኛነት ደረጃ አስቀድመው የሚዘጋጁበት ስኬማ መደበኛ ስኬማ ነው፡፡ የመጨረሻው የስኬማ አይነት ስነልሳናዊ ወይም የቋንቋ ስኬማ ሲሆን ቃላትን ለማገናዘብ

የሚያስፈልጉ ስነልሳናዊ መገለጫዎችንና እነዛ ቃላት አረፍተነገር የሚመሰርቱበትን መዋቅር የሚያካትት የስኬማ አይነት ነው (Huang, 2009)፡፡

ስኬማ ለአንባቢ የሚሰጠው ጠቀሜታ በርካታ ነው፡፡ ከነሱም የመጀመሪያው ዋናና ዝርዝር አላማዎችን ለአንባቢ በማሳዎቅ የአንባቢውን የትኩረት አቅጣጫ ለመወሰን ይረዳል፡፡ በመቀጠል በጽሁፉ ውስጥ ያልተሟሉ መረጃዎች ካሉ የቀደመ እውቀትን ተጠቅሞ ክፍተቱ እንዲሞላ ያግዛል፡፡ እንዲሁም ተገቢውን ተገቢ ካልሆነው ለይቶ ለማውጣት ያገለግላል፡፡ በመጨረሻም ነገሮችን በመገመት ለመረዳት ያገለግላል (Pearson 2009)፡፡
ቃላት፣ አረፍተነገሮችና የጽሁፍ ትርጉም አንባቢው ከማንበቡ በፊት ባለው ልምድና የቀደመ-እውቀት ምክንያት ተጽዕኖ ስለሚደርስባቸው እንደሁኔታው ይለዋወጣሉ፡፡ የንባብ ሂደቱም የሚከተለውን አይነት አካሄድ ይኖረዋል፡፡
ሶስተኛው የማንበብ ንድፈሀሳብ የማህበረባህላዊ ቅድመ-ግንባታውያን ነው፡፡ ከ1980ቹ መካከለኛው ዘመን ጀምሮ የማህበራዊ ቅድመ-ግንባታውያን ንድፈሀሳብ እየተስፋፋ መምጣት የአዕምሯውያን ንድፈሀሳብ እየተዳከመ እንዲሄድ አድርጎታል፡፡ በዚህ ንደፈሀሳብ በዋናነት የሚጠቀሰው የሩሲያዊው የስነልቦና ተመራማሪ Vygotsky የማህበረ-ባህላዊ እድገት ንድፈሀሳብ (Socio- cultural Development Theory) ነው፡፡ የማንበብ ትምህርት የመማር ሂደት በማህበራዊ ግንዛቤ ላይ የተመሠረተ ነው የሚለው አመለካከት በሰፊው የተንሰራፋበት ንድፈሀሳብ ነው፡፡

Doolittleeal (2006) እንደሚያብራሩት በዚህ ንድፈ ሀሳብ መሰረት እውቀትና ትርጉም የሚገኘው ከማህበረሰቡ ንቁተሳትፎ ነው፡፡ የተገኙት እውቀቶች አገልግሎታቸውም ለማህበረሰቡ ነው፡፡ በሌላ አገላለጽ የእውቀት ምንጩም ተጠቃሚውም ማህበረሰብ ነው፡፡

ከ1980- 90ቹ የማህበራዊ ቅድመ-ግንባታ ንድፈሀሳብ መስፋፋት አይነታዊ የምርምር ዘዴ ከመጠናዊና ከሙከራዊ የበለጠ እንዲሰራበት አድርጓል (Gaffney & Anderson,2000):: ማንበብን ከቃላት፣ ከቋንቋና ጽሁፍ ጋር አያይዞ መስራቱ እየቀነሰ ከማህበረሰብ፣ ከባህል፣ ከተነሳሽነትና ከፍላጎት ጋር አያይዞ ማጥናት እየጨመረ የሄደበት ጊዜ እንደነበር Gaffney & Anderson (2000) ያስረዳሉ፡፡

በ2011 በተዘጋጀው የማንበብ ምርምር መጽሀፍ አርታዒዎቹ Kamil et al. (2011) በቅኝታቸው እንደገለጹት ባለንበት ዘመን የምርምሮቹ የትኩረት አቅጣጫ በጣም ጠንካራና አድካሚ የሆኑ የምርምር ዘዴዎችን ማዘጋጀት እንዲሁም በተለያዩ አውዶች፣ በተለያዩ ሰዎችና

በልዩ ልዩ ልምምዶች የማንበብን ውጤታማነት መፈተሽ ነው፡፡ Kamil et al. (2011) ያነሱት በቀደሙት ጊዜያት ያልታየው ሌላው ጠቃሚ ነጥብ በማንበብ ሂደትና እድገት መካከል ስላለው ልዩነት ነው፡፡ ማንበብ ፊደላቱን አውቆ በትክክል ማለት መቻሉ ላይ ብቻ የሚቆም ሳይሆን በህይወት ዘመን ሁሉ ከሚያጋጥሙ የተለያዩ የጽሁፍ አይነቶች ጋር እራስን እያግባቡ እውቀትን የማዳበር የማያቋርጥ ሂደት ነው፡፡

በማንበብ ሂደት ዋናው መሰረታዊ ነገር መረዳት መቻል የሚለው ጽንሰሀሳብ እንደሆነ Paris & Hamilton (2009) ያስረዳሉ፡፡ ማለትም ካለመረዳት ማንበብ የቋንቋውን ድምጾች የማነብነብ ሂደት ብቻ ይሆናል፡፡ አንብቦመረዳት በተለያየ መንገድ ሲበየን ይስተዋላል፡፡ ቀደምት ብያኔዎች ዋና ትኩረታቸው በማሰብና ምክንያት በመስጠት ላይ ነው ምሳሌበParis & Hamilton (2009) የተጠቀሱት Thorndike:: ነገርግን የቅርብ ጊዜ ብያኔዎች ትኩረታቸው በአንብቦ መረዳት ተራክቧዊና ግንባታዊ ሂደት ላይ ነው (Paris & Hamilton, 2009)፡፡

የምርምርና የእድገት ሪፖርት መረዳትን ከተጻፉ ጽሁፎች ጋር በሚደረግ ተራክቦና ተሳትፎ ትርጉም የማውጣትና የመገንባት ሂደት በሚል ይተረጉመዋል፡፡ በተመሳሳይ አንብቦመረዳትን የተጻፉ ጽሁፎች ለመገንዘብ የሚደረግ ንቁና ውስብስብ ሂደት፣ ትርጉምን መተንተንና ማዳበር እና እንደየ ጽሁፉ አይነት፣ አላማና ሁኔታ ተገቢትርጉም የመስጠት ሂደት እንደሆነ Paris & Hamilton (2009) ያስረዳሉ፡፡

### 2.3 የአንብቦ መረዳት ሞዴሎች

በ1960ቹና 1970ቹ የነበረው የአንብቦ መረዳት ሞዴል አንብቦ መረዳትን ከመጻህፍት፣ ከታሪኮችና ጆርናሎች መረጃ የመሰብሰብና የማቀናጀት ሂደት በሚል ይገልጹታል (Fox & Alexander, 2009)፡፡ በዚህ ዘመን ከአንባቢው የሚጠበቀው ግብዓት ከጽሁፉ ውስጥ ተገቢውን መልእክት ማውጣት ስለነበር በጊዜው ተስፋፍቶ አገልግሎት ይሰጥ የነበረው ሞዴል የማውጣትና የመሰብሰብ ሞዴል (Extraction-Assembly Model) ነበር (Fox & Alexander, 2009)፡፡

በ1980ቹ አካባቢ አንብቦ መረዳት እይታው ባለሁለት አቅጣጫ እንደሆነ Fox & Alexander (2009) ያስረዳሉ፡፡ ማለትም ጽሁፉን ለመረዳት የአንባቢው ቅድመ እውቀትና አውዱ ወሳኝ ናቸው፡፡ በዚህ ወቅት የነበረው የማንበብ ሂደት ሞዴል የመገንባትና የማዋሃድ ሞዴል (Constructive-Integrative Model) በጽሁፉ መልዕክት ላይ እያንዳንዱ ሰው የራሱን ግለሰባዊ መልስ እንዲሰጥ በመፍቀዱ ጽሁፉ ከአንድ በላይ ትርጉም ይኖረዋል (Fox & Alexander, 2009)፡፡

በ21ኛው ክፍለ ዘመን የአንብቦ መረዳት ትኩረት በተለያዩ ባህላዊና አማራጫዊ አውዶች ላይ ማጠንጠን ጀመረ (Fox & Alexander,2009):: ምክንያቱም ከለውጡ መረዳት እንደሚቻለው ጽሁፍ በማህበረ ባህላዊ አውድና ማህበራዊ ተራክቦ መዳበሩንና አንብቦ መረዳት ውጤታማ የሚሆነው በተጠቀሱት ጉዳዮች ዙሪያ ማጠንጠን ሲችል ነው፡፡ እንደ Fox & Alexander (2009) ቅኝት አንብቦ መረዳት በመረጃ መረብ የሚገኙ መጽሀፎችን መጠቀም፣ ኮሚፒውተር በመጠቀም ዋቢዎችን ማጣቀስ፣ ዋቢዎችን በተገቢው ማደራጀት፣ በመረጃ መረብ የሚገኙ ጋዜጦችን ቅርጽና ዘውግ መለየት፣ የኮሚፒውተር ጽሁፎችን ከታተሙ ጽሁፎች ጋር ማወዳደር፣ የተጠቀሱ ምንጮችና በየመካከሉ የገቡ ስዕሎችና ግራፎችን ሚና መለየት፣ በኮምፒውተር የቀረቡ ጽሁፎችን ከድምጽና ምስል ጋር ማቀናጀትን ሁሉ ያካትታል:: የእነዚህ ነገሮች መካተት አዲሱን የተሻጋሪያዊ ኤክስቴንሽን ሞዴል እንዲታወቅ አድርጓል (Fox & Alexander, 2009)፡፡ በአጠቃላይ ከ1960ቹ ጀምሮ እስካለንበት ጊዜ ድረስ በአንብቦ መረዳት ላይ የተሰሩ ምርምሮች የማውጣትና የመሰብሰብ ሞዴል፣ የመገንባትና የማዋሀድ ሞዴልና ተሸጋጋሪያዊ ኤክስቴንሽን ሞዴል የሚባሉ ሶስት የተለያዩ ሞዴሎችን አስገኝቷል፡፡ የሞዴሎቹ መለያየትም በማንበብ ሂደት ላይ የራሱን አስተዋጽኦ ያበረክታል፡፡

ስለ አንብቦ መረዳት ሌላው መነሳት ያለበት ነጥብ እንዴት ይለካል? የሚለው ጥያቄ ነው፡፡ Leslie & Caldwell (2009) እንዳስገነዘቡት አንብቦ መረዳትን መለኪያ ዘዴዎች መደበኛና ኢ መደበኛ ተብለው በሁለት ይከፈላሉ፡፡ ቀደምት የመደበኛ መለኪያ ዘዴዎች አጭር አንቀጽ መጠቀምና ምርጫን ያካትታሉ፡፡ ምርጫ በመጠቀም የሚለኩ ክሂሎችን በዘጠኝ ቡድኖች እንደሚከተለው ከፍለዋቸዋል፡፡ (1) የቃላትን ትርጉም ማስታወስ; (2) ከይዘቱ ውስጥ ያሉትን ቃላት ትርጉም ማጠቃለል; (3) የምንባቡን ቅርጽ መከተል (4) የምንባቡን ዋና ሀሳብ ማቀናጀት (5) በምንባቡ በግልጽ ወይም በስውር የቀረቡ ይዘቶችን መሰረት በማድረግ ለጥያቄዎች መልስ መስጠት (6) ሀሳቦችን በተለያየ አቅጣጫ መረዳት (7) ከይዘቱ ማጠቃለያ ማውጣት (8) የጸሀፊውን ቴክኒክ መለየትና (9) የጸሀፊውን አላማ ነጥብ ድምጸትና አካሄድ መለየት ናቸው፡፡

ከ1970ቹ እስከ 1980ቹ መጀመሪያ ባሉት ጊዜያት የአንብቦ መረዳት መለኪያ የሚያጠነጥነው ቅደም ተከተል በመጠበቅ፣ ዋናውን ሀሳብ በማግኘትና በማጠቃለል ክሂሎች ላይ ሲሆን በ1980ቹ መጨረሻ አካባቢ ረጅም ምንባቦችን እንዲሁም ቀደምት እውቀትና ብልሀትንም በመጨመር መለካት ተጀመረ (Leslie & Caldwell, 2009)፡፡ ነገር ግን በ2000 መግቢያ ላይ አንብቦ መረዳትን ለመለካት የምንባቡ፣ የጥያቄዎቹ፣ የሰዎቹ፣ የምንባቡ ዘውግና ጭብጥ የመሳሰሉ ተላወጦዎች ተጽዕኖ አብሮ መታየት እንደ ተጀመረ Leslie & Caldwell (2009)

ያስረዳሉ፡፡ ከዚህ በተለየ መልኩ የአንብቦ መረዳት መደበኛ መለኪያ መሳሪያ ጥያቄዎችን፣ ማስታወስ ወይም እንደ ገና ማለት፣ ኢ መደበኛ የማንበብ አጋጣሚዎች፣ ግልጽ ውይይቶች ፣ አረፍተ ነገር የመለየት ተግባራትና የተለያዩ የመለኪያ ዘዴዎችን በዋናው ስር ማደራጀት የመሳሰሉ ኢ መደበኛ መለኪያ መሳሪያዎችን ያካትታሉ (Leslie & Caldwell, 2009)፡፡

## 2.4 ስነፅሁፋዊ ስራዎችን ተጠቅሞ ቋንቋን ማስተማር

በጥቅሉ ሲታይ የትምህርት አሰጣጥ ዘዴ በጣም ሰፊ ጽንሰ ሀሳብ ነው፡፡ በዚህ ስር የሚካተቱ በርካታ የትምህርት አቀራረቦችና ቴክኒኮች ያሉ ሲሆን እነዚህ ቴክኒኮችና አቀራረቦች በግላቸው የተለያየ አላማን ለማስፈጸም አጋዥች ናቸው፡፡ የትምህርት አሰጣጥ ዘዴ በተማሪዎች ዘንድ ለማምጣት የምናስበውን የባህሪም ሆነ የዕውቀት ለውጥ ለማስገኘት ዋነኛ መሳሪያ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ለማምጣት የምናስባቸውን ለውጦች በአንድ ጊዜ ለማስገኘት የሚያስችል አንድ ወጥ ዘዴ ግን የለም፡፡

ስለትምህርት አቀራረብ ዘዴዎች ለመነሻ ያክል ይህን ካልን በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ከሚጠቀሱት የትምህርት አቀራረብ ዘዴዎች መካከል አንዱ ስለሆነውና በዚህ ጥናትም ልዩ ትኩረት ስለሚሰጠው ስነፅሁፋዊ ዘዴ የተወሰኑ ሀሳቦችን እንመልከት፡፡

እንደ Ibsen (1995) አገላለጽ በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ስነፅሁፋዊ ዘዴ ማለት የፈጠራ ጽሑፎችን በምንጭነት በመጠቀም የቋንቋ አጠቃቀምን ለማስተማር የሚያገለግልና በባህሪው ተማሪ- መራሽ የሆነ የማስተማር ዘዴ ነው፡፡ በፈጠራዊ ዘዴ የቋንቋ መማር ማስተማር ሂደት አሀዱ (text) የክፍሉ የጋራ ተሞክሮ ወይም ልምድ ይሆናል፡፡ በዚህም በክፍሉ ውስጥ የመማር አውድ ይፈጥራል፡፡ በሌላ አገላለጽ ተማሪዎች አሀዱን ካነበቡ በኋላ የሚኖራቸው አመለካከት ወደ አንድ የጋራ አቅጣጫ እንዲያመራ ይረዳል፡፡

ፈጠራዊ ዘዴ ተማሪዎች እንዲያዳብሯቸው የሚጠበቅባቸውን ማናቸውንም ችሎታዎች (የቋንቋ አጠቃቀም፣ የመጻፍ ችሎታ ወዘተ.) በማናቸውም የመማር መስኮችና ሁኔታዎች በማስረጽ ረገድ ውጤታማ ነው፡፡ ስለሆነም በአንድ የማስተማር ጊዜ ተግባቦታዊ ችሎታ፣ ፈጠራዊ ችሎታና ባህላዊ ችሎታ ለማዳበር ሊያገለግል ይችላል፡፡ ፈጠራዊ ዘዴ በቋንቋ ትምህርት ውስጥ የቃላትን ፍቺ በገቡበት አውድ በመፈለግ ረገድ አራቱን ክሂሎች ያጣመረ ነው፡፡ በተጨማሪም የተማሪዎችን ማህበራዊ ክሂሎች በማዳበር ከታላሚው ቋንቋ ማህበራዊ ስርዓት ጋር ተስማምተውና ተግባብተው እንዲኖሩ ይረዳቸዋል (Ibsen, 1995)

ስነፅሁፋዊ የማስተማሪያ ዘዴ ሶስት አበይት ደረጃዎች ያሉት ሲሆን እያንዳንዱ ደረጃም በውስጡ ሁለት ሁለት ንዑሳን ደረጃዎች አሉት፡፡ ተሳትፎ (involvement) የሚባለው አብይ

ደረጃ በውስጡ ገፋፊ ሀይል (impetus)ና ግብዓት (input) የሚሉትን ንዑሳን ደረጃዎች የያዘ ሲሆን መስተጋብር (interaction) ደግሞ በውስጡ መለየት (identification)ና የአርምሞ (የዝምታ ጊዜ) (incubation) የሚሉትን ንዑሳን ደረጃዎች ይዟል፡፡ እንዲሁም ፍካሬ (interpretation) የሚባለው አብይ ደረጃ በውስጡ ጅማሮ (initiation)ና ማዛመድ (integration) የሚሉትን ንዑሳን ደረጃዎች ይዟል፡፡ የንዑሳን ደረጃዎች መነሻ በመሆን የሚያገለግሉት አበይት ደረጃዎች ናቸው፡፡ በደረጃ ሲታዩ አንደኛው ለአንደኛው ቅድመ ሁኔታዎች ናቸው፡፡ ማለትም የመጀመሪያው ንዑስ ደረጃ ለሁለተኛው፣ የሁለተኛው ለሶስተኛው…ቅድመ ሁኔታዎች ናቸው፡፡ ሶስቱ አበይት ደረጃዎች የያንዳንዱን ተማሪ የመማር ሂደት የሚመለከቱ ሲሆን በሁለተኛ ደረጃ የሚታዩት ስድስቱ ንዑሳን ደረጃዎች ደግሞ ስነ ዘዴያዊ ቅድመ ሁኔታዎችና ስነ ዘዴያዊ አቀራረቦችን የሚመለከቱ ናቸው (Ibsen, 1995 )

የዚህ ስነ ዘዴ አፍላቂ የሆኑት Ibsen (1995) እነዚህን ደረጃዎች በጥቅል መጠሪያ (the I model) የአይ ሞዴል ብለው ሰይመውታል፡፡ የስያሜው መነሻም የስድስቱ ንዑሳን ደረጃዎች ስያሜ የመጀመሪያ ፊደል አይ (I) መሆኑ ነው፡፡ ኢብሰን የፈጠሯቸውን የአይ ሞዴል ስድስቱን ደረጃዎች ከዚህ ቀጥለን አንድ በአንድ እንመልከት፡፡

**ሀ. ገፋፊ ሀይል** (Impetus)

ይህ ደረጃ የፈጠራ ስራዎችን ተጠቅሞ ቋንቋን በመማር ማስተማር ሂደት ሀሳብን በመቀበልና በመደራደር የመጀመሪያው ደረጃ ነው፡፡ በዚህ ደረጃ የተማሪዎች የመማር ፍላጎት ይነሳሳል፣ ስሜታቸውም ይቀሰቀሳል፡፡ ይህም በክፍል ውስጥ ለሚኖረው የነቃ ተሳትፎ ምቹ አጋጣሚን ይፈጥራል፡፡ ገፋፊ ሀይል ቅብብሎሻዊ ክሂሎች በማስተማር ረገድ የቅድመ ንባብ፣ የቅድመ ማዳመጥ፣ ወይም የቅድመ ጽሕፈት ደረጃዎችን የሚሸፍን ነው፡፡

**ለ. ግብዓት** (Input)

ይህ ደረጃ በስነ ጽሑፍ አማካይነት ተማሪዎች ቋንቋን ሲማሩ አሀዶችንና ሌሎች ስነ ጽሑፋዊ ስራዎችን የሚያነቡበት ወይም የሚያዳምጡበት ደረጃ ነው፤ ዕውቀትንና ቋንቋን ለማዳበር ዝግጁ የሚሆኑበትም ደረጃ ነው፡፡ ቀጣይ የመማር ተግባራትን ለማከናዎን ይቻል ዘንድም የነቃ የመማር ተሳትፎን የሚጠይቅ ደረጃ ነው፡፡

**ሐ. ልየታ** (Identification)

ይህ ደረጃ በስነ ጽሑፍ አማካይነት የሚፈጠረው የቋንቋ ተግባቦታዊ ሚና የሚታይበት ነው፡፡ ምክንያቱም ተማሪዎች በስነ ጽሑፋዊ ስራዎች ውስጥ ከሚያገኟቸው ገጸ ባህሪያት፣ ጭብጦች፣ ግጭቶች…ወዘተ. በመነሳት በያንዳንዱ ጉዳይ ላይ ጥቅል ቅኝት እንዲያካሂዱ እድል ይሰጣቸዋል፡፡ ይህም ተማሪዎች ስለአንድ ነገር እንዲያስቡ እንዲያሰላስሉ ያደርጋቸዋል፡፡

በቡድንና በጥንድ እየሆኑም የፈጠራ ስራው ስላጫረባቸው ጉዳይ የሚወያዩበት ወቅት በመሆኑ የተግባቦት ሂደት በጉልህ የሚታይበት ደረጃ ነው፡፡ ከፈጠራ ስራው ውስጥ ያገኙትን ተሞክሮም ራሳቸው ከሚያውቁት ተሞክሮ ጋር እንዲያነጻጽሩ እድል ያገኛሉ፡፡

**መ. የአርምሞ (የዝምታ) ጊዜ (Incubation)**

ይህ ደረጃ ተማሪዎች ከስነ ጽሑፋዊ ስራዎች ያገኙትን ልምድ ተጠቅመው ለመናገር ወይም ለመጻፍ ዝግጅት የሚያደርጉበት ነው፡፡ በዚህ ደረጃ ግላዊ አስተውሎትና መጻፍ እንዲሁም በዚሁ ሳቢያ የሚመነጨውን ሀሳብ በማፍለቅ ውጤት ይታይበታል፡፡

**ሠ. ጅማሮ (Initiative)**

ይህ ደረጃ በፈጠራ ስራዎች አማካይነት የተነሳሱት የተማሪዎች ስሜትና ፍላጎት በተግባር ላይ የሚውሉበት ነው፡፡ ከነዚህ የፈጠራ ስራዎች የተገኙት ልምዶች በተማሪዎች አእምሮ ላይ ያነሳሱት ሀሳብ ተብላልቶ አዲስ የተግባቦት አውድ ይፈጥራል፡፡ በመሆኑም ተማሪዎች በየግላቸው ያብላሉት ሀሳብ በጋራ ዳብሮ በአንድ ማዕከላዊ ነጥብ ላይ መግባባት ላይ መድረስ ያስችላል፡፡ በዚህ ደረጃ በጽሑፍ የቀረቡትን ሀሳቦች እንደገና በመቃኘት የቃላት፣ የሰዋስው ማስተካከያ ሲደረግበት ተማሪዎች ለተከታዩ ደረጃ ይዘጋጃሉ፡፡

**ረ. ማዛመድ (Integration)**

የስነጽሁፋዊ ጽሑፎችን በማንበብ የተገኘን እውቀት ቀደም ሲል ከነበረ ግላዊ እውቀት ጋር ለማገናዘብ የሚቻልበት ደረጃ ነው፡፡ ቋንቋንና ስነ ጽሑፍን ማቆራኘትም የፈጠራዊ ዘዴ የመጨረሻ ግብ ነው፡፡ ይህ ደረጃ ተማሪዎች ከተለያዩ የስነ ጽሑፍ አይነቶች ጋር በመተዋወቅ ባንዱ ወይም ከዚያ በላይ በሆኑት ላይ ትኩረት በማድረግ ጥሩ አንባቢዎች ወይም ጸሐፊዎች ለመሆን የሚያልሙበት ነው፡፡ በስነ ጽሑፍ አማካይነት ሊገኙ የሚችሉ ጠቀሜታዎችን በተመለከተ የተሰነዘሩ አስተያየቶች የሚለኩትም በዚህ ደረጃ ነው፡፡

Ibsen (1995) ከዘረዘሯቸው ስድስቱ የስነጽሁፋዊ የማስተማሪያ ዘዴ ደረጃዎች በተጨማሪ ሰባተኛ ደረጃ ሊኖር ይችላል፡፡ ይኸውም መተግበር (Implementation) ነው፡፡ በዚህ ደረጃ ተማሪዎች ራሳቸው አመንጭተው ድርሰቶችን መጻፍ እንደሚችሉ መገመት ይቻላል፡፡

እነዚህ የተመለከትናቸው የስነጽሁፋዊ የማስተማሪያ ስነ ዘዴያዊ አቀራረቦች ሊተገበሩ የሚችሉት ተማሪውና መምህሩ በሚኖራቸው የመማር ማስተማር መስተጋብር ነው፡፡ ስነ ዘዴያዊ አቀራረቦቹ ውጤታማ ይሆኑ ዘንድ መምህራን ሊኖራቸው የሚችለውን ሚና ከዚህ ቀጥለን እንመለከታለን፡፡

### 2.4.1 **ቋንቋን መሰረት ያደረጉ ስነ ዘዴያዊ አቀራረቦች**

ቋንቋን መሰረት ያደረጉ ስነ ዘዴያዊ አቀራረቦች ተከታዮቹ እንደሆኑ (Lazar, 1993፡ 23-27) ያስረዳሉ፡፡ እነዚህም፡-

- አራቱን ክሂሎች በማዳበር ላይ ያተኮረ ስነ ዘዴያዊ አቀራረብ
- ስነ ጽሑፍን እንደጥናት መስክ በማጥናት ላይ ያተኮረ ስነ ዘዴያዊ አቀራረብ
- ስልታዊነት
- የሰብዕና እድገት ማበልጸግን መሰረት ያደረገ ስነ ዘዴያዊ አቀራረብ ናቸው፡፡

ከዚህ በመቀጠል የእነዚህን ስነ ዘዴያዊ አቀራረቦች ምንነት ባጭር ባጭሩ እንመልከት፡፡

**ሀ. አራቱን ክሂሎች በማዳበር ላይ ያተኮረ ስነ ዘዴያዊ አቀራረብ**

እንደ Lazar (1993: 27) የዚህ ስነ ዘዴያዊ አቀራረብ ስነ ዘዴያዊ ግምት በስነ ጽሑፍ አሀዶች መሳሪያነት ቋንቋን መማር መርሀ- ትምህርቱን ከቋንቋና ስነ ጽሑፍ ጋር ለማገናኘት ይረዳል የሚል ነው፡፡ ይህ አመለካከት ተማሪዎች በታላሚው ቋንቋ አጠቃላይ የሆነ የቋንቋ እውቀት እንዲኖራቸው ከማድረጉም በላይ በቋንቋው ውስጥ የተለመዱትን ሰዋስዋዊ፣ ቃላዊና ዲስኩራዊ ክፍሎችን በአእምሯቸው ውስጥ ቀርጸው በአስፈላጊው ወቅት ሁሉ ስነጽሑፍ ላይ ሂስ እንዲሰጡ ያደርጋቸዋል፡፡

የቋንቋ ክሂሎችን ለማበልጸግ የሚረዳው ስነ ዘዴያዊ አቀራረብ አብይ ትኩረቱ አንድን ስነ ጽሑፍ ቋንቋን በማስተማር ሂደት እንዴት በመሳሪያነት ወይም በምንጭነት ልንጠቀምበት እንችላለን? የሚለው ላይ ነው፡፡ የፈጠራ ስራዎች የቋንቋ አጠቃቀም ለመዳ ሂደትን ስለሚያፋጥኑ እንደምንጭ ሆነው እንዲያገለግሉ በር ይከፍታል፡፡ ከዚህ ባለፈ ይህ ስነ ዘዴያዊ አቀራረብ ስነ ጽሑፍን እንደጥናት መስክ ማጥናት ላይ፣ ስልታዊ በሆነ መልኩ ባንዳንድ ስነ ልሳናዊ ገጽታዎች ላይ ትንታኔ መስጠት ላይ…ወዘተ. ትኩረት አያደርግም (Lazar, 1993: 28)፡፡

Carter and Long (1991: 7-8) በበኩላቸው ቋንቋን መሰረት ባደረገው ስነ ዘዴያዊ አቀራረብ ላይ ለቋንቋ ክሂሎች ቅድሚያ መስጠት አስፈላጊ እንደሆነ ይገልጻሉ፡፡ እንደነሱ አገላለጽ በዚህ ስነ ዘዴያዊ አቀራረብ በስነ ጽሑፍ አማካይነት ቋንቋን ማስተማር እጅግ ጠቃሚ ቢሆንም አፈጻጸሙ መምህር- መራሽ መሆኑ አላስፈላጊ ነው፡፡

በአጠቃላይ ቋንቋን መሰረት ያደረገና ተማሪ-መራሽ የሆነው ስነ ዘዴያዊ አቀራረብ ዋነኛ አላማው ተማሪዎች ከአሀዱ ጋር እንዲተዋወቁና ከዚህ በፊት የሚያውቁትን ልምድም ከፈጠራ ስራዎች ጋር እንዲያዛምዱ ማድረግ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አሀዱ (ጽሑፉ) ያሳደረባቸውን ስሜት ወይም ያገኙትን ግንዛቤ በጽሑፍም ሆነ በንግግር በብቃት መግለጽ እንዲችሉ ማስቻል

ነው፡፡ በእንዲህ አይነቱ የመማር ማስተማር ሂደት በቋንቋ አንጻር የሚኖረው ተራክቦ አንድ መንገድን ብቻ የተከተለ አይደለም፡፡ እንደተግባራቱ አይነትና ባህሪ በጥንድ፣ በቡድን፣ በግል ተግባቦት ይካሄዳል፡፡ ይህም የተማሪዎችን የቋንቋ ክህሎት በከፍተኛ ደረጃ ያሳድጋል፡፡

**ለ. ስነ ጽሑፍን እንደጥናት መስክ በማጥናት ላይ ያተኮረ ስነ ዘዴያዊ አቀራረብ**

ይህ አቀራረብ በአብዛኛው ተግባራዊ የሚሆነው በኮሌጅ (ዩኒቨርሲቲ) ደረጃ በሚማሩ ተማሪዎች ላይ ነው፡፡ የስነ ጽሑፍ ታሪኮች፣ የስነ ጽሑፍ ይዘቶች፣ የስነ ጽሑፍ ዘሮች፣ የስነ ጽሑፍ መሰረታዊ ጉዳዮች…ወዘተ. ላይ ትኩረት የሚያደርግ አቀራረብ ነው፡፡

**ሐ. የስልታዊነት አቀራረብ**

ስልታዊነት ድንበር ለይተው የቆሙትን ሁለቱን የትምህርት ዘርፎች ማለትም ስነ ጽሑፋዊ ሂስንና ስነ ልሳንን ለማገናኘት እንደ ድልድይ ሆኖ የሚያገለግል ዘርፍ ነው፡፡ በሁለቱ የትምህርት ዘርፎች ብቻም ሳይሆን በሁለቱ የትምህርት አይነቶች፣ የቋንቋ ትምህርትና የስነ ጽሑፍ ትምህርት መካከልም የቆመ ነው (Widdowson, 1975: 3-4)፡፡

ስነ ልሳን ለስነ ጽሑፋዊ ሂስ የሚያበረክተው የተወሰነ ፋይዳ አለ፡፡ እንደዚሁም ስነ ጽሑፋዊ ሂስ ለስነ ልሳን የሚያበረክተው ፋይዳ ይኖረዋል፡፡ ስልታዊነት በስነ ልሳንና በስነ ጽሑፍ መካከል የሚገኝ ነው ካልን እንደተነሳንበት አላማ ወደ አንዱ ሊያደላ የሚችልበት አጋጣሚ ይኖራል፡፡ ዋና ትኩረቱ ግን ከስነ ልሳናዊ እውነታዎች ጋር በተያያዙ ገለጻዎች ላይ ተመርኩዞ ትርጉምን ወይም ትርጓሜን በተቻለ መጠን ግልጽና ምልዑ በሆነ መንገድ ማቅረብ ነው (Widdowson, 1975: 1 እና Short, 1995: 1-5)፡፡

ስልታዊነት ስነ ጽሑፋዊ ስራን ለመተንተን የሚነሳው ከመሰረታዊ እሳቤ ሲሆን ስነ ልሳናዊ ቅደም ተከተሎችን ተከትክሎ ትንታኔውን ያቀርባል፡፡ የስልታዊነት ባለሙያዎች ስራም ስነ ጽሑፋዊ ስራው እንዴት እንደተዋቀረ ስነ ልሳንን መሰረት በማድረግ መተንተን ነው፡፡ ስለዚህም በአንድ ጽሑፍ ውስጥ የሚገኘውን ማነኛውንም ከቋንቋ ጋር ተዛምዶ ያለውን የጽሑፍ አካል ይተነትናል (Carter, 1986: 161) ፡፡

ስነ ጽሑፍ ያለውን አሻሚነት ለመተንተን ብሎም ለመረዳት እንዲሁም ጸሐፊው በቋንቋው እንዴት እንደተገለገለበት ለመገንዘብ ስልታዊነት እጅግ የጎላ ጠቀሜታ አለው (Widdowson, 1975: 10)፡፡ ስልታዊነት በባህሪው ራሱን ችሎ እንደማይሰራበት ዊዶውሰን ያስረዳሉ፡፡ ይኸውም የስነ ልሳንና የስነ ጽሑፍ ሂስን መሰረት አድርጎ የሚሰራበት ነው፡፡ በነዚህ ሁለት ሂሶች መካከል በእርግጥ ልዩነቶች አሉ፡፡ ልዩነታቸው የሚመነጨው ለቋንቋ ትንታኔ ከሚሰጡት

ጥልቀት አንጻር ነው፡፡ ስልታዊነት በዚህ ባህሪውም ቋንቋን ለሚማሩ ተማሪዎች ከሚማሩት ቋንቋ ወይም ስነ ጽሑፍ በመነሳት ቋንቋውን እንዲረዱት ያግዛቸዋል፡፡

**መ. የሰብዕና እድገት ማበልጸግን መሰረት ያደረገ ስነ ዘዴያዊ አቀራረብ**

ግጥም የተማሪዎችን የቋንቋ ክህሎትና ዕውቀት ከማበልጸጉም በላይ የተለያዩ ግላዊ ልምዳቸውን፣ አመለካከታቸውን፣ አስተሳሰባቸውን፣ አላማቸውን እንዲያዳብሩ ላቅ ያለ እገዛ ያደርጋል፡፡ ከዚህ ባሻገር ተማሪዎችን በማነቃቃት ለትምህርቱ ትኩረት እንዲሰጡ በማድረግ፣ እውናዊ ከሆነው የቋንቋ አጠቃቀም ጋር እንዲተዋወቁ እድል በመፍጠርም ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው፡፡

## 2.4.2 ከአንድ አሀድ ውስጥ የሚዘጋጁ መልመጃዎች አይነትና ባህሪያት

### 2.5.2.1 የመልመጃዎች ባህሪያት

Nuttal,C (1982፡ 120) እና Silberstein,S (1994፡ 135) እንደሚያስረዱት አንብቦ መረዳትን ለማዳበር የሚያስችሉ ከአንድ አሀድ ሊወጡ የሚችሉ መልመጃዎች ባህሪያት ከሚባሉት ውስጥ ዋና ዋናዎቹ ተከታዮቹ ናቸው፡፡

**ሀ. የቃል በቃል ምላሽ የሚሹ መልመጃዎች**

የዚህ አይነት ባህሪ ያላቸው መልመጃዎች ተማሪዎች ከሚያነቡት ጽሑፍ ውስጥ በቀላሉና ብዙም ሳይቸገሩ የሚቀርብላቸውን ጥያቄ ለመመለስ የሚያስችሉ ናቸው፡፡ በነዚህ አይነት መልመጃዎች የሚቀርቡ ጥያቄዎች መልሳቸው ከቀረበው አሀድ ውስጥ በቀጥታና በተሟላ ሁኔታ የሚገኝባቸው ናቸው፡፡ ስለዚህ ተማሪው መልስ ለመስጠት ከአሀዱ ውጭ መሄድ አይጠበቅበትም፡፡

**ለ. በራስ አገላለጽ የሚመለሱ መልመጃዎች**

የዚህ አይነት ባህሪ ያላቸው መልመጃዎች ከላይኞቹ የተለዩ ናቸው፡፡ እነዚህኞቹ መልመጃዎች የተማሪዎችን የራስ አገላለጽና የቃላት አጠቃቀም የሚጠይቁ ናቸው፡፡ እንደላይኞቹ ቃል በቃል የሚመለሱ አይደሉም፡፡ ስለሆነም የአሀዱን ጭብጥ በሚገባ መረዳት የግድ አስፈላጊ ነው፡፡ እነዚህ አይነት መልመጃዎች አሀዱን መሰረት አድርገው ለሚቀርቡ ጥያቄዎች ሀሳቡን ሳያዛቡ በራስ አገላለጽ መልስ መስጠትን የሚጠይቁ ናቸው፡፡ በመሆኑም የተማሪዎችን የፈጠራ አቅም በማነሳሳትና አዲስ ሀሳብ እንዲያፈልቁ በማድረግ ረገድ ላቅ ያለ ጠቀሜታ አላቸው፡፡

**ሐ. አውዳዊ መልስ የሚሹ መልመጃዎች**

የዚህ አይነት ባህሪ ያላቸው መልመጃዎች ተማሪዎች በቃላት፣ በሀረጋትና በዐ.ነገራት መካከል ሊኖር የሚችለውን የሀሳብ ትስስር በውል ተረድተው ምላሽ እንዲሰጡ የሚያደርጉ ጥያቄዎችን የያዙ ናቸው፡፡ መልመጃዎቹ አላማቸውን ይመቱ ዘንድ መምህራን ተከታዮችን ተግባራት

ቢያከናውኑ ይመረጣል፡፡ በአሀዱ ውስጥ ቁልፉ ሀሳብ የያዙ የተወሰኑ ቃላትን አውጥቶ ያልተሟላውን ሀሳብ መሰረት በማድረግ የሚመለሱ አውዳዊ ጥያቄዎችን መስጠት፣ከበድ ከበድ ያሉ ቃላት ያሉበት የተሟላ ጽሑፍ ሰጥቶ ጥያቄዎችን (በአውድ) እንዲመልሱ ማድረግ፣ በሚገቡበት አውድ የትርጉም ለውጥ የሚያመጡ ቃላትን እንዲለዩና ከመዝገበ ቃላዊ ፍቻቸው ጋር እንዲያነጻጽሩ ማገዝ፣ ከቃላት ባሻግር ሀረጋትንና ዐ.ነገራትን በአገባባቸው መሰረት መፍታት (መተርጎም) እንዲችሉ የሚያስችሉ መልመጃዎችን መስጠት፣ ማሰራት፡፡

**መ. ግምገማን የሚሹ መልመጃዎች**

ተማሪዎች በመልመጃዎቹ ውስጥ ለሚቀርቡ ጥያቄዎች መልስ እንዲሰጡ ብቻ ሳይሆን ምንና እንዴት እንደሚመልሱም ጭምር ተረድተው መልሳቸው ላይ ተጨባጭ መረጃዎች እንዲያቀርቡ የሚጠይቁ መልመጃዎች ናቸው፡፡ እንደዚህ አይነት ባህሪ ያላቸው መልመጃዎች የተማሪዎችን የአስተሳሰብ ደረጃ ከፍ እንዲል የሚያደርጉ ናቸው፡፡ የውስብስብነት ባህሪ የሚስተዋልባቸው ናቸው፡፡ ከዚህ ባሻግር ተማሪዎች መልስ ከመስጠታቸው በፊት በአሀዱ ውስጥ የቀረበውን ሀሳብ ከራሳቸው አመለካከት አኳያ መተንተንን ወይም መገምገምን እንዲለማመዱ ያደርጋል፡፡ ምክንያቱም መልመጃዎቹ የተማሪዎችን ሂሳዊ አስተሳሰብ፣ ምናብንና ልምድንም ጭምር የሚጠይቁ መሆናቸው ነው፡፡

**ሠ. ግላዊ አስተያየትን የሚሹ መልመጃዎች**

ተማሪዎች የተመረጠውን አሀድ ከተለያዩ ተዛማጅ አሀዶች ጋር አገናዝበው፣ ከራሳቸው ገጠመኝ ጋር በማነጻጸርና በማወዳደር የግል አመለካከታቸውን እንዲሰጡ የሚጋብዙ ጥያቄዎችን የሚይዙ መልመጃዎች ናቸው፡፡ አቀራረባቸውም ‹‹ስለዚህ ጉዳይ ያለህ/ሽ አቋም ምን ይመስላል፣ ከዚህ በላይ ስለቀረበው ሀሳብ ምን አስተያየት አለህ/ሽ›› የሚል አይነት ነው፡፡

**ረ. የማስታወስ ችሎታን የሚጠይቁ መልመጃዎች**

የዚህ አይነት ባህሪ ያላቸው መልመጃዎች ተማሪዎች ቀደም ብለው ያነበቡትን አሀድ መልመጃዎችን ሲሰሩ መለስ ብለው እንዲያስታውሱ በማድረግ አሁን ከገበዩት አዲስ እውቀት ጋር እንዲያገናዝቡ የሚያደርጉ ጥያቄዎችን የያዙ ናቸው፡፡ ለምሳሌ አሁን ካነበብከው/ሽው አሀድ ጋር ተመሳሳይ የሆነ ሀሳብ ያለው ሌላ አሀድ አንብበህ/ሽ ታውቃለህ/ ታውቂያለሽ፡፡

### 2.4.2.2 የመልመጃዎች አይነት

በስነ ጽሑፍ አማካይነት ቋንቋን ለማስተማር ከተመረጠ አሀድ የሚዘጋጁ መልመጃዎች በሁለት አይነት ይከፈላሉ፤ የቋንቋ መልመጃዎች (Language Exercises) እና ስነ ጽሑፋዊ (የይዘት) መልመጃዎች (Literary or Content Exercises) ተብለው (Waker, 1983: 6-9)፡፡ ዝርዝሩን ቀጥለን እንመልከት፡፡

### 2.4.2.2.1 የቋንቋ መልመጃዎች

የቋንቋ መልመጃዎች የተማሪዎችን የቋንቋ ችሎታ የሚያዳብሩና ለሚያጋጥሟቸው ስነ ጽሑፋዊ መልመጃዎች በደንብ የሚያዘጋጇቸው ሆነው ሊዘጋጁ ይገባል፡፡ በቋንቋ መልመጃዎች ውስጥ ተከታዮቹ መልመጃዎች ይካተታሉ፡፡

**ሀ. የዐ.ነገር አወቃቀር መልመጃዎች**

የነዚህ አይነት መልመጃዎች በቤት ስራ መልክ በጽሑፍ ተዘጋጅተው እንዲቀርቡ ሊደረጉ ይችላሉ፡፡ ወይም በክፍል ውስጥ በጥንድ/ በቡድን ሊሰሩ ይችላሉ፡፡

**ለ. የቃላት መልመጃዎች**

በአንድ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ሰዎች ከ90% በላይ የሚሆኑ ቃላትን ከአውድ ጋር በተገናኘ መልኩ ይማራሉ፡፡ ይሁን እንጂ በስነ ጽሑፍ ውስጥ የሚገኙትን ቃላት በተራ ንግግር ወይም ጽሑፍ ውስጥ እንደሚገኙ ቃላት በቀላሉ ለመገንዘብ አስቸጋሪ ነው፡፡ ስለሆነም ተማሪዎች የቃላትን አውዳዊ ፍቺ ለመረዳት የሚሰጣቸውን አሀድ በተለያየ አቅጣጫ ሊፈትሹት ግድ ይላል፡፡ ይህን ባደረጉ መጠን የቃላት እውቀታቸው ይጨምራል፣ በስነ ጽሑፋዊ ስራውም የመሳብና የመደሰት ነገር ይመጣል፡፡

ቀጥለው የተዘረዘሩት ፋይዳዎች በስነ ጽሑፍ አውድ ተጠቅሞ ቃላትን ማስተማር የሚያስገኛቸው ናቸው፡፡ በቀረበላቸው አሀድ ውስጥ የሚገኙ የከባድ ቃላትን ፍቺዎች ለማወቅ አገባባዊ፣ ሰዋስዋዊ፣ ተጠየቃዊ ፍንጮችን ለመጠቀም ያስችላቸዋል፣ የቃላት እውቀታቸው በከፍተኛ ደረጃ ያድጋል፣ በአሀዱ ውስጥ የተካተቱ ቁልፍ ቃላትን ለመረዳት ይረዳቸዋል፣ የቃላትን ትርጓሜ ለማወቅ የሚያደርጉት ዳሰሳ የመማር ፍላጎታቸው ከፍ እንዲል ያደርጋል፡፡

**ሐ. ክፍት ቦታዎችን በመሙላት የሚሰሩ መልመጃዎች**

በአንድ ጽሑፍ ውስጥ ክፍት ቦታዎችን በመተው ወይም ቃላትን በመግደፍ ተማሪዎች ለቦታው ተስማሚ የሆነውን ቃል መርጠው ወይም ገምተው እንዲሞሉ ለማድረግ የሚያስችሉ መልመጃዎች ክፍት ቦታዎችን በመሙላት የሚሰሩ መልመጃዎች ይባላሉ፡፡ እነዚህን አይነት መልመጃዎች መስራት ተከታዮቹን ጠቀሜታዎች ያስገኛል፡፡

የጽሕፈት ክሂልን ለማጎልበተ ያስችላል፣አንድን ጽሑፍ በትኩረት የማንበብ ልምድን ያሳድጋል የቀረበውን ጽሑፍ ጠንቅቆ የማንበብና የማስታወስ ችሎታን ያጎለብታል፣ ጽሑፍን በትኩረት የማንበብ ልምድን ስለሚያዳብር በጸሐፊው የተፈጠሩ ችግሮች/ ስህተቶች ካሉ ለይቶ ለማውጣትና ማስተካከያ ለመስጠት ያስችላል፡፡

**መ. አንድን ዐ.ነገር በሌላ አቅጣጫ ወይም መንገድ መጻፍን (Paraphrasing) ለመለማመድ የሚያስችሉ መልመጃዎች**

የዚህ አይነት መልመጃዎች ተማሪዎች የቀረበውን ጽሑፍ በራሳቸው አገላለጽ በተለየ መንገድ እንዲጽፉ ለማድረግ የሚያስችሉ ናቸው። እነዚህ አይነት መልመጃዎችን ማሰራትም ተከታዮቹን ፋይዳዎች ያስገኛል።

- ❖ የተለያዩ የዐ.ነገር አይነቶች (ነጠላ፣ ድርብ/ ውስብስብ) መኖራቸውን ያስገነዝባሉ፣
- ❖ በዐ.ነገር ውስጥ የሚገኙ መዋቅሮች (መስተዋድድ፣ ተውሳከ ግስ፣ ገላጭ...) በአንድ ዐ.ነገር ውስጥ ያላቸውን ሚና ለማወቅ ያስችላሉ፣
- ❖ አንድን ዐ.ነገር በልዩ ልዩ መንገድ መጻፍን/ መናገርን ያስለምዳሉ።

### 2.4.2.3 የስነጽሑፍ (የይዘት) መልመጃዎች

እነዚህ አይነት መልመጃዎች የተለያዩ ትርጓሜዎችን ለመስጠት የሚያስችሉ ክፍት ጥያቄዎችን የሚይዙ ሲሆኑ ለክፍል ውስጥ ውይይትና ክርክር ጥሩ መነሻ በመሆንም ያገለግላሉ። ይህ ውይይትና ክርክርም የንግግር፣ የጽሕፈት ወዘተ. ክሂሎችንና የእውቀት ዘርፎችን ለማጎልበት ያስችላል። በነዚህ መልመጃዎች ውስጥ የሚካተቱና የተለያየ ፋይዳ ያላቸው ንዑሳን መልመጃዎች አሉ። ቀጥለን እንመልከታቸው።

**ሀ. መዋቅራዊ መልመጃዎች**

መዋቅራዊ መልመጃዎች ሁለት አይነት አቀራረብ አላቸው። አንደኛው በአዛምድ መልክ የሚቀርብ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ አንድ ጽንሰ ሀሳብ የያዙ ጅምር ዐ.ነገሮችን በመስጠት አሟልተው እንዲጽፉ በመጠየቅ የሚቀርብ ነው። እንደነዚህ አይነት መልመጃዎች ቀጣዮቹን ጠቀሜታዎች ይለግሳሉ።

- ለአሰሳና አስተውሎት ንባብ ቅድሚያ መስጠትን ያስተምራሉ፣
- ዋና ዋና ሀሳቦችን መሰረት አድርጎ ልዩ ልዩ ማጠቃለያዎች መጻፍን ያለማምዳሉ፣
- የሚነበበውን ክንውን መሰረት በማድረግ አንድን ክንውን/ ተግባር በጽሑፍ ወይም በንግግር ቅደም ተከተልን ተከትሎ ማስፈርን ያስተምራሉ።

**ለ. ገጸ-ባህሪያትን መሰረት ያደረጉ መልመጃዎች**

እንደነዚህ አይነት መልመጃዎች ተማሪዎች ከገጸ ባህሪያት ጋር እንዲተዋወቁ ለማድረግ፣ የገጸ ባህሪትን አካላዊ ገለጻ መሰረት በማድረግ ገላጭ ድርሰት እንዲጽፉ ለማበረታታት፣ ከተለያዩ የአጻጻፍ ስልቶች ጋር እንዲተዋወቁ ለማድረግ፣ ገጸ ባህሪያትን በባህሪ እንዲገልጹ (የዋህ፣ ደግ፣ ክፉ...) ለማድረግ የሚያስችሉ ናቸው።

### ሐ. ክፍት መልመጃዎች

ተማሪዎችን በማወያየትና ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ በማድረግ የቋንቋ ችሎታቸውን ለማዳበር የሚያስችሉ መልመጃዎች ናቸው (Nuttal, 1982: 126)፡፡ እንደነዚህ አይነት መልመጃዎች ተከታዮቹ ጠቀሜታዎች አሏቸው፡፡

- በሚደረገው የርስ በርስ ውይይት የቋንቋ ችሎታን በከፍተኛ ደረጃ ያጎለብታሉ፣
- በግል፣ በጥንድ፣ በቡድን መልስ መመለስን ያበረታታሉ፣
- አሀዱ ከተነበበ በኋላ የተገኘውን ግንዛቤ ከሚያውቋቸው ነገሮች ጋር ማገናዘብን ያስተምራሉ፡፡

### መ. ሐተታዊ መልመጃዎች

እንደነዚህ አይነት መልመጃዎች ደግሞ በስነ ጽሑፍ አማካይነት ምን እንዴት እንደተባለ ለመገንዘብ ተማሪዎች የተለያዩ ትርጓሜዎችን ያከናውናሉ፡፡ በዚህ ሂደትም ተማሪዎች ስነ ጽሑፋዊ ስራውን በንቃት ያነባሉ፤ በትምህርቱ ወቅትም ንቁ ተሳትፎ ያደርጋሉ፡፡ ሐተታዊ መልመጃዎች የደራሲው የቋንቋ አጠቃቀም ምን እንደሚመስል ለመመርመር ያስችላሉ፣ደራሲው ያለውን የአጻጻፍ ስልት በመገንዘብ ተማሪዎች የራሳቸውን ችሎታ እንዲያዳብሩ ያስችላሉ፡፡

## 2.5 የግጥምና የአጭር ልቦለድ ባህርያት

ስነ ግጥምና አጭር ልቦለድ ከሌሎች የስነ ፅሁፍ ዘርፎች የሚለዩባቸዉ የየራሳቸዉ ባህርያት አሏቸዉ፡፡ እያንዳዳቸዉን ከዚህ እንደሚከተለዉ ቀርበዋል፡፡ ስነ ግጥም፡-እንደ ዘሪሁን (2000) አገላለፅ ስነ ግጥም በእጅጉ ጥንታዊነት እንዳለዉ የሚነገርለትና የሰዉ ልጅ ለብዙ ዘመናት ደስታዉንና ሀዘኑን፣ምኞትና ደስታዉን፣የአኗኗር ሁኔታዉንና ልዩልዩ ገጠመኙን በማንጎራጎርና በማዜም ሲገልፅበት የቆየ ኪነጥበብ ዘርፍ ነዉ፡፡

ግጥም እንደዘመኑ ፊለግ እንደገጣሚዉና እንደ ስነ ፅሁፍ አዋቂዉ አመለካከት ስለሚለያይ አንድ ወጥ የሆነ ብያኔ የለዉም፡፡ይሁን እንጅ ስነ ግጥም አንድን ነገር ወይም ድርጊት አድምቆና አጉልቶ ማሳየት፣ሃሳብን አክሮና አግዝፎ የማቅረብ ችሎታ ያለዉ በጥቂት ምርጥ ቃላት ብዙ ነገሮችን አምቆ የሚይዝና በሙዚቃዊ ቃናዉ የስሜት ህዋሳትን በቶሎ የሚነካ ለስሜት ቅርብነት ያለዉ ኪነ- ጥበብ ነዉ፡፡

ስነ-ግጥም ከሌሎች የስነ-ፅሁፍ ዘርፎች የሚለይባቸዉ የራሱ የሆኑ ዉስጣዊ ባህርያት ያሉትና ዉስጣዊ ባህርያቱም የተበቀ ምቱ፣ምጣኔዉና የቃላት ምርበዘይቤ ምስል ፊጣሪነቱ ናቸዉ ዘሪሁን (2000)፡፡

አጭር ልቦለድ፡-እንደ ዘሪሁን (2000) አገላለፅ አጭር-ልቦለድ የራሱ ቅርፅና ይዘት ያለዉ ከሌሎች የስነ ፅሁፍ ዘርፎች ተለይቶ የሚታወቅባቸዉ ባህርያት ያሉት በራሱ ክልል ሲጠናና ሲመረመር የራሱ የሆነ ኪነ-ጥበባዊ ስርዓት የሚታይበት፤በራሱ መጠነርዕይ ዉል ያላቸዉ ማህበራዊ እዉነታዎችን ሊያሳይ የሚችል አንድ የስነ-ፅሁፍ ዘር ነዉ።

አጭር ልቦለድ ከሌሎች የስነ-ፅሁፍ ስራዎች ተለይቶ የሚታወቅባቸዉ ባህርያት ፡-ነገሮችን አጉልተዉ የሚያሳዩ መሆናቸዉ፣ዉስብስብ ያለ ወይም የታመቀ ሃሳብ መያዝ፣ጥብቅ ትስስር ያለዉ፣ፈጣንነት ጎልቶ የሚታይበትና የሁሉም ነገር መቋጫ የሆነ አንድ ብቸኛ የትኩረት ነጥብ ያለዉ የልቦለድ አይነት ነዉ ዘሪሁን (2000)።

## 2.6 ኢስነፅሁፋዊ ፅሁፍ

The International Academic Forum www.iafor.org ድረገፅ በዘርፉ የተለያዩ በጥናት መስኩ ተመራማሪዎች ኢልቦለድን የሚበይኑት በተለያየ መንገድ መሆኑን ይገልፃል። ከነዚህም እንደ Gibbova (as cited in Elhabiri, 2014) ኢስነፅሁፋዊ ፅሁፍ የተለያዩ ፅሁፎች የሚጠቀመውም የአሁን ጊዜን ሁኔታና ጉዳይ፣ የመበየን፣ የማብራራት፣ የማስማማት፣ የአንባቢያንን ምን እንደሚያነቡ የሚያብራራ ነው። ሌላው Newmark (2004) እንደሚያብራሩት ኢስነፅሁፋዊ ፅሁፍ የሚፃፈው የነባራዊውን ዓለም ጉዳይና እውነታ እና የነባዊውን ዓለም እውነታ ለአንባቢያን ማቅረብ ነው። እንደ Nurrohmah et al. (2015) አገላለፅ ኢስነፅሁፋዊ ፅሁፍ እውነተኛ መረጃ፣ ትክክለኛ የሆነና በቀላል ቋንቋ የሚቀርብ ነው። በመሆኑም ኢስነፅሁፋዊ ፅሁፍ ትክክለኛ የሆነ፣እውነተኛ ድርጊት፣ መረጃ እና ጉዳይ ለአንባቢያን እንዲያነቡ የሚቀርብ ነው ማለት ይቻላል።

The International Academic Forum www.iafor.org ድረገፅ ብዙ ተመራማሪዎችን መነሻ በማድረግ ኢስነፅሁፋዊ ፅሁፍ ብዙ ዓይነቶች እንደ ሆኑ እንደሚከተለው ለመከፋፈል ይሞክራሉ። እነዚህም እንደ Nurrohmah et al.(2015) ገለፃ ኢስነፅሁፋዊ ፅሁፍን መዛግብት፣ የሳይንስ ፅሁፎች፣ የተለያዩ አከራካሪ ጉዳዮች፣ ወዘተ እንደሆኑ ሲገልፁ እንደእነ Mahdi and Ibraheem (2013) አገላለፅ ደግሞ ኢስነፅሁፋዊ ፅሁፍ ሰፊ ክልል ያለው ፅሁፍ የሆነ እንደ አስተዳደራዊ፣ ህጋዊና ሌሎች መንግስታዊ መረጃዎች፣ የንግድና የገንዘብ ፅሁፎች፣ ሳይንሳዊ ቴክኒካልና ህዝባዊ ፅሁፎች፤ በማለት ይከፍሉታል። በመሆኑም እነዚህ ኢስነፅሁፋዊ ፅሁፎችን የሚያጠቃልሉት ነገሮች አንቀፆች፣ የጋዜጣ ሪፖርቶች፣ ሳይንሳዊ ፅሁፎች፣ የግልና የሌላ ሰው የህይወት ታሪኮች፣ የፊልም ግምገማዎች፣ የማሰልጠኛ ማንዋሎችና ሌሎችን የሚያጠቃልል ነው።

የኢልቦለዳዊ ፅሁፎች ባህሪያት በተለያዩ አጥኚዎች ተብራርቷል፡፡ ከነዚህም መካከል Newmark (2004) ሲገልፁ ኢልቦለዳዊ ፅሁፎች ትኩረት የሚያደርጉት ለአንባያን የነባራዊውን ዓለም እውነታ ማሳየት ነው፡፡ አያይዘውም ሲገልፁ ኢልቦለዳዊ ፅሁፎች የሚፃፉት በሶስተኛ ወገን በቀላል ቋንቋ መረጃን ለመግለፅ ነው፡፡ ስለድምፀቱም ሲገልፁ የኢልቦለዳዊ ፅሁፍ አነባበብ በፍጥነት የሚነበብና ቋንቋውንም በቀላሉ የሚረዱት ነው፡፡ ሌላው እንደ Khosravishakib (2012) አገላለፅ ደግሞ ኢስነፅሁፋዊ ፅሁፍ በተራ ቋንቋ በመጠቀም የሚፃፍ ወይም ቋንቋውን በቀላሉ መረዳት የሚችሉት ነው፡፡ ተራ ቋንቋ በኢስነፅሁፋዊ ፅሁፍ ሲቀርብ የፅሁፉን ክብደት በቀላሉ ለመረዳት ይረዳል፡፡ ከዚህ ነጥብ በመነሳትና የኢልቦለዳዊ ፅሁፍን ከልቦለዳዊ ፅሁፍ ማንበብ ጋር ይለያያል፡፡ ምክንያቱም "ልቦለዳዊ ዊፅሁፍ (ለዋጭ) (ስሜት የሚቀይር) ተራ ቋንቋ (አከራካሪ) በእያንዳንዱ ቀን ንግግር በዘዴ የሚጠቀሙት ነው፡፡

The International Academic Forum www.iafor.org ድረገፅ ሌሎች የዘርፉ ምሁራንን በመጥቀስ ሲገልፅ ኢልቦለዳዊ ፅሁፍ በቋንቋ ትምህርት ክፍል ምንባብን ለማስተማር በጣም የሚጠቅም መሳሪያ ነው፡፡ ለምሳሌ ያክል እንደ Mokhtari (2014) እንደ ገለፁት በኢልቦለዳዊ ፅሁፎች መካከል ምንም ዓይነት ባህላዊ ልዮነት የለም በማለት ያብራራሉ፡፡ ኢልቦለዳዊ ፅሁፍን ተጠቅመን ስናስተምር ተማሪዎች ፅሁፉን እንዲተረጉሙ፣ እንዲያብራሩ አይፈለግም ባህላዊ ልዮነትም የለውም ምክንያቱም ኢልቦለዳዊ ፅሁፍ ዋነኛ ዓላማው የሚያተኩረው በትክክለኛ፣ እውነተኛ፣ በድርጊቶች፣ በመረጃዎችና በጉዳዮች ላይ ነው፡፡ ይሄውም ተማሪዎችም ኢልቦለዳዊ ፅሁፎችን የሚረዱት በግልፅ ነው፡፡ እንደ Mokhtari (2014) አገላለፅ ደግሞ ኢስነፅሁፋዊ ፅሁፎችን መጠቀም ለተማሪዎች የቃላትና የሰዋሰው እውቀት ለማግኘት ይረዳቸዋል፡፡ ለምሳሌ ያህል ተማሪዎች ኢስነፅሁፋዊ ፅሁፍ በሰዋሰውና ቃላትን በቀላሉ ሊረዱ ይችላሉ ማለት ነው፡፡ ምክንያቱም ኢስነፅሁፋዊ ፅሁፍ ቃላትና ሰዋሰው ፅሁፉ በአእምሮ ሊያዙ የሚችሉ ስለሚሆኑ ነው፡፡ ተማሪዎችም በቀጥታ ኢስነፅሁፋዊ ፅሁፍ የተወሰነ ሀሳብን ለማግኘት እንጅ ፅሁፉ እንዲተረጎም አይፈለግበትም፡፡

## 2.7 የሀገር ውስጥ ጥናቶች ቅኝት

አማርኛ ቋንቋን በማስተማር ረገድ ልቦለድና ኢልቦለድ ያላቸውን ሚና በሚመለከት ጥናቶች ተካሂደዋል ብሎ መናገር አይቻልም፡፡ ይሁን እንጂ የተወሰኑ ጥናቶች በስነፅሁፍ ዙሪያ ላይ ተካሂደዋል፡፡ አጥኚው ይዞት ከተነሳው ርዕሰ ጉዳይ ጋር ተዛማጅነት ያለው የውጭ ጥናት ለመቃኘት ተሞክሯል ከዚህ ውጭ ግን ለማግኘት አልተቻለም፡፡ አጥኝው ባደረገው ፍተሻም ወደ ስድስት የሚደርሱ ጥናቶች በሁለተኛ ዲግሪ ደረጃ አግኝቷል፡፡ ጥናቶች ከዚህ ጥናት ጋር

በቀጥታም ባይሆን በተዘዋዋሪ ተቀራራቢነት ያላቸው በመሆኑ በዚህ ክፍል እንደሚከተለው ተቃኝተዋል፡፡

በተደረገው ዳሰሳ በጉዳዩ ላይ ለመጀመሪያ ጊዜ የቀረበው ጥናታዊ ጽሑፍ የዘመንፈስ (1991) ጥናት ነው፡፡ የጥናቱ ርዕስ ‹‹በስነ ጽሑፍ አማካይነት አማርኛ ቋንቋን በማስተማር የአጭር ልቦለድ ሚና በ11ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ የተካሄደ ጥናት›› የሚል ነው፡፡ የጥናቱ ዋነኛ አላማ በአጭር ልቦለድ አማካይነት አማርኛ ቋንቋን በማስተማር ተማሪዎች ሀሳባቸውን በጽሑፍ የመግለጽ ችሎታቸውን ማዳበራቸውን በሙከራ ማረጋገጥ ነው፡፡ ጥናቱ በመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያነት የቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተናንና የጽሑፍ መጠይቅን ተጠቅሟል፡፡ መጠናዊ የምርምር ዘዴን በመረጃ መተንተኛነት የተጠቀመ ሲሆን በጥናቱ መሰረት የተገኘው ውጤት እንደሚያመለክተው በሙከራዊ ሁኔታ በአጥኚው የተማሩት ተማሪዎች የተሻለ ውጤት አስመዝግበዋል፡፡

የዘመንፈስ ጥናት ከዚህ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው ስነ ጽሑፍን መሰረት አድርጎ አማርኛ ቋንቋን በማስተማር ላይ ያተኮረ መሆኑ ነው፡፡ ከዚህ ባሻገር በፈጠራዊ ዘዴ አማርኛ ቋንቋን ስነ ጽሑፍን ተጠቅሞ ማስተማር ውጤታማ መሆን አለመሆኑን በሙከራ ለማረጋገጥ መነሳቱ ያመሳስለዋል፡፡

የዘመንፈስ ጥናት ምንም እንኳ ከዚህ ጥናት ጋር የሚመሳሰሉባቸው ጉዳዮች ቢኖሩም ጉልህ ልዩነቶችም አሉት፡፡ ከልዩነቶቹ መካከል አንደኛው የዘመንፈስ ጥናት በምንጭነት የተጠቀመው አጭር ልቦለድን ሲሆን ይህ ጥናት ግን ግጥምንና አጭር ልቦለድን ይሆናል፡፡ እንደዚሁም የዘመንፈስ ጥናት አጭር ልቦለድ አማርኛ ቋንቋን ለማስተማር ያለውን ሚና ለማረጋገጥ ታስቦ የተካሄደ ሲሆን ይህ ጥናት ግን ግጥምና አጭር ልቦለድ የአማርኛ ቋንቋ አንብቦ መረዳት ክሂልን ለማሳደግ ያለውን ሚና በሙከራ ለማረጋገጥ የሚደረግ ይሆናል፡፡ በመረጃ መተንተኛነት የሚጠቀመውም መጠናዊ ዘዴን ይሆናል፡፡ ከዚህ ባሻገር የዘመንፈስ ጥናት በ11ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ የተሞከረ ሲሆን ይህ ጥናት ግን በ10ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ የሚሞከር ነው፡፡ ከቦታና ከዘመን አንጻርም ልዩነቶች አሉት፡፡ የዘመንፈስ ጥናት በ1991 ዓ.ም በአዲስ አበባ የካቲት 12 ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ላይ የተካሄደ ሲሆን ይህ ጥናት ግን በ2015 ዓ.ም በሻምቡ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ላይ ይካሄዳል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ዘመንፈስ በ1991 የነበረውን መማሪያ መፅሀፍት የተጠቀመ ሲሆን አጥኚው ምርምር ሊያደርግ ያሰበው የክፍል ደረጃ መማሪያ መፅሀፍት ደግሞ በ2004 ዓ.ም የታተመውን ነው፡፡ ሌላው ጉልህ ልዮነት ዘመንፈስ የተጠቀመው የስነፅሁፍ ዘርፍ አንደኛውን ለብቻ ሲሆን ይሄ ደግሞ የሚጠቀመው ሁለቱን የስነ-ፅሁፍ ዘርፎች በጣምራ መሆኑ ይሆናል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ይህ ጥናት ትኩረት አድርጎ

የተነሳው ስነፅሁፍና ኢስነፅሁፋዊ ፅሁፎች የአማርኛ ቋንቋን የማንበብ ክሂልን በተመለከተ ይሆናል፤ የዘመንፈስ ግን ስነፅሁፍን ብቻ የሚያይ ነው፡፡

ሌላው **የክንፈሚካኤል** (1995) ጥናት ነው፡፡ የጥናቱ ርዕስ ‹‹ስነ ጽሑፋዊ ይዘቶች የተማሪዎችን የቋንቋ ክሂልና የስነ ጽሑፍ እውቀት ለማሳደግ ያላቸው እገዛ በ1993ና በ1994 ዓ.ም ለ10ኛ እና 11ኛ ክፍል መማሪያነት በተግባር ላይ በዋሉ መጻህፍት›› የሚል ነበር፡፡ የጥናቱ ዋነኛ አላማ በተጠቀሱት መጻህፍት ውስጥ የተካተቱት ስነ ጽሑፋዊ ይዘቶች የቋንቋ ክሂሎችንና የስነ ጽሑፍ እውቀትን ለማዳበር ያላቸውን ውጤታማነት መፈተሸ ነበር፡፡ ለጥናቱ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች በሰነድ ፍተሻና በጽሑፍ መጠይቅ ተሰብስበዋል፡፡ በጥናቱ መጨረሻ የተገኘው ውጤት እንደሚያመለክተው አራቱን ክሂሎች በማሳደግ ረገድ የስነ ጽሑፍ ይዘቶች የጎላ ጠቀሜታ አላቸው፡፡

የክንፈሚካኤል ጥናት ከዚህ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው የተለያዩ ስነ ጽሑፋዊ ጽንሰ ሀሳቦችን ያካተተ መሆኑ ይሆናል፡፡ የሚለየው ደግሞ የክንፈሚካኤል ጥናት በተጠቀሱት መጻሕፍት ውስጥ የተካተቱትን ሁሉንም የስነ ጽሑፍ ዘሮች የሚመለከት መሆኑ ይሆናል፡፡ ይህ ጥናት ግን ግጥምና አጭር ልቦለድ የአማርኛ ቋንቋን በማስተማር ረገድ ለአንብቦ መረዳት ያለውን ሚና በሙከራ ለማረጋገጥ የሚካሄድ ይሆናል፡፡

በሶስተኛ ደረጃ የሚጠቀሰው ጥናት የጌትነት ታፈረ(1998) ጥናት ነው፡፡ የጌትነት ጥናት ‹‹ልቦለድን በመጠቀም በክፍል ውስጥ የአንብቦ መረዳት ትምህርት አቀራረብ ፍተሻ›› የሚል ርዕስ ያለው ነበር፡፡ ዋነኛ አላማው መምህራን ልቦለድን ተጠቅመው የአንብቦ መረዳት ትምህርትን ሲያስተምሩ የአቀራረብ ሁኔታቸውን መፈተሸ ነበር፡፡ ጥናቱ በቪዲዮ የታገዘ ምልከታን፣ የጽሑፍ መጠይቅንና ቃለ መጠይቅን በመረጃ መሰብሰቢያነት ተጠቅሟል፡፡ በዚህ መሰረት የተገኘው ውጤት እንደሚጠቁመው መምህራኑ የአንብቦ መረዳት ትምህርት አቀራረብ ደረጃዎችን ባግባቡ እንደማይጠቀሙና የአንብቦ መረዳት የማስተማሪያ ስልቶችን በብቃት እንደማይተገብሩ መረዳት ተችሏል፡፡

የጌትነት (1998) ጥናት ከዚህ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው ስነ ጽሑፍ በቋንቋ ትምህርት ረገድ የሚያበረክታቸውን ጽንሰ ሀሳባዊ ማብራሪያዎች በማካተቱ ይሆናል፡፡ የሚለየው ደግሞ የጌትነት ጥናት ልቦለድን በመጠቀም የክፍል ውስጥ የአንብቦ መረዳት ትምህርት አቀራረብን ለመፈተሸ የተደረገ በመሆኑ ይሆናል፡፡ ይህ ጥናት ደግሞ ስነፅሁፍና ኢስነፅሁፋዊ ፅሁፎች የአማርኛ ቋንቋን የማንበብ ክሂልን በማስተማር ረገድ ያለውን ሚና በሙከራ ለማረጋገጥ አልሞ የተነሳ

ይሆናል፡፡ በተጨማሪም ይህ ጥናት ከሁለቱ ስነ-ጽሁፋዊ ስራዎች የትኛው ይበልጥ ለአንብቦ መረዳት ክሂል የተሻለ መሆኑን በሙከራ ማረጋገጥ ነው፡፡

ሌላው ጥናት የዳዊት (2000) ጥናት ነው፡፡ ጥናቱ ‹‹በቤኒሻንጉል ጉሙዝና በጋምቤላ ክልሎች ለመጀመሪያ ደረጃ ሁለተኛ እርከን (7ኛና 8ኛ ክፍል) ተማሪዎች በተዘጋጁ የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የተካተቱ ስነ ጽሑፋዊ ስራዎች አመራረጥና አደረጃጀት›› የሚል ርዕስ አለው፡፡ የጥናቱ ዋነኛ አላማ በተጠቀሱት ክልሎች ለ7ኛ ና 8ኛ ክፍል ተማሪዎች በተዘጋጁ የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የሰፈሩት የስነ ጽሑፍ ስራዎች እንዴት እንደተመረጡና እንደተደራጁ መመርመር ነበር፡፡ ጥናቱ የሰነድ ፍተሻን፣ የጽሑፍ መጠይቅን እና ቃለ መጠይቅን በመረጃ መሰብሰቢያነት ተጠቅሟል፡፡ በዚህ መሰረት የጥናቱ ውጤት እንደሚያመለክተው የተመረጡት ብዙዎቹ ስነ ጽሑፋዊ ይዘቶች የርዝማኔ ችግር የሚስተዋልባቸው፣ የተማሪዎችን እድሜ ያላገናዘቡ፣ ከቀላል ወደ ከባድ ያልተደራጁ፣ ተከታታይነትና ተለጣጣቂነት የሌላቸው ወዘተ. ሆነው ተገኝተዋል፡፡

የዳዊት ጥናት ከዚህ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው እንደሌሎቹ ሁሉ ስነ ጽሑፋዊ ጽንሰ ሀሳቦችን ማንሳቱ ወይም ስነ ጽሑፍ ላይ ማተኮሩ ነው፡፡ የዳዊት ጥናት በመጻሕፍት ውስጥ የተካተቱ ስነ ጽሑፋዊ ይዘቶችን እንዴት እንደተመረጡና እንደተደራጁ ለመፈተሽ የተደረገ ሲሆን ይህ ጥናት ግን ስነፅሁፍና ኢስነፅሁፋዊ ፅሁፎች የአማርኛ ቋንቋን የማንበብ ክሂልን በማስተማር ረገድ ያላቸውን ሚና በሙከራ ለማረጋገጥ አልሞ የተነሳ ይሆናል፡፡

ሌላው የጌትነት አዲስ (2001) ጥናት ነው፡፡ የጥናቱ ርዕስ ‹‹ በረጅም ልቦለድ ቅንጫቢ አማርኛ ቋንቋን ማስተማር ያለው ውጤታማነት በተመረጠ አንድ የምስራቅ ጎጃም ዞን ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት በ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ የተካሄደ ጥናት›› የሚል ነው፡፡ የጥናቱ አብይ አላማ በረጅም ልቦለድ ቅንጫቢ አማካይነት በፈጠራዊ ዘዴ አማርኛ ቋንቋን ማስተማር ጽሕፈትን፣አንብቦ መረዳትን፣ የቃላት ፍቺ መለየትን፣ ዐ.ነገሮችን በሌላ አባባል መጻፍን፣ በአያያዥ ቃላት ባዶ ቦታዎችን መሙላትን ወዘተ. ለማስተማር ያለውን ውጤታማነትና ተተግባሪነት በሙከራ ማረጋገጥ ነበር፡፡ ጥናቱ የቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተናንና የጽሑፍ መጠይቅን በመረጃ መሰብሰቢያነት ተጠቅሟል፡፡ መጠናዊ የምርምር ዘዴንም በመተንተኛ ዘዴነት ተጠቅሟል፡፡ በዚህ መሰረት የጥናቱ ውጤት እንደሚጠቁመው በስነ ጽሑፍ (ረጅም ልቦለድ) አማካይነት የአማርኛ ቋንቋን ማስተማር ውጤታማ ነበር፡፡

የጌትነት (2001) ጥናት ከዚህ ጥናት ጋር የሚመሳሰለው ስነ ጽሑፍን ተጠቅሞ አማርኛ ቋንቋን ማስተማር ውጤታማ መሆን አለመሆኑን በሙከራ ለማረጋገጥ አልሞ መነሳቱና በ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ ማተኮሩ ነበር፡፡

የጌትነት (2001) ጥናት ከዚህ በላይ በተጠቀሱት ነጥቦች ከዚህ ጥናት ጋር የሚመሳሰል ቢሆንም ልዩነቶችም ግን አሉት፡፡ ከነዚህ መካከል አንደኛው የጌትነት ጥናት ረጅም ልቦለድን በምንጭነት የተጠቀመ ሲሆን ይህ ጥናት ግን ስነፅሁፍና ኢስነፅሁፋዊ ፅሁፎች የአማርኛ ቋንቋን የማንበብ ክሂልን በማስተማር ረገድ ያለውን ሚና በሙከራ ለማረጋገጥ አልሞ የተነሳ ይሆናል፡፡ ከዚህ ባሻገር የጌትነትጥናት በመረጃ መተንተኛነት የተጠቀመው መጠናዊ ዘዴን ሲሆን ይህ ጥናት ግን ከመጠናዊ ዘዴ በተጨማሪ አይነታዊ ዘዴንም ይጠቀማል፡፡ እንዲሁም ጥናቶቹ ከተከናዎኑበት ጊዜና ቦታ አንጻርም ልዩነት አላቸው፡፡ የጌትነት ጥናት በ2001 በጎጃም በር ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ላይ የተካሄደ ሲሆን ይህ ግን በ2015 በሻምቡ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ት/ቤት ላይ የሚደረግ ይሆናል፡፡

# ምዕራፍ ሶስት
# 3. የጥናቱ ዘዴ

## 3.1. የጥናቱ ንድፍ

የጥናቱ ዓላማ ስነፅሁዊና ኢ-ስነፅሁፋዊ ፅሁፎች የአማርኛ ቋንቋ የአንብቦ መረዳት ክሂልን በማሻሻል ረገድ ያላቸውን ሚና መመርመር ነው፡፡ ይህ ጥናት በአይነቱ መጠናዊ ሲሆን የሚከተለው የአጠናን ንድፍ ከፊል ሙከራዊ በመሆኑ የሁለት ተጠኝ ቡድኖች የቅድመና ድህረ ፈተና በመፈተን የሚመረምር ነው፡፡ ሁለቱ ተጠኝ ቡድኖች ምንም ሳይማሩና በተለያዩ ምንባቦች ከተማሩ በኋላ በሚያስመዘግቧቸው የፈተና ውጤቶች አማካይነት ያሳዩትን የአንብቦ መረዳት ክሂል ልዩነት ተመርምሯል፡፡

## 3.2. የናሙና አመራረጥ

### 3.2.1. የትምርት ቤት አመራጥ

ይህንን ከፊል ሙከራዊ ጥናት ለማድረግ ደግሞ ሰፊ ጊዜ ይጠይቃል፡፡ በመሆኑም የሚመረጠዉ ትምህርት ቤት የሻምቡ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ነው፡፡ በመሆኑም አጥኚው ይህንን ጥናት ለማካሄድ ትምህርት ቤቱ የተመረጠው በአመች ናሙና ዘዴ ነዉ፡፡ ምክንያቱም አጥኚው ጥናቱን ለማካሄድ ባሰበበት ትምህርት ቤት በመማር ማስተማር ሂደቱ ላይ የሚገኝ በመሆኑና ጥናቱን ለማካሄድ ከገንዘብ፣ ከጉልበትና ከጊዜ አንፃር ያለውን ሁኔታ መነሻ በማድረግ አመቺ ስለሚሆንለት ነው፡፡

### 3.2.2. የተማሪዎች አመራረጥ

ለዚህ ጥናት የተመረጡት ተማሪዎች በሻምቡ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ውስጥ የሚማሩ የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች ሲሆኑ በአላማ ተኮር አመራረጥ ዘዴ ተመርጠዋል፡፡ የተመረጡበት ምክንያትም አጥኝው ለዚህ ጥናት መረጃ ለመሰብሰብ ባሰበበት ጊዜ ከቦታው ቅርበትና ከተማሪዎቹ ጋር ካለው የቅርብ ግንኑነት አንፃር እንዲሁም በትምህርት ሰዓት የተገኙ ምቹ አጋጣሚዎችንም ለዚህ ጥናት ለማዋል ስለሚታመን ነዉ፡፡ ከዚህ ባሻገር 10ኛ ክፍል የ2ኛ ደረጃ ትምህርት የሚሰጥበት በመሆኑ፣ ችግሮች ካሉ ከስሩ ጀምሮ ለመፍታትና ለቀጣዮቹ የክፍል ደረጃዎች ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር የሚያስችል ስለሚሆን ነዉ፡፡ ከነዚህ 915 ተማሪዎች ዉስጥ በቀላል የዕጣ ናሙና ዘዴ መሰረት ሁለት ተጠኝ ክፍሎች ማለትም 10E እና 10M ወንድ45 ሴት 57 በድምሩ 102 ተማሪዎች የተመረጡበትም ምክንያት ለአጥኚው በቀላሉ ማግኘት ስለሚያስችል ነው፡፡ እነዚህ የተመረጡ ክፍሎች በጥናቱ ተሳታፊ ሆነዋል፡፡ በመሆኑም አጥኚው በተጠኝነት የተመረጡትን ክፍሎች ይዞ በስነፅሁፋዊ ፅሁፍ 51 እና በኢ-ስነፅሁፋዊ ፅሁፍ 51 ተማሪዎች አማካይነት ለማስተማር ክፍለ ጊዜ በመያዝ ተግባራዊ አድርጓል፡፡

## 3.3. የማስተማሪያ ፅሁፍ ዝግጅት

ለዚህ ጥናት ለማስተማሪያነት አጥኚው የተጠቀመው የማስተማሪያ ውህዶች የስነፅሁፋዊና የኢ-ስነፅሁፋዊ ናቸው፡፡ ለሁለቱ ቡድኖች የማስተማሪያ ውሁድ አሀዶቹ የሚዘጋጁት የ10ኛ ክፍል የአማርኛ የመማሪያ መጽሐፉንና የተማሪዎችን ደረጃ ከግምት ውስጥ በማስገባት ሲሆን ለስነፅሁፋዊ ተማሪዎች የአጭር ልቦለድ ፅሁፎች ባካተተ መልኩ ነው፡፡ ሌላው በኢ-ስነፅሁፋዊ ፅሁፎች ለሚማሩ ተማሪዎች ደግሞ የማስተማሪያ ውሁድ አሀዶቹ የሚዘጋጁት የአማርኛ የመማሪያ መጽሐፉንና የተማሪዎችን ደረጃ ከግምት ውስጥ በማስገባት መረጃ ሰጪ፣ የህይወት ታሪኮችን፣ አስረጅ ፅሁፎችንና የመሳሰሉትን ኢስነፅሁፋዊ ፅሁፎችን ባካተተ መልኩ ነው፡፡

ጥናቱን ለማኬድ ተማሪዎች የቅድመ ትምህርት ፈተናውን ከተፈተኑ በኋላ ተሳታፊ ቡድኖችን በስነጽሁፋዊና በኢ-ስነጽሁፋዊ ጽሁፎች የሚማሩ ተማሪዎችን በመለየት የማንበብ ክሂላቸውን ለማስተማር ምንባቦች ከተለያዩ ማስተማሪያና አጋዥ መፅሀፎች እንዲመጥኑ ተደርገው በአጥኚው ተዘጋጅተዋል፡፡ ለዚህም የቀድሞው የ9ነኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ የተማሪው መፅሀፍ፣ፍቅረማርቆስ ደስታ ከቡስካ በስተጀርባ እና ኪሲነር ፣2009፣ትምህርት ሚኒስቴርን 1992 ለማስተማሪያነት ተጠቅሟል፡፡

የተዘጋጁትን የማስማሪያ ምንባቦች ለተለያዩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ለክፍል ደረጃው መመጠን አለመመጠናቸዉን አስተያየት እንዲሰጡባቸዉ ማድረግና አስተያየቶችን በመቀበል በተሰጡት አስተያየቶች መሠረት እንደገና ተሻሽለው እንዲዘጋጁ ተደርጓል፡፡ በመጨረሻም በተማሪዎቹ ቁጥር ልክ ተራብተው ለእያንዳንዱ ተማሪ በነፍስ ወከፍ ተሰጥቷል፡፡ ጥናቱን ከግብ ለማድረስም የጥናቱ ተሳታፊዎች የሚማሩበትን መደበኛ ክ/ጊዜ በአግባቡ በመጠቀም በሳምንት ሁለት ክፍለ ጊዜ በማስተማር፣ ለማስተማሪያነት የተዘጋጁትን ምንባቦች በመጠቀምና በተጨማሪም የተለያዩ ምንባቦችን እንዲያነቡ ማለትም ከልቦለድ፣ እንዲሁም ከጋዜጦች፣ መጽሄቶች ወዘተ ምንባቦችን እንዲያነቡ ጥቆማዎችን በመስጠት ከመደበኛው መማር ማስተማር ተጨማሪ ግንዛቤን በመፍጠርና በሳምንት ሁለት ቀናት በቀን ለ40 ደቂቃ፣ ለስድስት ሳምንት ያህል እንዲማሩ ተደርጓል፡፡

ተዘጋጅቶ የቀረበው ምንባብ ተማሪዎች አንብበው የተረዱትን ሃሳብ በቃልና በጽሁፍ ምላሽ የሚሰጡበት ሆኖ የአንብቦ መረዳት ክሂላቸውን የሚያጐለብቱበትን ተግባራት የያዘ ሲሆን የንባብ ተግባራትን /ቅድመ ንባብ፣ በንባብ ጊዜ/ በማስታወስ የሚመለሱ ጥያቄዎች፣ ከምንባብ ውስጥ ዋና ዋና ሃሳብን መለየት፣ ከምንባቡ የወጡ ቃላትን ተመሳሳይና ተቃራኒ መስጠት፣ የምንባብን ሃሳብ ማሳጠር፣ በተለያዩ ነገሮች መካከል ያለ ተመሳስሎን ማውጣት፣ ከምንባብ

ውስጥ ዋና ሃሳብን ማውጣት፣ አንብቦ የመረዳት ተግባራትን ለማከናወን ያስችል ዘንድ ተዘጋጅቷል፡፡

## 3.4 የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ

ለዚህ ጥናት አስፈላጊ የሚሆኑ መረጃዎችን ለመሰብሰብ የሚያስፈልጉ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች የአንብቦ መረዳት ፈተና እና የፅሁፍ መጠይቅ ናቸው፡፡ እነዚህ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች የሚመረጡት የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ችሎታን ለመለየት የተሻሉ ስልቶች ስለሚሆኑ ነዉ፡፡ አፈፃፀሙም በሁለት ዙር የሚከናወን ሲሆን ይኸዉም ቅድመ-ፈተና (pre test) እና ድህረ-ፈተና (post test) ነው፡፡

### 3.4.1 ፈተና

**ቅድመ-ፈተና** (pre test):-የዚህ ፈተና አላማ ተማሪዎች ልምምዱን ከመጀመራቸዉ በፊት የአላቸዉን ቅድመ የአንብቦ መረዳት ችሎታ ለመፈተሽ ሲሆን የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች ለሁለቱም ተጠኝዎች ቡድን አስራ አምስት ጥያቄዎችን የያዙ ምንባቦች ተዘጋጅተዋል፡፡ እነዚህ ጥያቄዎች ተማሪዎች እንዲፈተኑ ከተደረገ በኂላ ዉጤቱን መዝግቦ በመያዝ ወደ ትምህርቱ ተገብቷል፡፡

**ድህረ-ፈተና** (post test):- የዚህ ፈተና አላማ ሁለቱ ተጠኝ ቡድኖች በአዲሱ ዘዴ ከተማሩ በኂላ በተማሪዎች መካከል ያለዉን የአንብቦ መረዳት ችሎታ ልዩነት ለማየትና ከቅድመ-ፈተና ዉጤታቸዉ ጋር ያለዉን ልዩነት ለመገምገም ነው፡፡ ፈተናው የክፍል ደረጃዉን መሰረት አድርጎ ተዘጋጅቷል፡፡ የሚዘጋጀዉ ፈተና ከዚህ በፊት በቅድመ-ፈተናዉ ያልቀረበና አዲስ ሆኖ ለሁለቱም ቡድኖች አስራ አምስት ጥያቄዎች የያዘ ንባብ ተዘጋጅቷል፡፡ ጥያቄዎችም በአይነታቸዉ ዝግ (close-ended) ሆነዉ የተዘጋጁ ሲሆን አስፈላጊነቱም የተለያየ ጥያቄ ማዘጋጀት ጥቅሙ በአንድ አይነት ትዕዛዝ በቀረበ ጥያቄ ተማሪን መመዘን ስለማይቻልና ጥናቱን ተአማኒነት ስለሚያሳጣው ነው፡፡

የሁለቱም ተጠኚ ቡድኖች የፈተና ይዘቶች የሚዘጋጁት አጠቃላይ የንባብ ሃሳብን፣ከንባብ የወጡ ዝርዝር ሀሳቦችንና የቃላት አዉዳዊ ፍችን ባካተተ መልኩ ነው፡፡

### 3.4.2 የፅሁፍ መጠይቅ

የፅሁፍ መጠይቅ ሁለተኛዉ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ነዉ ፡፡ አላማዉም ተማሪዎች ስለ አንብቦ መረዳት በአዲሱ ዘዴ ከመማራቸዉ በፊትና ከተማሩ በኂላ ያላቸዉን የንባብ ችሎታ ለማነፃፀር ነዉ፡፡ እነዚህም የፅሁፍ መጠይቆች ትኩረትም ተማሪዎች ለንባብ ያላቸዉን ችሎታ ለመግለፅ የሚያስችሉ ይሆናሉ፡፡

### 3.5 የመረጃ መተንተኛ ዘዴ

በቅድመ- ትምህርትና በድህረ-ትምህርት በፈተና እና በፅሁፍ መጠይቅ የተሰበሰቡት የጥናቱ መረጃዎች በአግባቡ ተደራጅተዉ የማጣራት ስራ ከተሰራ በኋላ የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ችሎታ ለመለካትና ያላቸዉን ችሎታ ለመፈተሽ በቅድመ-ትምህርት እና በድህረ-ትምህርት ፈተና እና የፅሁፍ መጠይቅ የተገኙ ዉጤቶችን ለማነፃፀር ዳግም ልኬት ቲ-ቴስት (Repeated measures t-test) እና በነፃ ናሙና ቲ-ቴስት(Independant sample t-test) ቀመር አማካኝነት ተሰርቷል።

# ምዕራፍ አራት

# 4. የውጤት ትንተናና ማብራሪያ

## 4.1. የውጤት ትንተና

ለዚህ ጥናት የተመረጡት ተማሪዎች በሻምቡ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ውስጥ የሚማሩ የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች ሲሆኑ በአላማ ተኮር አመራረጥ ዘዴ ተመርጠዋል፡፡ የተመረጡበት ምክንያትም አጥኚው ለዚህ ጥናት መረጃ ለመሰብሰብ ባሰበበት ጊዜ ከቦታው ቅርበትና ከተማሪዎቹ ጋር ካለው የቅርብ ግንኙነት አንፃር እንዲሁም በትምህርት ሰዓት የተገኙ ምቹ አጋጣሚዎችንም ለዚህ ጥናት ለማዋል ስለሚታመን ነዉ፡፡ ከዚህ ባሻግር 10ኛ ክፍል የ2ኛ ደረጃ ትምህርት የሚሰጥበት በመሆኑ፣ ችግሮች ካሉ ከስሩ ጀምሮ ለመፍታትና ለቀጣዮቹ የክፍል ደረጃዎች ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር የሚያስችል ስለሚሆን ነዉ፡፡ ከነዚህ 915 ተማሪዎች ዉስጥ በቀላል የዕጣ ናሙና ዘዴ መሰረት ሁለት ተጠኝ ክፍሎች ማለትም 10E እና 10M ወንድ45 ሴት 57 በድምሩ 102 ተማሪዎች የተመረጡበትም ምክንያት ለአጥኚው በቀላሉ ማግኘት ስለሚያስችል ነው፡፡ እነዚህ የተመረጡ ክፍሎች በጥናቱ ተሳታፊ ሆነዋል፡፡ በመሆኑም አጥኚው በተጠኝነት የተመረጡትን ክፍሎች ይዞ በስነፅሁፋዊ ፅሁፍ 51 እና በኢ-ስነፅሁፋዊ ፅሁፍ 51 ተማሪዎችን በማስተማር ክፍለ ጊዜ በመያዝ ተግባራዊ አድርጓል፡፡ ጥናቱ አላማ አድርጎ የተነሳው ስነፅሁፋዊና ኢስነፅሁፋዊ ፅሁፎች የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ክሂል ከማሻሻል ረገድ ያለቸውን ሚና መመርመር ነው፡፡

ይህን ለማሳካት በፈተናና በፅሁፍ መጠይቅ በተሰበሰቡት መረጃዎች ከስነፅሁፋዊ እና ከኢስነፅሁፋዊ ፅሁፎች የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ክሂል ከማሻሻል ረገድ የበለጠ አስታዋፅኦ ያለዉ የትኛዉ ነዉ? ከስነፅሁፋዊና ኢ-ስነፅሁፋዊ ፅሁፎች የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ክሂል ተነሳሽነት ለማጎልበት የበለጠ አስተዋፅኦ ያለው የትኛዉ ነዉ? የሚሉት መሠረታዊ የምርምሩ ጥያቄዎች ተተንትነዋል፡፡

የጥናቱ የመጀመሪያ ትንተና የተደረገው ተማሪዎቹን በየትኛው የምንባብ ይዘት መማር እንዳለባቸው ለመምረጥ ከስነፅሁፋዊና ኢ-ስነፅሁፋዊ ፅሁፎች በተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ክሂል ላይ ልዮነት መኖሩን መገንዘብ ነው፡፡ ይሄውም በቅድመ ትምህርት የተገኘው ውጤት ተቀራራቢ መሆኑን ተተንትኗል፡፡ ለዚህም በፈተና የተገኘው መረጃ ትንተና በገላጭ ስታስቲክስና በባዕድ ናሙና ልኬት ቲ-ቴስት (Independant sample t test) ተሰልቷል፡፡

የመረጃ ትንተና ውጤቱም በሁለቱ መሠረታዊ ጥቄዎች አንፃር እንደሚከተለው በ12 ሠንጠረዦች ቀርቧል፡፡ የመጀመሪያው መሪ ጥያቂ -ከስነፅሁፋዊና ከኢስነፅሁፋዊ ፅሁፎች በተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታ ላይ የበለጠ ፋይዳ ያለውን መመርመር፡የሚል ሲሆን በሰንጠረዥ 4.1 የተመለከተውን ይመስላል፡፡

**ሠንጠረዥ4.1፡- የስነ-ጽሁፋዊና ኢስነ-ጽሁፋዊ ቡድኖች የቅድመ ትምህርት የአንብቦ መረዳት ክሂል ፈተና ውጤት በነፃ ናሙና** (independent sample t-test) **ቲ-ቴስት ትንተና**

| ቡድን | ፈተና | ናሙና | አማካይ ውጤት | መደበኛ ልይይት | መደበኛስ ህተት | የቲዋጋ | የነፃነት ደረጃ | የ"p"ዋጋSig. |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የስነፅሑፍ | ቅድመ | 51 | 7.41 | 1.226 | .352 | 2.265 | 100 | .026 |
| የኢስነ ፅሁፍ | ቅድመ | 51 | 7.31 | 1.257 | .176 | 2.265 | 100 | .027 |

የሚጠበቀው አማካይ ውጤት (Expected mean $\geq$ 10),(p $\leq$ 0.05)

በሠንጠረዥ አንድ እንደተመለከተው የስነ-ጽሁፍ ቡድን የቅድመ ትምህርት የአንብቦ መረዳት ክሂል ፈተና አማካይ ውጤት (7.41) ሲሆን የኢስነ-ጽሁፍ ቡድን የቅድመ ትምህርት የአንብቦ መረዳት ክሂል ፈተና አማካይ ውጤት (7.31) ነዉ፡፡በመሆኑም የስነ-ጽሁፍ ቡድን የአንብቦ መረዳት ክሂል ፈተና ዉጤት ከኢስነ-ፅሁፍ ቡድን የአንብቦ መረዳት ክሂል ፈተና ዉጤት ተቀራራቢ ሆኖ ተገኝቷል ፡፡ ይህም የቅድመ ትምህርት የስነ ፅሁፍና ኢስነፅሁፍ ቡድኖች ከሚጠበቀው አማካይ ውጤት ከ(10) በታች ሆኖ ተገኝቷል፡፡

እንዲሁም የስነ-ጽሁፍ ቡድን ተማሪዎች የቅድመ ትምህርት የአንብቦ መረዳት ክሂል ፈተና መደበኛ ልይይት (1.226) ሲሆን የኢስነ-ፅሁፍ ቡድን ተማሪዎች የቅድመ ትምህርት የአንብቦ መረዳት ክሂል ፈተና መደበኛ ልይይት ደግሞ (1.257) ነዉ፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ የሁለቱም ቡድኖች የቲ -ዋጋ 2.265 በ (100 የነፃነት ደረጃ፤p $\leq$0.05) መሆኑን ትንተናው ያሳያል፡፡ ይህም ሁለቱ ቡድኖች በተለያዩ ዘዴዎች ከመማራቸዉ በፊት የአንብቦ መረዳት ክሂል ችሎታቸዉ መሰረታዊ ልዩነት እንደሌላቸዉ ያሳያል፡፡

**ሠንጠረዥ 4.2፡- የስነ-ጽሁፋዊና ኢስነ-ጽሁፋዊ ቡድኖች የድህረ ትምህርት የአንብቦ መረዳት ክሂል ፈተና ውጤት በነፃ ናሙና** (independent sample t-test) **ቲ-ቴስት ትንተና**

| ቡድን | ፈተና | ናሙና | አማካይ ውጤት | መደበኛ ልይይት | መደበኛ ስህተት | የቲ-ዋጋ | የነፃነት ደረጃ | የ"p"ዋጋ Sig."" |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ስነጽሁፍ | ድህረ | 51 | 15.53 | 3.246 | .454 | 11.464 | 100 | .000 |
| ኢስነጽሁፍ | ድህረ | 51 | 7.82 | 3.537 | .495 | 11.464 | 100 | .000 |

የሚጠበቀው አማካይ ውጤት (Expected mean $\geq$ 10 ), ( $p \leq 0.05$)

የስነ ፅሁፍና የኢስነጽሁፍ ቡድኖችን የድህረ ፈተና ትንተና ስንመለከት፤ የስነ-ጽሁፍ ቡድን የድህረ ትምህርት የአንብቦ መረዳት ክሂል ፈተና አማካይ ውጤት (15.53) ሲሆን የኢስነ-ጽሁፍ ቡድን (7.82)፣ የስነ ጽሁፍ ቡድን መደበኛ ልይይት 3.246፣ የኢስነጽሁፍ 3.537 መሆኑን ትንተናው ሲያሳይ የስነጽሁፍ ቡድኑ አማካይ ውጤት ከሚጠበቀው አማካይ ውጤት $\geq$ 10 ) በላይ ፣የኢስነጽሁፍ ቡድኑ ደግሞ ከሚጠበቀው አማካይ በታች መሆኑን (በቲ-ዋጋ 11.464፣በነፃነት ደረጃ 100፣ $p \leq 0.05$) መሆኑን አመልክቷል።

ይህም የስነጽሁፍ ቡድኑ ከኢስነ ጽሁፍ ቡድኑ የድህረ ትምህርት የአንብቦ መረዳት ክሂል ፈተና በ (7.71) በልጦ ከፍተኛ ልዩነት አሳይቷል።

**ሠንጠረዥ 4.3. የስነ ጽሁፍ ቡድን ቅድመና ድህረ ትምህርት የአንብቦ መረዳት ክሂል ፈተና ውጤት የነፃ ናሙና ቲ-ቴስት ትንተና**

| ቡድን | ፈተና | ናሙና | አማካይ ውጤት | መደበኛ ልይይት | መደበኛ ስህተት | የቲ-ዋጋ | የነፃነት ደረጃ | የ"p"ዋጋ Sig. |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ስነጽሁፍ | ቅድመ | 51 | 7.41 | 1.226 | .352 | 2.265 | 50 | .026 |
| | ድህረ | 51 | 15.53 | 3.246 | .454 | 11.464 | 50 | .000 |

የሚጠበቀው አማካይ ውጤት (Expected mean $\geq$ 10), ($p \leq 0.05$)

በሠንጠረዡ እንደተመለከተዉ በስነ-ፅሁፍ ቡድን በቅድመ ትምህርቱ ፈተና **የነፃ ናሙና** ቲ-ቴስት ትንተናው እንዳሳየው፤የስነጽሁፍ ቡድን አማካይ ውጤት(7.41)፣መደበኛ ልይይት(1.226)፤ ሆኖ ሲገኝ በድሀረ ፈተናው ደግሞ አማካይ ውጤት(15.53)፣መደበኛ

ልይይት(3.246)፤ሆኖ ተገኝቷል፡፡ የቅድመ ፈተናው ከሚጠበቀው አማካይ ውጤት≥ 10 ) በታች ሲሆን የድህረ ፈተናው ውጤት ደግሞ ከሚጠበቀው አማካይ ውጤት በላይ መሆኑን የቲዋጋ 2.265 እና 11.464 ፤በ50 የነፃነት ደረጃ፣ $p \leq 0.05$) መሆኑን ተመላክቷል፡፡ይህም በቅድመና በድህረ ትምህርት ፈተናዎች መካከል በ8.12 የድህረ ትምህርት አንብቦ መረዳት ክሂል ፈተናው በልጦ ተገኝቷል፡፡

**ሠንጠረዥ4.4. የኢስነ ጽሁፍ ቡድን ቅድመና ድህረ ትምህርት የአንብቦ መረዳት ክሂል ፈተና ውጤት የነፃ ናሙና ቲ-ቴስት ትንተና**

| ቡድን | ፈተና | ናሙና | አማካይ ውጤት | መደበኛ ልይይት | መደበኛ ስህተት | የቲ-ዋጋ | የነፃነት ደረጃ | የ"p"ዋጋ Sig. |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የኢስነ ጽሁፍ ቡድን | ቅድመ | 51 | 7.31 | 1.257 | .176 | 2.265 | 100 | .027 |
| | ድህረ | 51 | 7.82 | 3.537 | .495 | 11.464 | 100 | .000 |

የሚጠበቀው አማካይ ውጤት (Expected mean ≥ 10), ($p \leq 0.05$)

**ሠንጠረዥ 4.4.** የኢስነ ጽሁፍ ቡድን ቅድመና ድህረ ትምህርት የአንብቦ መረዳት ክሂል ፈተና ውጤት የነፃ ናሙና ቲ-ቴስት ትንተና ሲሆን በትንተናው እንደተመለከተው የቅድመ ትምህርት የአንብቦ መረዳት ክሂል ፈተና አማካይ ውጤት 7.31፣ሲሆን መደበኛ ልይይቱ 1.257 ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በአንፃሩ የድህረ ትምህርቱ የአንብቦ መረዳት ክሂል ፈተና አማካይ ውጤት 7.82፣መደበኛ ልይይቱ ደግሞ 3.537 ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በቅድመና ድህረ አማካይ ውጤት መካከል ያለው ልዩነት ሲታይ በ0.51 የድህረ ትምህርት የአንብቦ መረዳት ክሂል ፈተና አማካይ ውጤት በልጦ ቢገኝም ከሚጠበቀው አማካይ ውጤት (≥ 10) በታች ሆኖ መገኘቱን ትንተናው አሳይቷል፡፡ ይህም የሚያሳየው በድህረና ቅደመ መካከል ልዩነት እንዳለው ነው፡፡

**ሠንጠረዥ4.5. የስነ ጽሁፍ ቡድን ቅድመና ድህረ ትምህርት የአንብቦ መረዳት ክሂል ፈተና ውጤት የዳግም ልኬት ቲ-ቴስት ትንተና**

| ቡድን | ፈተና | ናሙና | አማካይ ውጤት | መደበኛ ልይይት | መደበኛ ስህተት | የቲ-ዋጋ | የነፃነት ደረጃ | የ"p"ዋጋ Sig. |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ስነጽሁፍ | ቅድመ | 51 | 7.12 | 2.536 | .435 | 12.936 | 50 | .000 |
| | ድህረ | 51 | 15.53 | 3.246 | .454 | 27.569 | 50 | .000 |

የሚጠበቀው አማካይ ውጤት (Expected mean ≥ 10), ($p \leq 0.05$)

በሠንጠረዡ እንደተመለከተዉ በስነ-ፅሁፍ ቡድን በቅድመ ትምህርቱ ፈተና የዳግም ልኬት ቲ-ቴስት ትንተናው እንዳሳየው፤የስነጽሁፍ ቡድን አማካይ ውጤት (7.12)፣መደበኛ ልይይት (2.536)፤ ሆኖ ሲገኝ በድህረ ፈተናው ደግሞ አማካይ ውጤት (15.53)፣መደበኛ ልይይት (3.246)፤ሆኖ ተገኝቷል፡፡ የቅድመ ፈተናው ከሚጠበቀው አማካይ ውጤት≥ 10 ) በታች ሲሆን የድህረ ፈተናው ውጤት ደግሞ ከሚጠበቀው አማካይ ውጤት በላይ መሆኑን የቲዋጋ 12.936 እና 27.569 ፤በ50 የነፃነት ደረጃ፣ $p \leq 0.05$) መሆኑን አመላክቷል፡፡

**ሠንጠረዥ4.6. ኢስነ ጽሁፍ ቡድን ቅድመና ድህረ ትምህርት የአንብቦ መረዳት ክሂል ፈተና ውጤት የዳግም ልኬት ቲ-ቴስት ትንተና**

| ቡድን | ፈተና | ናሙና | አማካይ ውጤት | መደበኛ ልይይት | መደበኛ ስህተት | የቲ-ዋጋ | የነፃነት ደረጃ | የ"p"ዋጋ Sig. |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ኢስነጽሁፍ | ቅድመ | 51 | 7.16 | 2.955 | .414 | 7.721 | 50 | 0.000 |
| | ድህረ | 51 | 7.22 | 3.537 | .495 | 12.461 | 50 | 0.000 |

የሚጠበቀው አማካይ ውጤት (Expected mean ≥10), ($p \leq 0.05$)

በሠንጠረዡ እንደተመለከተዉ በኢስነ-ፅሁፍ ቡድን በቅድመ ናድህረ ትምህርቱ ፈተና የዳግም ልኬት ቲ-ቴስት ትንተናው እንዳሳየው፤የኢስነጽሁፍ ቡድን አማካይ ውጤት (7.16) ፣መደበኛ ልይይት (2.955)፤ ሆኖ ሲገኝ በድህረ ፈተናው ደግሞ አማካይ ውጤት (7.22) ፣መደበኛ ልይይት(3.537)፤ሆኖ ተገኝቷል፡፡ የቅድመ ፈተናውም ሆነ የድህረ ፈተናው አማካይ ውጤት ከሚጠበቀው አማካይ ውጤት (≥ 10) በታች መሆኑን የቲዋጋ 7.721 እና 12.461 ፤በ50 የነፃነት ደረጃ፣ $p \leq 0.05$) ተመላክቷል፡፡ የድህረ ትምህርት አንብቦ መረዳት ክሂል ፈተና አማካይ ውጤት ከቅድመ ትምህርት አንብቦ መረዳት ክሂል ፈተና አማካይ ውጤት በ0.06 በሆነ ልዩነት አሳይቷል፡፡ በመሆኑምበቅድመና በድህረ ፈተናው መካካል ጉል የሆነ ልዩነት አልታየም፡፡

ከስነፅሁፋዊ እና ከኢስነፅሁፋዊ ፅሁፎች በተማሪዎች አንብቦ መረዳት ችሎታ ላይ የበለጠ አስተዋፅኦ ያለው የትኛው ነው? ለሚለው የጥናቱን የመጀመሪያ መረጃዎች (በዳግመምልኬትና በነፃ ናሙና ቲ ቴስት) ስታቲስቲክስ ተተንትኗል፡፡ ስነፅሁፋዊና ኢስነፅሁፋዊ ፅሁፎች በተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ክሂል ላይ የሚኖራቸው ሚና ምን እንደሆነ በቅደመ ፈተናና በድህረ ፈተና በተሰበሰበው መረጃ አማካዩና መደበኛ ልይይቱ ተስልቷል፡፡ በቅድመና በድህረ ትምህርት ፈተናዎች መካከል ጉልህ ልዩነት መኖርና አለመኖሩን ለመፈተሽም የዳግም ልኬት እና በነፃ ናሙና ቲ-ቴስት ተግባር ላይ ውሏል፡፡

በመሆኑም ይህ መሰረታዊ ጥያቄ ከስነ-ፅሁፋዊና ኢስነ-ፅሁፋዊ ፅሁፎች የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ክሂል ለማጎልበት የበለጠ አሰታዋፅኦ ያለዉ የትኛዉ ነዉ?የሚለዉን ለመለየት በቅድመ ትምህርትና በድህረ ትምህርት በተገኘዉ የፅሁፍ መጠይቅ መሰረት እንደሚከተለዉ ተተንትኗል፡፡

**ሠንጠረዥ4.7** ፡ የስነጽሁፋዊና ኢስነጽሁፋዊ ቡድኖችየፅሑፍ መጠይቅ የቅድመ ትምህርት የነፃ ናሙና ቲ-ቴስት (independent sample t-test) ትንተና

| ቡድን | መጠይቅ | ናሙና | አማካይ ውጤት | መደበኛ ልይይት | መደበኛስ ህተት | የቲ-ዋጋ | የነፃነት ደረጃ | የ"p"ዋጋSig. |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የስነፅሑፍ | ቅድመ | 51 | 21.07 | 3.521 | .493 | -2.373 | 100 | .020 |
| የኢስነ ፅሁፍ | ቅድመ | 51 | 21.04 | 3.735 | .523 | -2.712 | 100 | .020 |

የሚጠበቀው አማካይ ውጤት (Expected mean $\geq$ 25), ($p \leq 0.05$)

**ሠንጠረዥ 4.7፡** የፅሑፍ መጠይቅ የነፃ ናሙና ቲ-ቴስት (independent sample t-test) ትንተና ሲሆን ከለይ በሰንጠረዥ 4.7 በተገለፀዉ መሰረት የስነ-ፅሁፍ ቡድን የቅድመ ትምህርት የአንብቦ መረዳት ክሂል የፅሁፍ መጠይቅ አማከይ ዉጤት (21.07)፣መደበኛ ልይይት 3.521 ሲሆን የኢስነ-ፅሁፋዊ ቡድን የቅድመ ትምህርት የአንብቦ መረዳት ክሂል የፅሁፍ መጠይቅ አማካይ ዉጤት ደግሞ (21.04)፣መደበኛ ልይይት 3.735 ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህም የነፃ ናሙና ቲ-ቴስት ትንተና የሁለቱም ቡድን አማካይ ውጤት ከሚጠበቀው አማካይ ውጤት ($\geq$ 25) በታች መሆኑን የስነ ጽሁፍ ትንተናው የቲ ዋጋ -2.373 እና የኢስነጽሁፍ ትንተናው የቲዋጋ -2.712፣ በ(100 የነፃነት ደረጃ፣ $p \leq 0.05$) አሳይቷል፡፡የሁለቱም ቡድኖች የቅድመ ትምህርት የአንብቦ መረዳት የፅሁፍ መጠይቅ ዉጤት ከአማካይ ዉጤቱ ያለዉ ርቀት ሲታይ ተቀራራቢ የሆነ ተነሳሽነት እንዳላቸዉላቸዉ ያሳያል፡፡በቅድመና በድህረ አማካይ ውጤቶች መካከል የ0.03 ለዩነት ብቻ በማሳየቱ ተቀራራቢ ተነሳሽነት ያላቸው መሆኑን ያሳያል፡፡

**ሠንጠረዥ4.8 ስነጽሁፍእና ኢስነጽሁፍ ቡድኖች የፅሑፍ መጠይቅ የድህረ ትምህርት የነፃ ናሙና ቲ-ቴስት (independent sample t-test) ትንተና**

| ቡድን | መጠይቅ | ናሙና | አማካይ ውጤት | መደበኛ ልይይት | መደበኛ ስህተት | የቲ-ዋጋ | የነፃነትደረጃ | የ"p"ዋጋ Sig. |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ስነጽሁፍ | ድህረ | 51 | 29.12 | 3.445 | .482 | 7.934 | 100 | .000 |
| ኢስነጽሁፍ | ድህረ | 51 | 23.29 | 3.951 | .553 | 7.934 | 100 | .000 |

የሚጠበቀው አማካይ ውጤት (Expected mean $\geq$ 25), ($p \leq 0.05$)

የድህረ መጠይቅ ትንተናውን ስንመለከት የስነጽሁፍ ቡድኑ አማካይ ውጤት 29.12፣መደበኛ ልይይት 3.445 ሆኖ ሲገኝ የኢስነጽሁፍ ቡድኑ አማካይ ውጤት 23.29 ፣መደበኛ ልይይት 3.951 መሆኑን ትንተናው አሳይቷል። በድህረ ትንተናው እንደታየው የስነጽሁፍ ቡድኑ አማካይ ውጤት ከሚጠበቀው አማካይ ከ ($\geq$ 25) በላይ መሆኑን ትንተናው ሲያሣይ፣ የኢስነጽሁፍ ቡድኑ አማካይ ውጤት ግን ከሚጠበቀው አማካይ ከ ($\geq$ 25) በታች ሆኖ መገኘቱን በ (የቲዋጋ 7.934፣በነፃነት ደረጃ100፣ በ $p \leq 0.05$) መሆኑን ትንተናው አመልክቷል። በስነ ጽሁፍና በኢስነጽሁፍ የጽሁፍ የድህረ የጽሁፍ መጠይቅ አማካይ ውጤቶች መካከል የስነ ጽሁፍ ቡድኑ በ5.83 በልጦ በከፍተኛ ልዩነት አሳይቷል

**ሠንጠረዥ 4.9 የሥነ ጽሁፍ ቡድን የቅድመና ድህረ ትምህርት የፅሁፍ መጠይቅ ዉጤት የነፃ ናሙና ቲ ቴስት ትንተና**

| ቡድን | መጠይቅ | ናሙና | አማካይ ውጤት | መደበኛ ልይይት | መደበኛ ስህተት | የቲ-ዋጋ | የነፃነትደረጃ | የ"p"ዋጋ Sig. |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የስነጽ ሁፍ ቡድን | ቅድመ | 51 | 21.07 | 3.521 | .493 | -2.373 | 100 | .020 |
| | ድህረ | 51 | 29.12 | 3.445 | .482 | 7.934 | 100 | .000 |

የሚጠበቀው አማካይ ውጤት (Expected mean $\geq$ 25), ($p \leq 0.05$)

**ሠንጠረዥ4.9** የሥነ ጽሁፍ የነፃ ናሙና ቅድመና ድህረ የጽሁፍ መጠይቅ ትንተና ሲሆን የቅድመ ትምህርት አንብቦ መረዳት የቅድመ የጽሁፍ መጠይቅ አማካይ ውጤት

21.07፣መደበኛ ልይይት 3.521 ሆኖ የተገኘ ሲሆን የድህረ ትምህርት የአንብቦ መረዳት ክሂል የጽሁፍ መጠይቅ አማካይ ውጤት 29.12፣መደበኛ ልይይት 3.445 ሀኖ ተገኝቷል፡፡

በመሆኑም በድህረትምህርት አንብቦ መረዳት ክሂል የጽሁፍ መጠይቅና በቅድመ መጠይቅ መካከል ያለ ሲሆን የድህረትምህርት የጽሁፍ መጠይቅ አማካይ ውጤት በ8.05 በልጦ ከፍተኛ ልዩነት አሳይቷል፡፡

**ሠንጠረዥ4.10 የኢሥነ ጽሁፍ ቡድን ቅድመና ድህረ የጽሑፍ መጠይቅ ዉጤት የነፃ ናሙና ቲ ቴስት ትንተና**

| ቡድን | መጠይቅ | ናሙና | አማካይ ውጤት | መደበኛ ልይይት | መደበኛ ስህተት | የቲ-ዋጋ | የነፃነት ደረጃ | የ"p"ዋጋ Sig. |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የኢስነጽ ሁፍ ቡድን | ቅድመ | 51 | 21.04 | 3.735 | .523 | -2.712 | 100 | .020 |
| | ድህረ | 51 | 23.29 | 3.951 | .553 | 7.934 | 100 | .000 |

የሚጠበቀው አማካይ ውጤት (Expected mean $\geq$ 25), ( p $\leq$ 0.05)

ሠንጠረዥ 4.10 የኢሥነ ጽሁፍ የነፃ ናሙና ቅድመና ድህረ መጠይቅ ትንተና ሲሆን የቅድመ ትምህርት የአንብቦ መረዳት ክሂል የጽሁፍ መጠይቅ አማካይ ውጤት 21.04፣መደበኛ ልይይት 3.735 ሆኖ የተገኘ ሲሆን የድህረ ትምህርት የአንብቦ መረዳት ክሂል የጽሁፍ መጠይቅ አማካይ ውጤት 23.29፣መደበኛ ልይይት 3.951 መሆኑን ትንተናው አሳይቷል፡፡ በመሆኑም በመካከላቸው ያለው ልዩነት በ 2.25 የድህረ መጠይቁ በልጦ ተገኝቷል፡፡

**ሠንጠረዥ 4.11 የስነፅሑፍ ቡድን የቅድመና ድህረ ትምህርት የፅሑፍ መጠይቅ የዳግም ልኬት ቲ-ቴስት ትንተና**

| ቡድን | መጠይቅ | ናሙና | አማካይ ውጤት | መደበኛ ልይይት | መደበኛ ስህተት | የቲ-ዋጋ | የነፃነት ደረጃ | የ "p"ዋጋ Sig. |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የስነፅ ሑፍ | ቅድመ | 51 | 21.07 | 3.521 | .493 | 41.319 | 50 | .000 |
| | ድህረ | 51 | 33.82 | 6.196 | .868 | 36.680 | 50 | .000 |

የሚጠበቀው አማካይ ውጤት (Expected mean=25), (p $\leq$ 0.05)

ከላይ በሰንጠረዡ 4.11 ለመግለፅ እንደተሞከረዉ የስነ-ፅሁፍ ቡድን በቅድመ መጠይቅ ትንተናው እንደታየው የስነጽሁፍ ቡድኑ አማካይ ውጤት 21.07፣ መደበኛ ልይይት 3.521

መሆኑን በ(41.319 የቲዋጋ፣ በ50 የነፃነት ደረጃ፣ $p \leq 0.05$) ሲያሣይ ይህም አማካይ ውጤቱ ከሚጠበቀው ከ≥25 በታች ሆኖ ሲገኝ የድህረ ትምህርት የአንብቦ መረዳት ክሂል የጽሁፍ መጠይቅ አማካይ ውጤት 33.82 ፡ መደበኛ ልይይት 6.196 ሆኖ መገኘቱን በ(36.680 የቲዋጋ፣ በ50 የነፃነት ደረጃ፣ $p \leq 0.05$) ትንተናው አሳይቷል፡፡

ይህም የድህረ ትምህርቱ የጽሁፍ መጠይቅ አንብቦ መረዳት ክሂልአማካይ ውጤት በ12.75 ከቅድመው በልጦ ተገኝቷል፡፡

**ሠንጠረዥ4.12 የኢስነ ፅሁፍ የፅሑፍ ቡድን የቅድመና ድህረ ትምህርት የጽሁፍ መጠይቅ የዳግም ልኬት ቲ-ቴስት ትንተና**

| ቡድን | መጠይቅ | ናሙና | አማካይ ውጤት | መደበኛ ልይይት | መደበኛ ስህተት | የቲ-ዋጋ | የነፃነት ደረጃ | የ "p"ዋጋ Sig. |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የኢስነ ፅሁፍ | ቅድመ | 51 | 21.04 | 3.635 | .423 | 40.298 | 50 | .000 |
| | ድህረ | 51 | 20.01 | 3.615 | .506 | 45.088 | 50 | .000 |

የሚጠበቀው አማካይ ውጤት (Expected mean=25), ($p \leq 0.05$)

የኢስነጽሁፍ ቡድኑ የቅድመ ትምህርት አንብቦ መረዳት ክሂል የጽሁፍ መጠይቅ አማካይ ውጤት 21.04፣መደበኛ፤ልይይት 3.635 መሆኑ በ (ቲ ዋጋ 40.298፣ በ50 የነፃነት ደረጃ፣በ $p \leq 0.05$) አሳይቷል፡፡በዚህ ትንተና አማካይ ውጤቱ ከሚጠበቀው አማካይ ከ≥25 በታች ሆኖ ተገኝቷል፡፡

የድህረ መጠይቅ ትንተና ስንመለከት የኢስነ-ፅሁፍ ቡድን የድህረ ትምህርት የአንብቦ መረዳት ክሂል የፅሁፍ መጠይቅ አማካይ ዉጤት (20.01)፣መደበኛ ልይይት 3.615 ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም የኢስነ-ፅሁፍ ተማሪዎች የቅደመ ትምህርትየጽሁፍ መጠይቅ ከድህረ ትምህርት የአንብቦ መረዳት ክሂል የፅሁፍ መጠይቅ አማካይ ዉጤት በ1.03 የቅድመ መጠይቁ ብልጫ አሳይቷል፡፡ ይሁንና የሁለቱም መጠይቆች አማካይ ውጤት ከሚጠበቀው ከ(≥25) በታች በሆኑንም አመላክቷል፡፡

በአጠቃላይ የስነ-ፅሁፍ ተማሪዎች የድህረ ትምህርት የአንብቦ መረዳት ክሂል የፅሁፍ መጠይቅ አማካይ ዉጤት33.83 ሲሆን የኢስነጽሁፍ አማካይ ውጤት 20.01 ሆኖ የድህረው ከሚጠበቀው ከ(≥25) በልጦ መገኘቱን በ(ቲዋጋ 36.680 ፣ በነፃነት ደረጃ 50፣ በ $p \leq 0.05$) ሲያሣይ የኢስነጽሁፍ ቡድኑ አማካይ ውጤት ግን ከሚጠበቀው ከ(≥25) በታች መሆኑን

በ(ቲዋጋ 45.088፣በ 50 የነፃነት  ደረጃ፣ በ $p \leq 0.05$) መሆኑን አመላክቷል፡፡ በመካከላቸው ያለው ልዩነትም የስነጽጉፍ ቡድኑ በ13.81 በሆነ  ከፍተኛ ልዩነት በልጦ ታይቷል፡፡

## 4.2 የውጤት ማብራሪያ

የዚህ ጥናት ትኩረት ስነጽሁፋዊና ኢ-ስነጽሁፋዊ ፅሁፎች የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ክሂልን ከማዳበር ረገድ ያላቸውን ፋይዳ መመርመር ነው፡፡ በመሆኑም በፈተና በተሰበሰቡት መረጃዎች መሠረት ስነጽሁፋዊና ኢ-ስነጽሁፋዊ ፅሁፎች የአንብቦ መረዳት ክሂል ችሎታን በማጎልበት ረገድ ያላቸውን ፋይዳ፣ ልዩነት ይኖረው አይኖረው እንደሆነ ለመፈተሽ መረጃዎች በዳግም ልኬት እና በነፃናሙና ቲ ቴስት ስታቲስቲክሶች ተተንትነዋል፡፡

የዚህ ጥናት የመጀመሪያው ዓላማም "ስነ-ፅሁፋዊ እና ኢስነ-ፅሁፋዊ ፅሁፎች በተማሪዎች አንብቦ መረዳት ችሎታ ላይ የበለጠ አስተዋፅኦ ስለየሚኖራቸውን ሚና መመርመር" የሚል ነበር፤ ዓላማውንም ለመፈተሽ መረጃው በዳግም ልኬትና በነፃናሙና ቲ-ቴስት ስታትስቲክስ ተተንትኗል፡፡

የፈተናው ቅድመ ትንተና የታየው በስነ ጽሁፍ ቡድን እና በኢስነጽሁፍ ቡድን መካከል የጐላ ልዩነት አለመኖሩን አሳይቷል፡፡ይህም የፈተናው የቅድመ ፈተና የነፃና የዳግም ናሙና ቲ ቴስት እንዳሳየው አማካይ ውጤታቸው ከሚጠበቀው ከ10 በታች ሆኖ መገኘቱን በ(ቲ ዋጋ 2.265፣ 100 የነፃነት ደረጃ፣$p \leq 0.05$) መሆኑን ትንተናው ያሳያል፡ በዚህም መሰረት በሁለቱ ቡድኖች መካከል የአንብቦ መረዳት ክሂል ልዮነት አለመኖሩን አረጋግጧል፡፡

በድህረ ፈተናው የስነጽሁፍ ቡድኑ አማካይ ውጤት ከሚጠበቀው ከ(10) በላይ ሆኖ የተገኘ መሆኑን (በቲ-ዋጋ 11.464፣በነፃነት ደረጃ  100፣  $p \leq 0.05$) አሳይቷል፡፡ይህም በድህረ ፈተናው የተገኘው የቲ ዋጋ  11.464 ፣ ከቲ ሠንጠረዥ ዋጋ 1.99 በልጦ በመገኘቱ  በድህረ ፈተናው የስነጽሁፍ ቡድኑ የጐላ ልዩነት  ያሣያል፡፡

የኢስነ ጽሁፍ የድህረ ትንተና ውጤቱ እንዳመለከተው ከሚጠበቀው አማካይ ውጤት ($\geq$ 10) በታች ሆኖ መገኘቱን ትንተናው ከማሳየቱም በተጨማሪም (የቲዋጋ11.464፣ በ100 የነፃነት ደረጃ፣ $p \leq 0.05$) የነፃ ናሙና ትንተናው አሳይቷል፡፡
በሌላ መልኩ የስነ ጽሁፍ ተማሪዎች በቅድመና ድህረ አማካይ ውጤቶች መካካል ጉልህ የሆነ ልዩነት የታየ ሲሆን የድህረ ትምህርቱ የአንብ መረዳት ክሂል አማካይ ውጤት ከቅደመ ትምህርት አንብቦ መረዳት ክሂል ውጤት ተሽሎ የተገኘ መሆኑን (ሠንጠረዥ 4.5) ላይ ተመላክቷል፡፡

የኢስነ ጽሁፍ የድህረ ትምህርት አንብቦ መረዳት ክሂል ፈተና አማካይ ውጤት ከቅድመ ትምህርት አንብቦ መረዳት ክሂል ፈተና አማካይ ውጤት በ0.06 በሆነ ልዩነት ያሣየ መሆኑን (በሠንጠረዥ 4.6) ላይ መመልከት ይቻላል፡፡ በመሆኑም በቅድመና በድህረ ፈተናው መካካል ጉል የሆነ ልዩነት አልታየም፡፡

ከዚህ ጥናት ጋር ተመሳሳይ ግኝት ያላቸው ጥናቶች ዘመንፈስ (1991) በሙከራ / በልምምድ የተማሩ ተማሪዎች የተሻለ ውጤት እንዳስመዘገቡ፣የክንፈሚካኤል(1995)፤በስነ ጽሁፍ ተማሪዎችን ማስተማር አራቱን ክሂሎች የሚያሳድግ መሆኑን፣reza mokhtari (2014) በስነፅሁፋዊ ፅሁፍ የተማሩት ተማሪዎች የተሻለ ብቃት እንዳላቸው አሳይቷል፡፡

በተጨማሪም ጥሩነሽ (2005) እና ነብዮ (2006) ጥናቶች ውጤት ጋር ይደጋገፋል፡፡ ስነፅሁፋዊ ፅሁፍ የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ክሂል ችሎታ ለማሳደግ የላቀ ድርሻ እንዳለው ካገኟቸው የጥናት ውጤቶች ጋር ተመሳሳይ ነዉ፡፡ በጥቅሉ ስነፅሁፋዊ ፅሁፍ የአንብቦ መረዳት ክሂልን ለማዳበር ከተለመደው የአንብቦ መረዳት ክሂል ማስተማሪያ ፅሁፍ የበለጠ ውጤታማ መሆኑን የዚህ ጥናት ግኝት አሳይቷል፡፡

በጥናቱ ውጤት መሰረት አንብቦ የመረዳት ችሎታ ላይ መሻሻል የታየው ከምንባቡ የወጡ ቃላትን ተመሳሳይና ተቃራኒ በማውጣት፣ ከምንባቡ ዋና ሀሳብ በመለየት፣ ከምንባቡ ሀሳብ በመነሳት በፅሁፍና በቃል ሀሳብን መግለፅ ለማስተማሪያነት የቀረቡ ፅሁፎች ዋና ዋና ሀሳብን ለመለየት አመቺ በመሆናቸው፣ የፀሀፊውን መልዕክት መለየትና መረዳት፣ ከተሰጠው ፅሁፍ በመነሳት ማጠቃለያ መስጠት፣ ሀቅና የግል አስተያየቶችን ለመለየት ግልጽ በመሆናቸው ለዚህ ውጤት አብቅቷቸዋል ቢባል ምክንያታዊነት ይኖረዋል፡፡ ይህም ማለት እንደዚህ አይነት መልመጃዎች ቢዘጋጁ የአንብቦ መረዳት ችሎታቸውን ያዳብራል ማለት ነው፡፡

ሁለተኛው የጥናቱ ጥያቄ “ከስነፅሁፋዊና ኢ-ስነፅሁፋዊ ፅሁፎች የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ክሂል ተነሳሽነት ለማጎልበት የበለጠ አስተዋፅኦ የሚኖራቸውን መመርመር፡፡” የሚል ነበር፤ ጥያቄውንም ለመፈተሽ መረጃው በነፃና በዳግም ናሙና ቲ ቴስት ስታትስቲክስ ተተንትኗል፡፡ መረጃው ተተንትኖ የተገኘው ውጤት እንዳሳየው በኢስነፅሁፋዊ ፅሁፍ የተማሩት ተማሪዎች የቅድመ ትምህርት የአንብቦ መረዳት ክሂል የፅፍ መጠይቅ አማካይ ከድህረ ትምህርት የአንብቦ መረዳት ክሂል የፅሁፍ መጠይቅ አማካይ ውጤት በ 1.03 በልጦ የታየ ሲሆን በስነ-ፅሁፋዊ ፅሁፍ የተማሩት ተማሪዎች የድህረ ትምህርት አንብቦ መረዳት ክሂል የፅሁፍ መጠይቅ የዳግም ቲ ቴስት አማካይ ዉጤት ከቅድመ ትምህርት የአንብቦ መረዳት ክሂል የፅሁፍ መጠይቅ በ12.75 በልጦ (ሠንጠረዥ 4.11) እንደተመለከተው ከፍተኛ ልዩነት አሳይቷል፡፡

የድህረ መጠይቁ ትንተና እንዳሳየው የፅሁፍ መጠይቅ አማካይ ዉጤት ከሚጠበቀው ከ(≥25) በልጦ መገኘቱን በ(ቲዋጋ 36.680 ፣ በነፃነት ደረጃ 50፣ በ p≤0.05) አሳይቷል፡፡ ይህም በቅድመና በድህረ ትንተናው ጉልህ ልዩነት መኖሩን የተገኘው የቲዋጋ 36.680 ከሠንጠረዥ ዋጋ ከ2.011 በልጦ መገኘቱን ትንተናው አመልክቷል፡፡

ስነፅሁፋዊ ይዘት ያላቸው ምንባቦችን ተጠቅሞ ማስተማር በተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ክሂል ላይ ያለውን ሚና በተመለከተ የተገኘው የዚህ ጥናት ውጤት ጥሩነሽ (2005) እና ነብዮ (2006) ካገኙት የጥናት ውጤት ጋር ተመሳሳይ መሆኑን ያሳያል፡፡

በአጠቃላይ በክለሳ ድርሳን ክፍሉ እንደቀረበው ስነጽሁፋዊ ፅሁፍ የአንብቦ መረዳት ክሂል ችሎታን የሚያጎልበት መሆኑን Lazar (1993)፣ carterand Long(1991)፡፡)፣ Hill (1986 የምርምር ውጤቶች አመላክተዋል፡፡ በዚህ ጥናት ውጤትም ስነጽሁፋዊ ጽሁፍ ምንባብ የአንብቦ መረዳት ክሂል ችሎታን በማሻሻል ረገድ ከፍተኛ ድርሻ እንዳለው የስታቲስቲክስ ውጤቱ አመላክቷል፡፡

በመማር ማስተማሩ ወቅት በተደረገው ኢቀጥተኛ ምልከታም በትምህርቱ መጀመሪያ ላይ በሁለቱም ይዘትይማሩ የነበሩ ተማሪዎች ያሳዩት የነበረው የመማር ስሜት ዝቅተኛ ነበር፤ በሂደት ግን በስነፅሁፋዊ ፅሁፎች የተማሩ ተማሪዎች ንቁ ተሳትፎ ያሳዩ ሲሆን በኢ-ስነፅሁፋዊ ፅሁፍ የተማሩት ተማሪዎች ብዙም የነቃ ተሳትፎ አልነራቸውም፡፡

ይህም ጥሩነሽ (2005) እና ነብዮ (2006) ካገኙት ጥናት ዉጤት ጋር ይመሳሰላል፡፡ ስለዚህ የአንብቦ መረዳት ክሂል ችሎታን ለማጎልበት በስነፅሁፋዊ ፅሁፎች የተደራጁ ምንባቦችን ተጠቅሞ ማስተማር የተሻለ ነው ቢባል ተገቢነት እንዲኖረው ያደርጋል፡፡

በአጠቃላይ የዚህ ጥናት ውጤት ስነፅሁፋዊ ፅሁፍን ተጠቅሞ ማስተማር የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ክሂል የማሳደግ ፋይዳ አለው፤ የሚል አንድምታ ይኖረዋል፡፡ ይህም የድህረ ትምህርት የተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ክሂል ፈተና አማካይ ውጤት ከቅድመ ትምህርት የአንብቦ መረዳት ክሂል ፈተና አማካይ ውጤት ጉልህ ሆኖ መገኘቱ አንዱ ማስረጃ ሊሆን ይችላል፡፡ በተጨማሪ የድህረ ትምህርት የአንብቦ መረዳት ክሂል የፅሁፍ መጠይቅ አማካይ ዉጤት ከቅድመ ትምህርት የፅሁፍ መጠይቅ አማካይ ውጤት ጉልህ ሆኖ መታየቱ ተጨማሪ ሊሆን ይችላል፡ በአጠቃላይ በዚህ ጥናት የተገኙ ውጤቶች እንደሚያመለክቱት ስነፅሁፋዊ ፅሁፍን ተጠቅሞ ማስተማር የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ክሂል ከማሻሻል ረገድ ከፍተኛ ፋይዳ አላቸው፤ለማለት ይቻላል፡፡

# ምዕራፍ አምስት

# 5. ማጠቃለያ፣ መደምደሚያና መፍትሔ

## 5.1. ማጠቃለያ

የጥናቱ ዋና አላማ በስነፅሁፋዊና ኢ-ስነፅሁፋዊ ፅሁፎች በተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ የአንብቦ መረዳት ክሂል ላይ ያለውን ሚና መመርመር ነበር። በዚህም መሰረት በጥናቱ ምላሽ ሊሰጥባቸው የታለሙት መሰረታዊ ጥያቄዎች የሚከተሉት ነበሩ።

1. ከስነፅሁፋዊ እና ኢስነፅሁፋዊ ፅሁፎች በተማሪዎች አንብቦ መረዳት ችሎታ ላይ የበለጠ አስተዋፅኦ ያለው የትኛው ነው?
2. ከስነፅሁፋዊና ኢ-ስነፅሁፋዊ ፅሁፎች የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ክሂል ለማጎልበት እና ለማስተማር የበለጠ ልዩነት ያሳየው የትኛው ነው?

የጥናቱ ተሳታፊዎች በሆሮ ጉዱሩ ወለጋ ዞን ሻምቡ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ2015 ዓ.ም በ10ኛ የክፍል ትምህርታቸውን በመከታተል ላይ ያሉ ተማሪዎች ናቸው። በዚህ የክፍል ደረጃ ከሚማሩ 915 ተማሪዎች መካከል በእድል ሰጪ ናሙና የተመረጡት የ "10E"ና "10G" የክፍል 102 ተማሪዎች የጥናቱ ተሳታፊዎች ሆነዋል። በጥናቱ ዋነኛው የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያም ፈተና ነዉ። ሁለተኛው ደግሞ የፅሁፍ መጠይቅ ሲሆን እንደሪስ ዓባይ ለሁለተኛ ድግሪ ማሟያ ካቀረበዉ ጥናት ላይ እንዳለ በመውሰድ ተዘጋጅቶ ስራ ላይ ውሏል።

ተጠኚዎችም በመማር ማስተማሩ ሂደት በየትኛው የፅሁፍ ይዘት እንደሚማሩ ከመመረጣቸዉ በፊት የቅድመ ትምህርት አንብቦ መረዳት ፈተና ከዚህ በፊት ጥሩነሽ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት የተጠቀሙበትንና አስተማማኝ ሆኖ የተገኘዉን እንዳለ በመዉሰድ የተማሪዎቹን የአንብቦ መረዳት ክሂልን ለመለካት ተግባራዊ ሆኗል። በመቀጠልም ለማስተማሪያነት የተዘጋጁትን ማስተማሪያ ፅሁፎች ለስድስት ሳምንት ሲማሩ ቆይተዋል፤በመጨረሻም ከቅድመ ትምህርት ፈተና ጋር አቻ የሆነ የድህረ ትምህርት ፈተና ተግባራዊ በማድረግ ለጥናቱ የሚፈለገው መረጃ ተሰባስቧል።

በፈተና አማካኝነት የተሰበሰበውን መረጃ መሰረት በማድረግ በቅድሚያ በዋናነት የዚህ ጥናት ጉዳይ የሆነውን በስነፅሁፋዊና በኢስነፅሁፋዊ ፅሁፎች የአማርኛ ቋንቋን የአንብቦ መረዳት ክሂልን ለማስተማር ያላቸው ፋይዳ ምን እንደሆነ ለማረጋገጥ በቅድመ ትምህርት ፈተናና በድህረ ትምህርት የተገኘውን መረጃው በዳግም ልኬትና በባዕድ ናሙና ቲ-ቴስት ተተንትኗል። በዚህም የቅድመ ትምህርት ፈተና በሁለቱ ይዘቶች በሚማሩ ተማሪዎች ላይ አማካይ ውጤቶች መካከል በስታቲስቲክስ የጎላ ልዩነት ያልታየበት ሲሆን፣በድህረ ትምህርት ፈተና በተገኘው

አማካዩች መካከል በዳግም ልኬትና ነፃ ናሙና ቲ-ቴስት መሰረት በስታቲስቲክስ ጉልህ ($p<0.05$) ልዩነት ታይቷል፡፡ በዚህም ስነፅሁፋዊ ፅሁፍ በተማሪዎች የአንብቦ መረዳትሰ ክሂል ላይ ለውጥ እንዳመጣ ለመረዳት ተችሏል፡፡

በሁለተኛው ደግሞ ከስነፅሁፋዊና ኢ-ስነፅሁፋዊ ፅሁፎች የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ክሂል ለማጎልበት የበለጠ አስተዋፅኦ ያለው የትኛው ነው? ከሚለው አንጻር በሁለቱ ፈተናዎች ማለትም በቅድመና በድህረ ያለውን ልዩነት ለማየት በዳግም ልኬትና በነፃ ናሙና ቲ-ቴስት ትንተና መሰረት የድህረ ፈተናው አማካይ ውጤት መካከል በስታትስቲክስ ጉልህ የሆነ ልዩነት ($p\leq0.05$) ታይቷል፡፡ ይህም በተማሪዎች ዘንድ የስነጽሁፋዊ አንብቦ መረዳት ክሂል የተሻለ ውጤት ሲያሳይ ፤ በኢስነፅሁፋዊ ፅሁፍ አንብቦ መረዳት ክሂል ተነሳሽነት ላይ የጎላ ልዩነት እንደማያሳይ ለመረዳት ተችሏል፡

በአጠቃላይ የጥናቱ ትንተና በተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ክሂል ላይ በስነፅሁፋዊ ፅሁፍ የሚማሩ ተማሪዎች በኢስነፅሁፋዊ ፅሁፍ ከሚማሩ ተማሪዎች የተሻለ የአንብቦ መረዳት ክሂል እንዳላቸው አሳይቷል፡፡ በመሆኑም ስነ-ፅሁፋዊ ፅሁፍን መሰረት ያደረገ ምንባብን ተጠቅሞ ማስተማር በተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ክሂል ላይ ለውጥ ሊያመጣ እንደሚችል ይጠቁማል፡፡

## 5.2 መደምደሚያ

በጥናቱን ውጤትና ማብራሪያ መሰረት በማድረግ ከሚከተሉት መደምደሚያ ላይ ተደርሷል፡፡

1. በስነፅሁፋዊ ፅሁፍና በአንብቦ መረዳት ክሂል መካከል ግንኙነት አለ፡፡ ይህም ስነፅሁፋዊ ፅሁፍ የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ክሂል በማገዝ ረገድ ሚና አለው የሚል እንድምታ አለው፡፡
2. በኢስነፅሁፋዊ ፅሁፍና በአንብቦ መረዳት ክሂል መካከል የተለየ ግንኙነት የለም፡፡ ይህም ኢስነፅሁፋዊ ፅሁፍ የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ክሂል በማገዝ ረገድ የጐላ ሚና እንደሌለው እንድምታ አለው፡፡
3. በስነፅሁፋዊ ፅሁፍና በኢስነፅሁፋዊ ፅሁፍ በአንብቦ መረዳት ክሂል መካከል ልዩነት ታይቷል፡፡ በመሆኑም ስነፅሁፋዊ ፅሁፍ የአንብቦ መረዳት ክሂል በማሻሻል ረገድ ተማሪዎች ተጠቃሚዎች መሆናቸውን ያመላክታል፡፡

## 5.3 የመፍትሔ ሀሳብ

በዚህ ጥናት የተደረሰባቸውን ውጤቶች ተግባራዊ ለማድረግ ብሎም የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ክሂልና ተነሳሽነትን ለማሳደግ እንዲቻል የሚከተሉት የመፍትሔ ሀሳቦች ተጠቁመዋል፡፡

1. በቋንቋ መማሪያ መጽሀፍት ውስጥ የሚካተቱ ምንባቦች ስነፅሁፋዊ ይዘት ያላቸው በመጠን ያነሱ ስለሆኑ ከኢስነፅሁፋዊ ጋር በእኩል መልኩ ቢመረጡ፡፡
2. የዚህ ጥናት ትንተና በተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ክሂል ላይ በስነፅሁፋዊ ፅሁፍ የተማሩ ተማሪዎች በኢስነፅሁፋዊ ፅሁፍ ከሚማሩ ተማሪዎች የተሻለ የአንብቦ መረዳት ክሂል እንዳላቸው አሳይቷል፡፡ በመሆኑም ስነ-ፅሁፋዊ ፅሁፍን መሰረት ያደረገ ምንባብን ተጠቅሞ ማስተማር በተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ክሂል ላይ ለውጥ ሊያመጣ እንደሚችል ታውቆ መምህራን ስነፅሁፋዊ ፅሁፎች ለአንብቦ መረዳት ክሂል ያላቸውን ጠቀሜታ ተገንዝበው፣ ስነፅሁፋዊ ፅሁፎችን በመጠቀም ቢያስተምሩ፤ ተማሪዎችም ከመማር ማስተማሩ ሂደት በተጨማሪ በሚያነቡበት ጊዜ ለስነፅሁፋዊ ፅሁፎች ተገቢውን ትኩረት ቢያደርጉ፡፡
3. ሁለቱንም ይዘቶች ከግምት ውስጥ ያስገባና ያነፃፀረ ጥናት ወደፊት ቢካሄድ የተሻለ ግንዛቤና የአሰራር ስልት ሊገኝ ይችላል፡፡ የሚሉት በአጥኚው የቀረቡ የመፍትሔ ሀሳቦች ናቸው፡፡

## ዋቢዎች


በድሉ ዋቅጅራ። (1996)። *በስነፅሁፍ ቋንቋን ማስተማር።* አዲስ አበባ፤ ንግድ ማተሚያ ድርጅት።

ክንፈሚካኤል ሱጋ። 1995። *"ስነፅሁፋዊ ይዘቶች የተማሪዎችን የቋንቋ ክሂልና የስነፅሁፍ እውቀት ለማሳደግ ያላቸው እገዛ በ1993ና 1994 ዓ.ም ለ10ኛና 11ኛ ክፍል መማሪያነት በተግባር ላይ በዋሉ መፃህፍት።"* ያልታተመ የድህረ ምረቃ ቴሲስ፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ አዲስ አበባ።

ዘመንፈስ ባራኪ። 1991። *"በስነፅሁፍ አማካኝነት አማርኛ ቋንቋን በማስተማር የአጭር ልቦለድ ሚና 11ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ የተካደ ጥናት።"* ያልታተመ የድህረ ምረቃ ቴሲስ፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ አዲስ አበባ።

ዳዊት ፍሬህይወት። 2000። *"በቤኒሻንጉል ጉምዝና በጋምቤላ ክልሎች ለመጀመሪያ ደረጃና ሁለተኛ ርከን (7ኛና 8ኛ ክፍል) ተማሪዎች የተዘጋጁ የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ውስጥ የተካተቱ ስነፅሁፋዊ ስራዎች አመራረጥ አደረጃጀት።"* ያልታተመ። የድህረ ምረቃ ቴሲስ፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ አዲስ አበባ።

እንድሪስ አባይ። (1994)። በቴክስት ውቅር ብልሃቶች በዐማርኛ ማንበብን መማር በተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታ ላይ ያለው ተጽዕኖ- በስድስተኛ ክፍል ተተኳሪነት። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፤ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ፣ያልታተመ።

ዘሪሁን አስፋዉ ። (2000) ። የስነ-ፅሁፍ መሰረታዉያን ።አዲስ አበባ፣

ጌትነት ታፈረ። 1998። *"ልቦለድን መጠቀም በክፈል ስውጥ የአንብ መረዳት ትምህርት አቀራረብ ፍተሻ፤ በትግራይ ክልል፣ ማዕከላዊ ዞን በተመረጡ አራት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ላይ የተካሄደ ጥናት ።"* ያልታተመ። የድህረ ምረቃ ቴሲስ፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ አዲስ አበባ።

ጌትነት አዲስ። 2001። *"በረጅም ልቦለድ ቅንጫቢ አማርኛ ቋንቋን ማስተማር ያለው ውጤታማነት በተመረጠ አንድ የምስራቅ ጎጃም ዞን ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ የተካሄደ ጥናት።"* ያልታተመ። የድህረ ምረቃ ቴሲስ፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ አዲስ አበባ።

ጥሩነሽ ክንፈ። 2005። *በሰሜን ሸዋ ዞን በእነዋሪ ሚሊኒዬም መሰናዶና አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ9ኛ ክፍል ተማሪዎች የአማርኛ ቴክስት አወቃቀር እውቀት አንብቦ የመረዳት ችሎታን በማጎልበት ረገድ ያለው ሚና።* ያልታተመ። የድህረ ምረቃ ቴሲስ፤ ባህርዳር ዩኒቨርስቲ፣ ባህርዳር።

ፈቃደ አዘዘ (1991) ‹‹አንዳንድ ነጥቦች ስለ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት አላማዎች፣ ስለ መማሪያ መፃህፍትና ስነ ጽሑፍ ሚና በቋንቋ ትምህርት (1944-1983)››:: ለቋንቋዎች ጥናት ተቋም ዘጠነኛ ዓመታዊ ሴሚናር የቀረበ፣ አ.አ.ዩ

Armbruister,Bonnie.Band.,andobsorn, Jen.H. 2002. *Reading Instruction and Assessment*. Understanding the IRA standards: Boston Allyn and Bacon.

Carter, R. and M.N (1991) *Teaching Literature*. Londodon: Rutledge.

Conely,M,W.(1992). *Content Reading Instruction*.Communication. Approach New York: Mc Graw-Hill Inc.

Dole,J.A.,Duffy,G.G.,Roehler,L.R.,and Pearson,D.D.(1991).Moving from the old To the new: Research on reading comprehension instruction.Revie Of Educational Research

Doolittle,P.Hicks,D. Triplett,C. Nichols,W.and Young, C.(2006).Reciprocal Teaching for Reading Comprehension in Higher Education: AStrategy for Fostering the Deeper Understanding of Texts. *International Journal of Teaching and Learning in Higher Education. 17*(2), 106-118.

Dymock,S (2007) Comprehension strategy Instruction: Teaching narrative Text structure Awarness. International Reading Association.The reading teacher, 6(12) pp.161-167.

Fox,E.& Alexander, P.A.(2009). Text Comprehension: A Retrospective, Perspective, and Prospective. In S. E. Israel & G. G. Duffy (Eds.), *Handbook of Research on Reading Comprehension* (pp. 227-239). New York: Routledge

Gaffney, J. S., & Anderson, R. C. (2000). Trends in Reading Research in United State: Changing Intellectual Currents Over Three Decades.In M. L. Kamil, P. B. Mosenthal, P. D.

Graham,Richard,T (1987).*Content Reading and the Reaction of meaning.English Teaching forum 76(2) 78-99.*

Grellet,F.(1981) *Developing Reading skills: practical Guide to Reading compherension Exercisis: Cambridge: cup.*

Greenwood,J. (1981).′′Comprehension and Reading ." in Abbott.G.and Wingard,p. (eds).Teaching of English asan International Language:Apractical Guide.

Cambridge University press

Gunning,Thomas G.(1996).Creating Reading Instruction for All Children.Chapter 6 192-236.

Guthrie, J.T., &Wigfield, A. (2000).Engagement and motivation in reading. In M.L. Kamil, P.B. Mosenthal, P.D. Pearson, & R. Barr (Eds.), *Handbook of reading research:* Volume III (pp. 403-422). New York, NY: Erlbaum.

Harmer,J. *(1991) The practice of English language Teaching London: New York longman.*

Hill,J (1986) *Using Literature in Language Teaching. London: MacmillanPublisher Ltd.*

Huang, Qian (2009). Background knowledge and reading teaching.*Asian Social Science*, 5 (5), 138-139

Hyland, ken (1990) *Purposes and strategy*: Teaching Extensive Reading skills. English Teaching forum. Xxv III (2) 14-17

Kamil, M. L., Afflerbach, P., Pearson, P. D., & Moje, E. B. (2011). Preface: Reading Reseach in a Changing Era: An Introduction to the Handbook of Reading Research.In M. L. Kamil, P. Afflerbach, P. D. Pearson & E. B. Moje (Eds.), *Handbook of Reading Research* (Vol. IV, pp. xiii-xxvi). New York: Routledge.

Khalaji, Reza & Vafaeeseresht, Karim (2012). The impact of reading strategy trainining on the reading comprehension of Iranian EFL learners. *Journal of Language Teaching and Research, 3* (1), 135-140.

Lazar, G (1986) *Literature and Language Teaching:* Cambridge CUP.

Leslie,L. & Cladwell, J. (2009). Formal and Informal Measures of Reading Comprehension.In S. E. Israel & G. G. Duffy (Eds.), *Handbook of Research on Reading Comprehsion* (pp. 403). New York: Routledge

Mckay, S (1986) *Literature in Language Calassroom In Brumfit, C.J. and R.A carter (eds). Literature and Language teaching*. Hongkong: Educational Law- priced Books Scheme with Oxford Universty Ptess.

Mike,C.,Julie,C.,& Sally,W.(1998).Comprhension:Theories & Strategies.Dominican College,School of Education

Nelson, Gayie. L (1984) *Reading Astudent center Approach*: EnglishTeaching Forum xxII(4) 2-5.

Nuttal, C (2000) *Teaching reading skills in a foreign language*:/2nd ed./Heinemann Educational Books.

Paris, S. G, & Hamilton, E. E. (2009). The Development of Children' Reading Comprehension. In S. E. Israel & G. G. Duffy (Eds.), *The Development of Children's Reading Comprehension* (pp. 32-53). New York: Routledge

Pearson,P.D. (2009). The Roots of Reading Comprehension Instruction.In S. E.Israel & G.G. Duffy (Eds.), *Handbook of Research on Reading Comprehension* (pp. 3-31). New York: Routledge

Reza Mokhtari (2014) *The Comparative Study of Literary vs. Non-literary Text and Iranian EFL Learners" Performance on Cloze Tests of Inference*- ACADEMY PUBLISHER Manufactured in Finland.

Rumelhart,D.E.(1977). Towards an Interactive model of Reading.In S,Dornic (ed),Attentionand Performance IV.NewYork.NY:Academic Press.

Schiefele, U.Scheffner, E., Moller,.&Wigfield,A. (2012). Dimensions of Reading Motivation and Their Relations to Reading Behavior and Competence.*Reading Research Quarterly*,47(4), 427-463.

Sheridan,M,E.(1981). Theories of Reading and Implications for Teachers.*Reading Horizons.*22, (1).

Simith, F.(1985). Reading. Greating Britain combridge University Press.Slavin,R.E.

_________(1980).Cooperative learning. Review of educational research

Wigfield, A., & Guthrie J.T. (1997).Relations of Children's Motivation for Reading to the Amount and Breadth of Their Reading.*Journal of Educational psychology*, 89(3), 420-432

Wiliams, E. (1984). Reading language in the classroom.London: machillan publishing.

*www.research gate.net.*

## አባሪዎች

### አባሪ 1. በስነፅሁፋዊና ኢ-ስነፅሁፋዊ ፅሁፍ የሚማሩ ተማሪዎች የቅድመትምህርት ፈተና

በስነፅሁፍና በኢ-ስነፅሁፋዊ ፅሁፍ የአማርኛ ቋንቋ ለአንብቦ መረዳት ክሂልን ከማሻሻል ረገድ ያለው ሚና በሚል ርዕስ ለሚካሄደው ምርምር መረጃ እንዲያስገኝ ለ10ኛ ክፍል ተማሪዎች የተዘጋጀ የአማርኛ ቋንቋ ቅድመ ትምህርት ፈተና /20%/

የፈተናው መነሻ ሰዓት 2፡00 ሰዓት

ለፈተናው የተሰጠ ጊዜ 2፡00 ሰዓት

**አጠቃላይ መመሪያ**

*ይህ ፈተና የተማሪዎችንየአማርኛ ቋንቋ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለመለካት የቀረበ ነው፡፡ ጥያቄዎቹ በቀረበው የምንባብ ሃሳብ መሠረት የሚመለሱ ሆነው አራት ንዑሳን ክፍሎች አሏቸው፡፡ የመጀመሪያው ክፍል ለቃላት የሚስማማቸውን ፍቺ ከተሰጡት አማራጮች ውስጥ መምረጥ፣ ሁለተኛው ምንባቡን መሠረት በማድረግ ሀረጎቹ የሚያስተላልፉትን ሃሳብ መግለጽ፣ ሦስተኛው የምንባቡን ዋና ዋና ሃሳቦች ለይቶ ማውጣት፣ አራተኛው የምንባቡን መልዕክት መፃፍ ናቸው፡፡*

*ሁሉንም ጥያቄዎች ለመስራት የተፈቀደው ጊዜ 2፡00 ሰዓት ነው፡፡ በተሰጠው ጊዜ የሁሉንም ጥያቄዎች መልስ ፃፍ/ፊ/፡፡ቀጥሎ የቀረበውን ምንባብ አንብባችሁ ከምንባቡ በኋላ የቀረቡትን ጥያቄዎች እንደአጠያየቃቸው መልሱ፡፡*

**ምንባብ**

*የንግግርንም ሆነ የጽሁፍን መልዕክት ለማንጠር ለማጉልበትና ለማስዋብ ከሚያገለግሉት ሥነ ቃላዊ ፈርጦቻችን መካከል ምሳሌያዊ ንግግሮች ይገኙበታል፡፡ እነዚህም ምሳሌያዊ ንግግሮች በከተማም ሆነ በገጠር በሚኖሩ የማንኛውም ቋንቋ ተናጋሪዎች የሚገለገሉባቸው የህዝብ ቅርሶች ናቸው፡፡ አንድ ማህበረሰብ ማህበራዊ ህይወቱ እያደገ፣ አስተሳሰቡም እየሰፋ መሄዱ እሙን ነው፡፡ ስለዚህ ከዘመኑ ጋር አብረው የሚራመዱ ምሳሌያዊ ንግግሮችን መርጦ መጠቀም ያስፈልገዋል፡፡ ለምሳሌ አብዛኞቹ የአማርኛ ምሳሌያዊ ንግግሮች ጠቃሚ ፍሬ ሃሳብ የማስተላለፋቸውን ያህል አንዳንዶቹ አፍራሽ መልዕክት ያዘሉ ናቸው፡፡ አንዳንድ ጊዜም ምሳሌያዊ ንግግሮችን ትክክለኛ ባልሆነ ቦታ በንግግር መልክ መጠቀም ጉዳት አለው፡፡*

*"ዝምታ ወርቅ ነው"*

*"ዝም ባለ አፍ ዝንብ አይገባበትም"*

*የሚሉትና ሌሎችም እድሜ ጠገብ የአማርኛ ምሳሌያዊ ንግግሮች ለዚህ በዋቢነት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ እነዚህን የመሳሰሉ ምሳሌያዊ ንግግሮች ያለ ቦታው ከተጠቀምን የመናገርን ነውርነት*

ሰብከው የዝምታን አስፈላጊነት የሚያወድሱ ይሆናሉ፡፡ በማንኛውም ጊዜ ዝም ማለት ተገቢ ነው የሚል አንድምታ ያላቸው ይመስላሉ፡፡ ይህ ሁኔታ ክፉ ደጉን ላልለየው ታዳጊ ወጣት ጉዳት እንዳለው መገመት አይሳንም፡፡

የዕድሜ እኩዮቿ ሲወያዩ ያዳመጠችውን፣ በሬድዮ የሰማችውን፣ በቴሌቪዥን ያየችውን በመንገድ ላይ የተመለከተቻቸውን ርዕሰ ጉዳይ አንስታ ወላጆቿን ለማወያየት የፈለገች ወጣት አንደበቷ ተፈትቶ የፈለገችውን አትናገርም፡፡ ምነው ቢሉ ወላጆቿ እርስ በእርስም ሆነ ከእንግዳ ጋር ሲወያዩ አዳምጣ የበኩሏን አስተያየት ለመሰንዘር ስትሞክር "አይ! የምን ቀደም ቀደም ነው!" ተብላ ገና በጧቱ ቀንዷን ትመታለች ከማበረታቻ ይልቅ ወቀሳን በአእምሮዋ ትሰንቃለች የዝምታን "ወርቅነት" እያንገሸገሻት እንደ ኮሶ ጨልጣ ታድጋለች፡፡ ያ መራራ ኮሶ ደግሞ በአእምሮዋ ሰርጾ ለዝምታ ይዳርጋታል፡፡

የዝምታ በሽታ ተስፋፍቶ ጠባሳው በየስራ ገበታው ሁሉ መታየቱ አይካድም በየቀበሌው፣ በየመስሪያ ቤቱ፣ በየትምህርት ቤቱ በአእምሮው የሚጉላላውን ጠቃሚ ሃሳብ ከሚሰነዝረው አፉን ባደባባይ ሸብቦ በየጓዳ ጐድጓዳው የሚተነፍሰው ይበረክታል፡፡ ይህ ልማድ ለሀገር እድገት የሚበጅ አይደለም፡፡ ጥሩውን መልካም መጥፎውን መጥፎ እያልን ታታሪዎችን አበረታትተን ዋልጌዎችን ካልወቀስን ዕድገታችን ይገታል በሽታን ካልተናገሩ ፈውስ አይገኝምና በተገቢው ስፍራና ሁኔታ የመናገር ባህል ልናዳብር ይገባል፡፡

"የዝም የዝምታ" የተባልን ይመስል አንደበታችንን ለጉመን መቀመጣችን ትርፉ አጎብዳጅነትን ተለማማጭነትን በራስ ያለመተማመን በጨቅላ አእምሮ በማስረጽ እድገትን መግታት ነውና ይህ ልምድ መወገድ ይኖርበታል፡፡ ይህን ስር የሰደደ የውይይት አሜኬላ ከስሩ ገርስሰን ለመጣል መነሳት አለብን፡፡ ችግሩ መንታ በቀል ነው፡፡ ገና ከጨቅላነቱ ጀምሮ የብሂሉን "ፋይዳ" ከእናቱ ጡት ጋር ቀላቅሎ እየማገ ያደገውን ወጣት ብቻ ሳይሆን አዋቂንም ጭምር ይጐዳል፡፡ አንጋፋው ትውልድ ከአዲሱ ትውልድ አስተያየት ተቀብሎ ጉድፉን ለመንቀስ ሲጥር አይታይም፡፡ በእፍኙ የዘገናት እውቀት ጐተራ ሙሉ ትሆንበታለች፡፡

ስለዚህ ታዳጊው ትውልድ አስተያየቱን የመሰንዘርልምድ እንዲያዳብር ማበረታታት ይሻል፡፡ አዋቂውም ቢሆን በውል አዳምጦ ጠቃሚውን ሃሳብ ከጐጂው እየለየ የማሳየት ኃላፊነቱን ሊወጣ ይገባል፡፡ ያለበለዚያ "ልጅ ያቦካው ለራት አይበቃም" እያልን የባለ አደራውን አእምሮ ገና በእንጭጩ ከቀጨነው ሀገራችን ካለችበት የድህነት አረንቋ መንጥቆ የሚያወጣት ተመራማሪ አእምሮ ማግኘት ይቸግራል፡፡ እንክርዳድ ዘርቶ ስንዴ ለማዝመር መቋመጥ ሞኝነት ነውና ከወዲሁ ዘራችንን እናጥራ፡፡

/ ትምህርት ሚኒስቴር፣ 1992 ዓ.ም./

*መመሪያ አንድ፡- ምንባቡን መሠረት በማድረግ ለቃላቱ የሚስማማቸውን ፍቺ ምረጥ/ጭ/* (10%)

--------- 1. ርዕሰ ጉዳይ

*ሀ. ጠቃሚ ለ. ቁም ነገረኛ ሐ. ፍሬ ሃሳብ መ. አሳሳቢ ጉዳይ*

--------- 2. የበኩሏን

*ሀ. የፊናዋን ለ. የጉኗን ሐ. የሃሳቧን መ. የስሜቷን*

-------- 3. ታታሪ

*ሀ. ዝንጉ ለ. ዳተኛ ሐ. ቆፍጣና መ. ባተሌ*

-------- 4. ፈርጥ

*ሀ. ዘርፍ ለ. ጌጥ ሐ. ጥበብ መ. ደርዝ*

------- 5. እንድምታ

*ሀ. አንድ አይነት ለ. ትርጉም ሐ. አንዳፍታ መ. አንድ ላንድ*

*መመሪያ ሁለት፡- በምንባቡ ሃሳብ መሠረት ሀረጎቹ የሚያስተላልፉትን ሃሳብ ግለጽ/ጭ/* (5%)

1. *መልዕክትን ማንጠር*---------------------------------------------------------------------------------
   ---------------------------------------------------------------------------------------------------
2. *አፍራሽ መልዕክት ያዘሉ* ---------------------------------------------------------------------------
   ------------------------------------------------------------------------------------------------
3. *እንደበታችንን ለጉመን* --------------------------------------------------------------------------
   ------------------------------------------------------------------------------------------------
4. *አፉን ባደባባይ ሽብቦ*------------------------------------------------------------------------------
   ---------------------------------------------------------------------------------------------------
5. *ለሀገር እድገት አይበጅም*---------------------------------------------------------------------------
   ------------------------------------------------------------------------------------------------

***መመሪያ ሦስት፡-*** *ቀጥሎ የምንባቡን ዋና ዋና ሃሳቦች የሚመለከቱ ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡ የምንባቡን ሃሳብ በመንተራስ ለጥያቄዎቹ ትክክለኛውን መልስ ፃፍ/ፃፊ/፡፡* (2%)

1. *የአራተኛው አንቀጽ ዋና ሃሳብ ምንድን ነው?*-----------------------------------------------
2. *በአምስተኛውና በስድስተኛው አንቀጽ መካከል ያለው ሃሳብ ምንድን ነው?*-------------

***መመሪያ አራት፡-*** *የምንባቡን አጠቃላይ መልዕክት የሚመለከቱ ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡ ለቀረቡት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ስጥ/፡፡* (3%)

1. *እንደ ምንባቡ ሃሳብ ታዳጊ ወጣቶች አስተያየታቸውን ለመሰንዘር እንዳይደፍሩ የሚያደርጋቸው ምንድን ነው?*
2. *በምንባቡ የመጨረሻ አንቀጽ የመጨረሻ መስመር ላይ "እንክርዳድ ዘርቶ ስንዴ ለማዝመር መቋመጥ ሞኝነት ነውና ገና ከወዲሁ ዘራችንን እናጥራ" የሚለውን የሃሳብ አገላለጽ ከምንባቡ አጠቃላይ ሃሳብ ጋር እንዴት ይዛመዳል?*
3. *ለምንባቡ ተስማሚ ርዕስ ሰይሙ፡፡*

## አባሪ 2. የስነ ጽሁፍ ቡድን የፈተና መረጃ

| ቅድመ ፈተና | | | | | | | | ድህረ ፈተና | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ተቁ | ፈተና | ተቁ | ፈተና | ተቁ | ፈተና | ተቁ | ፈተና | ተቁ | ፈተና | ተቁ | ፈተና | ተቁ | ፈተና | ተቁ | ፈተና |
| 1 | 7 | 27 | 10 | 53 | 7 | 79 | 8 | 1 | 15 | 27 | 13 | 53 | 6 | 79 | 14 |
| 2 | 6 | 28 | 10 | 54 | 9 | 80 | 8 | 2 | 11 | 28 | 16 | 54 | 5 | 80 | 5 |
| 3 | 8 | 29 | 10 | 55 | 9 | 81 | 7 | 3 | 20 | 29 | 16 | 55 | 6 | 81 | 14 |
| 4 | 8 | 30 | 6 | 56 | 8 | 82 | 6 | 4 | 16 | 30 | 20 | 56 | 5 | 82 | 5 |
| 5 | 6 | 31 | 6 | 57 | 7 | 83 | 9 | 5 | 17 | 31 | 12 | 57 | 5 | 83 | 9 |
| 6 | 7 | 32 | 8 | 58 | 8 | 84 | 7 | 6 | 17 | 32 | 19 | 58 | 5 | 84 | 5 |
| 7 | 9 | 33 | 7 | 59 | 7 | 85 | 8 | 7 | 18 | 33 | 15 | 59 | 13 | 85 | 12 |
| 8 | 7 | 34 | 8 | 60 | 8 | 86 | 8 | 8 | 14 | 34 | 8 | 60 | 5 | 86 | 5 |
| 9 | 5 | 35 | 6 | 61 | 7 | 87 | 8 | 9 | 16 | 35 | 20 | 61 | 5 | 87 | 8 |
| 10 | 8 | 36 | 20 | 62 | 7 | 88 | 7 | 10 | 20 | 36 | 18 | 62 | 6 | 88 | 10 |
| 11 | 7 | 37 | 8 | 63 | 10 | 89 | 6 | 11 | 18 | 37 | 14 | 63 | 5 | 89 | 5 |
| 12 | 7 | 38 | 8 | 64 | 7 | 90 | 6 | 12 | 13 | 38 | 8 | 64 | 5 | 90 | 10 |
| 13 | 8 | 39 | 7 | 65 | 5 | 91 | 7 | 13 | 17 | 39 | 16 | 65 | 5 | 91 | 5 |
| 14 | 9 | 40 | 7 | 66 | 7 | 92 | 6 | 14 | 14 | 40 | 18 | 66 | 5 | 92 | 5 |
| 15 | 8 | 41 | 6 | 67 | 6 | 93 | 6 | 15 | 14 | 41 | 18 | 67 | 11 | 93 | 5 |
| 16 | 4 | 42 | 20 | 68 | 10 | 94 | 7 | 16 | 14 | 42 | 17 | 68 | 5 | 94 | 7 |
| 17 | 9 | 43 | 7 | 69 | 8 | 95 | 6 | 17 | 14 | 43 | 13 | 69 | 5 | 95 | 6 |
| 18 | 7 | 44 | 7 | 70 | 5 | 96 | 8 | 18 | 19 | 44 | 20 | 70 | 6 | 96 | 12 |
| 19 | 10 | 45 | 7 | 71 | 5 | 97 | 6 | 19 | 17 | 45 | 8 | 71 | 15 | 97 | 10 |
| 20 | 8 | 46 | 8 | 72 | 7 | 98 | 6 | 20 | 18 | 46 | 12 | 72 | 5 | 98 | 6 |
| 21 | 9 | 47 | 20 | 73 | 8 | 99 | 7 | 21 | 18 | 47 | 18 | 73 | 15 | 99 | 12 |
| 22 | 9 | 48 | 7 | 74 | 7 | 100 | 10 | 22 | 14 | 48 | 17 | 74 | 14 | 100 | 10 |
| 23 | 9 | 49 | 8 | 75 | 8 | 101 | 6 | 23 | 14 | 49 | 13 | 75 | 5 | 101 | 5 |
| 24 | 9 | 50 | 8 | 76 | 7 | 102 | 10 | 24 | 15 | 50 | 8 | 76 | 12 | 102 | 12 |
| 25 | 10 | 51 | 10 | 77 | 8 | | | 25 | 17 | 51 | 20 | 77 | 15 | | |
| 26 | 6 | 52 | 8 | 78 | 7 | | | 26 | 15 | 52 | 8 | 78 | 5 | | |

## አባሪ 3.የኢስነ ጽሁፍ ቡድን የፈተና መረጃ

| ቅድመ ፈተና | | | | | | | | ድህረ ፈተና | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ተቁ | ፈተና | ተቁ | ፈተና | ተቁ | ፈተና | ተቁ | ፈተና | ተቁ | ፈተና | ተቁ | ፈተና | ተቁ | ፈተና | ተቁ | ፈተና |
| 1 | 8 | 27 | 10 | 53 | 6 | 79 | 8 | 1 | 8 | 27 | 11 | 53 | 6 | 79 | 9 |
| 2 | 6 | 28 | 10 | 54 | 9 | 80 | 8 | 2 | 6 | 28 | 4 | 54 | 8 | 80 | 5 |
| 3 | 8 | 29 | 10 | 55 | 9 | 81 | 6 | 3 | 7 | 29 | 4 | 55 | 9 | 81 | 10 |
| 4 | 8 | 30 | 6 | 56 | 8 | 82 | 6 | 4 | 8 | 30 | 5 | 56 | 5 | 82 | 5 |
| 5 | 6 | 31 | 6 | 57 | 7 | 83 | 9 | 5 | 9 | 31 | 12 | 57 | 5 | 83 | 9 |
| 6 | 7 | 32 | 8 | 58 | 8 | 84 | 7 | 6 | 17 | 32 | 8 | 58 | 5 | 84 | 5 |
| 7 | 9 | 33 | 7 | 59 | 7 | 85 | 8 | 7 | 9 | 33 | 15 | 59 | 4 | 85 | 10 |
| 8 | 7 | 34 | 8 | 60 | 8 | 86 | 8 | 8 | 5 | 34 | 7 | 60 | 5 | 86 | 5 |

| | | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 9 | 5 | 35 | 6 | 61 | 7 | 87 | 8 | 9 | 12 | 35 | 4 | 61 | 5 | 87 | 8 |
| 10 | 8 | 36 | 20 | 62 | 7 | 88 | 7 | 10 | 9 | 36 | 5 | 62 | 6 | 88 | 10 |
| 11 | 7 | 37 | 8 | 63 | 10 | 89 | 6 | 11 | 14 | 37 | 9 | 63 | 16 | 89 | 5 |
| 12 | 7 | 38 | 8 | 64 | 7 | 90 | 6 | 12 | 5 | 38 | 8 | 64 | 6 | 90 | 10 |
| 13 | 8 | 39 | 7 | 65 | 5 | 91 | 7 | 13 | 6 | 39 | 5 | 65 | 12 | 91 | 5 |
| 14 | 9 | 40 | 7 | 66 | 7 | 92 | 6 | 14 | 13 | 40 | 10 | 66 | 5 | 92 | 4 |
| 15 | 8 | 41 | 6 | 67 | 8 | 93 | 6 | 15 | 7 | 41 | 4 | 67 | 11 | 93 | 13 |
| 16 | 4 | 42 | 20 | 68 | 10 | 94 | 7 | 16 | 7 | 42 | 7 | 68 | 10 | 94 | 7 |
| 17 | 9 | 43 | 7 | 69 | 8 | 95 | 6 | 17 | 13 | 43 | 9 | 69 | 8 | 95 | 6 |
| 18 | 9 | 44 | 7 | 70 | 5 | 96 | 8 | 18 | 8 | 44 | 3 | 70 | 6 | 96 | 12 |
| 19 | 10 | 45 | 7 | 71 | 5 | 97 | 6 | 19 | 20 | 45 | 8 | 71 | 11 | 97 | 10 |
| 20 | 8 | 46 | 8 | 72 | 7 | 98 | 6 | 20 | 15 | 46 | 10 | 72 | 5 | 98 | 6 |
| 21 | 9 | 47 | 20 | 73 | 8 | 99 | 7 | 21 | 9 | 47 | 6 | 73 | 6 | 99 | 12 |
| 22 | 9 | 48 | 7 | 74 | 7 | 100 | 10 | 22 | 7 | 48 | 7 | 74 | 11 | 100 | 10 |
| 23 | 10 | 49 | 8 | 75 | 8 | 101 | 6 | 23 | 9 | 49 | 10 | 75 | 5 | 101 | 5 |
| 24 | 9 | 50 | 8 | 76 | 7 | 102 | 10 | 24 | 11 | 50 | 8 | 76 | 5 | 102 | 13 |
| 25 | 10 | 51 | 10 | 77 | 8 | | | 25 | 20 | 51 | 20 | 77 | 7 | | |
| 26 | 7 | 52 | 8 | 78 | 8 | | | 26 | 16 | 52 | 6 | 78 | 7 | | |

**አባሪ 4፡- በስነፅሁፍና በኢ-ስነፅሁፋዊ ፅሁፍ ለሚማሩ የቀረበ የድህረትምህርት ፈተና ምንባብ**

በስነፅሁፍና በኢ-ስነፅሁፋዊ ፅሁፍ ለሚማሩ ተማሪዎችየአማርኛ ቋንቋን የአንብቦ መረዳት ክሂልን ከማሻሻል ረገድ ያለው ሚና በሚል ርዕስ ለሚካሄደው ምርምር መረጃ እንዲያስገኝ ለ10ኛ ክፍል ተማሪዎች የተዘጋጀ የአማርኛ ቋንቋ ድህረ ትምህርት ፈተና /20%/

የፈተናው መነሻ ሰዓት 3፡00

ለፈተናው የተሰጠ ጊዜ 2፡00

**አጠቃላይ መመሪያ**

ይህ ፈተና የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለመለካት የቀረበ ነው፡፡ ጥያቄዎቹ በቀረበው የምንባብ ሃሳብ መሠረት የሚመለሱ ሆነው አራት ንዑሳን ክፍሎች አሏቸው፡፡ የመጀመሪያው ክፍል ለቃላት የሚስማማቸውን ፍቺ ከተሰጡት አማራጮች ውስጥ መምረጥ፣ ሁለተኛው ምንባቡን መሠረት በማድረግ ሀረጉችና ዓረፍተ ነገሮቹ የሚያስተላልፉትን ሃሳብ መግለጽ፣ ሦስተኛው የምንባቡን ዋና ዋና ሃሳቦች ለይቶ ማውጣት፣ አራተኛው የምንባቡን መልዕክት መፃፍ ናቸው፡፡

ሁሉንም ጥያቄዎች ለመስራት የተፈቀደው ጊዜ 2፡00 ሰዓት ነው፡፡ በተሰጠው ጊዜ የሁሉንም ጥያቄዎች መልስ ፃፍ/ፊ/፡፡

ቀጥሎ የቀረበውን ምግባብ አንብባችሁ ከምንባቡ በኂላ የቀረቡትን ጥያቄዎች እንደአጠያየቃቸው መልሱ፡፡

## ምንባብ

ነጋ አባጀበል ትውልዱም እድገቱም ጅማ ከተማ ነው። ገና የአንደኛ ደረጃ ተማሪ በነበረበት ወቅት አጫጭር ግጥሞችን መፃፍ ያዘወትር ነበር። ለሥነጽሁፍ ያለው ፍቅር በጨቅላ አእምሮው ውስጥ መጠንሰስ የጀመረውም በዚሁ ጊዜ ነበር። አሁን የአስራ አንደኛ ክፍል ተማሪ ነው። የሥነ ጽሁፍ ክበብ አባልና ግንባር ቀደም ተሳታፊም ነው። በእረፍት ሰዓት በሚተላለፈው የትምህርት ቤቱ የሬድዮ ኘሮግራም ትምህርት ሰጪና አዝናኝ የሆኑ ግጥሞችን አጫጭር ልብ ወለዶችንና ጭውውቶችን እያሰናዳ ስለሚያቀርብ ታዋቂነት አግኝቷል።

ደብዳቤ የመፃፃፍ ልምድም አለው። የሚጽፈውም በደብዳቤ ከተዋወቃቸው የብዕር ጓደኞቹ ጋር ሲሆን ጥቂቶቹ ከሀገር ውጪ አብዛኞቹ ግን በሀገራችን የተለያዩ ክፍሎች የሚኖሩ ናቸው። ከእድሜ እኩዮቹ ጋር በሚያደርገው የደብዳቤ ልውውጥ ብዙ ቁም ነገሮችን ገብይቷል። ከመኖሪያ አካባቢው ርቀው የሚገኙ ሰዎችን ባህል፣ ማህበራዊ ህይወት፣ የአካባቢዎቹን መልካምድራዊ አቀማመጥና የአየር ጠባይ ለመረዳት የቻለው ከጓደኞቹ የብዕር ትሩፋት ነው። የሰው በልቶ አያድሩም ተኝቶ እንዳሉ፣ እሱም ተገቢውን ምላሽ የመስጠት ልምድ አካብቷል።

ከብዕር ጓደኞቹ አንዱ የሆነው ሀቢብ ያዩ የፃፈለት ደብዳቤ የደረሰው ከጥቂት ቀናት በፊት ነው። ላኪው የአፋር ብሔረሰብ ተወላጅ በመሆኑ በደብዳቤው ላይ የብሔረሰቡን የጋብቻ ልማድ በዝርዝር አትቷል። ነጋም ቀደም ሲል እንደሚያደርገው የደብዳቤውን ይዘት ለትምህርት ቤት ጓደኞቹ ለማስተላለፍ ደፋ ቀና ማለቱን ተያይዞታል።

በደብዳቤው ላይ የሰፈረውን መልዕክት ቃል በቃል ማሰማቱ አልታይህ አለው። ስለዚህ ታሪክ ፈጥሮ፣ ሴራ አሰናስሎ በውብ ቋንቋ የተከሸነ አጭር ልብ ወለድ ሊያነጉት ፈለገ። ይሁንና ይህን የብዕር ትኩሳቱን በረዶ እንደተዘረገፈበት ረመጥ ያከሰመው አሳሳቢ ችግር ተፈጠረ። እንኳን ልብ ወለድን የሚያህል በሳቢያና በውጤት የሚተበተብ ሴራ ይቅርና ለቅርብ ጓደኛ የሚፃፍ ማስታወሻ እንኳን ብዙ ሊያሳስብ እንደሚገባ ለአፍታ በመዘንጋቱ ራሱን ታዘበው።

